# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 213 ሚያዝያ 3 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# የሕዝብ ጥያቄዎችን በየደረጃው ለመመለስ እየሰራ መሆኑን የሱማሌ ክልል አስታወቀ



ፍቃዱ ዴረሳ

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ መድረኮች ሕዝቡ ያነሳቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ እየሰራ መሆኑን የሱማሌ ክልል አስታወቀ። የሕግ የበላይነት፣ የጎሳ ግጭት፣ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች፣ መልካም አስተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ፤ የኑሮ ውድነት እንዲሁም የመሬት ወረራ ሕብረተሰቡ በስፋት ያነሳቸው ጥያቄዎች ነበሩ።

የሶማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሃመድ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት ብልፅግና ፓርቲ በቅርቡ ባካሄደው ጉባኤው የወሰናቸውን ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ በመልካም አስተዳደር፣ ልማት እንዲሁም በሰላምና ሌሎች ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የክልሉን ሕዝብ ያሳተፈ ውይይት መደረጉን አስታውሰዋል።

በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ከማሕበረሰቡ ጋር በተደረገው ውይይት መሰረት በመንግሥትና በፓርቲው የተከናወኑ በርካታ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉ ሁሉ መስተካከል አለባቸው ብሎ ያመነባቸውን ሃሳቦችና ጥያቄዎች መነሳታቸውን ገልጸዋል።

በተለይም ከዚህ በፊት ማሕበረሰቡ ከሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መካከል የሰላም ጥያቄ አንዱና ዋነኛው በመሆኑ ፓርቲውና መንግሥት ትኩረት አድርገው በሰራቸው


**የሕዝብ ጥያቄዎችን በየደረጃው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**


# «ለብሄራዊ መግባባት ውይይቱ ስኬታማነት ሁሉም መብቱን ሊጠቀምና ሃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል»

- ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ
የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሰብሳቢ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ለብሄራዊ መግባባት ውይይቱ ስኬታማነት በአገር ውስጥና በተለያዩ የውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሙሉ መብታቸውን ሊጠቀሙና ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ሰብሳቢ ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ገለጹ።

ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለብሄራዊ መግባባት ውይይቱ ስኬታማነት ሁሉም መብቱን ሊጠቀምና ሃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል። ወሳኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ሕዝቡ የሰላም እጦትና ጦርነት አንገሽግሾታል፣ ከባድ መስዋዕት ከፍሏል ከዚህ መውጣት ይፈልጋል።

ሁሉንም ነገር ብሄራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ይፈታዋል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ተግባር አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠርና ማመቻቸት ነው። ውሳኔና ሃላፊነቱ የሕዝቡ ነው ብለዋል።

ወጣቶች በስፋት ሊሳተፉ ይገባል። የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚያንገበግባቸው፣ ስለኢትዮጵያ ያገባናል የሚል



ወገን በሙሉ ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ መጻኢ እጣ ፈንታ ተወያይቶ መወሰን አለበት። ሚዲያውም ለሕዝብ ቅርብ መሆን፣ ለሰላም መስፈን መስራት ይጠበቅበታል።

አጀንዳው የሚሰበሰበው ከሕዝብ ነው። ጉዳዮች ተነቅሰው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በማስቀደም የመጀመሪያ ውይይት ይካሄዳል። ገለልተኛ የሆኑ፣ የሕዝብን አጀንዳ እንደራሳቸው አድርገው ትክክለኛ የውይይት መርሃ ግብሩን የሚያስፈጽሙ አወያዮች እንደሚኖሩም ጠቁመዋል።

«በጦርነት በርካታ ወጣቶች አጥተናል፣ አካል ጎድሏል፣ ረሃብም አንገሽግሾናል ሕዝቡ ይበቃል ብሏል። ውይይቱን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለራሱ ሲል እንደሚያሳካው የተስፋ ጭላንጭል ይታየኛል፣ አሁን ጉዳዩ አገር ሆኖ የመቀጠልና ያለመቀጠል ስለሆነ ትኩረት በመስጠት ስኬታማ ውይይት ለማድረግ መነሳት ያስፈልጋል» ብለዋል።

ውይይቶቹ ወደ መግባባት እንደሚወስዱ ተስፋ እናደርጋን። የውይይት ውጤቶቹ በእርቅና የአገር ግንባታ ላይ የራሱ ተጽእኖ ይኖረዋል። ከጅማሬው ስራዎቻችን በጥንቃቄና በጥራት መጀመር አለብን በሚል እምነት ስራዎች እየሰራን እንገኛለን ሲሉ ተናግረዋል።

የተሰሩ ስራዎች፣ የተጻፉ ጽሁፎች፣ በክልሎችና በከተሞች የተካሄዱ ሕዝባዊ ውይይቶች በግብአት መልኩ


**«ለብሄራዊ መግባባት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**
















## በኦሮሚያና በሱማሌ ክልሎች ከድርቁ ተጨማሪ የአንበጣ ወረርሽኝ ሥጋት መሆኑ ተጠቆመ


ገጽ 4










አቶ ግርማ ሃይሉ

## ዞኑ ሕብረተሰቡን በሚያጉላሉና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ በማይወጡ አመራሮች ላይ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን አስታወቀ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሕብረተሰቡን በሚያጉላሉና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በማይወጡ አመራሮች ላይ የእርምጃ እየወሰደ መሆኑን በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ግርማ ሃይሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት ቀደም ሲል በዞኑ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመለየት በተደረገው እንቅስቃሴ በተለያዩ ሴክተሮች ባለጉዳይ የማጉላላት፣ ጉቦ የመፈለግ አዝማሚያና የአገልጋይነት መንፈስ መጓደል የመሳሰሉት ችግሮች ታይተዋል።

ሰሞኑን በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች እንደተደረገው ሁሉ በልዩ ዞኑም ሰፊ ሕዝባዊ ውይይት መደረጉን ያነሱት ዋና አስተዳዳሪው፣ በየእለቱ ሕዝብ የሚገለገልባቸው እንደ ትራንስፖርት፣ የመሬት አስተዳደርና ማዘጋጃ አካባቢዎች ዙሪያ ሕዝቡ በስፋት ችግሮች አንስቷል። ዞኑም እነዚህን ችግሮች በመንተራስ እርምጃዎች መውሰድ ጀምሯል።

እንደ ችግሩ ክብደት ደሞዝ የመቁረጥ፣ ከደረጃ ዝቅ የማድረግና ወደ ሕግ የማቅረብ ስራ እየተሰራ መሆኑን የተናገሩት አቶ ግርማ፣ የተለያየ ችግር በመፍጠር በመንግሥትና በሕዝብ መከከል አመኔታ እንዲፈጠር በሚያደርጉና የተሰጣቸውን አደራ ወደ ጎን በመተው ሕዝቡን በሚያማርሩ አመራሮች ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ እንደሚወሰድ ጠቁመዋል።

በውይይት መድረኩ የዞኑ ነዋሪዎች ያነሷቸው የመንገድ፣ የውሃ፣ የመብራትና የመሰረተ ልማት ጥያቄዎች መኖራቸውን የጠቀሱት ዋና አስተዳዳሪው፣ በዞኑ ደረጃ የሚሰራውን አቅም በፈቀደ መልኩ እየሰሩ በክልልና በፌዴራል ደረጃ የሚመለሱት ደግሞ በደረጃው አቅርበው ምላሹን እየተጠባበቁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ዞኑ ከሁሉም በላይ ምክርን ያስቀድማል ያሉት አቶ ግርማ፣ ስለዚህ ሁሉም አመራር ከሕዝብ አብራክ መውጣቱን በመገንዘብ ሕዝቡን በቅንነትና በታማኝነት ራሱን እንዲያዘጋጅ ጠይቀዋል።

በዞኑ ገበያን ለማረጋጋት በዘንድሮ ዓመት 18 ሺህ ሄክታር መሬት በመስኖ ስንዴ ተሸፍኖ 900ሺ ኩንል ምርት ለማግኘት እየተሰራ መሆኑንና መንግሥት በድጎማ የሚያቀርባቸውን መሰረታዊ ሸቀጦች ለሕዝቡ የማድረስ ስራ እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል። ሸቀጦቹን የሚደብቁ ነጋዴዎች ላይ በተደረገው ጥብቅ ቁጥጥር በርካታ ሺህ ሊትር የተደበቀ ዘይት መያዙን ተናግረዋል።

ዘይቱን ለሕዝብ ነጋዴዎቹን ደግሞ ለሕግ ማቅረብ መቻላቸውን የተናገሩት ዋና አስተዳዳሪው፣ ወንጀል ለመከላከልና ገበያን የማረጋጋት ስራ ለማሳለጥም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በተቀናጀ መልኩ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

ከማዳበሪያ አቅርቦት ጋር ተያይዞ ሕዝቡ ያነሳውን ጥያቄ በሁለት መንገድ ለመፍታት መዘጋጀታቸውን የገለጹት አቶ ግርማ፣ መንግሥት ከሚያቀርበው ማዳበሪያ በተጨማሪ ሕዝቡ በብዛት የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል።



# በመተከል ዞን የነበረውን አለመረጋጋት በዘላቂነት ለመፍታት እርቀ ሰላም ተካሄደ

አዲስ አበባ፡- በመተከል ዞን የነበረውን አለመረጋጋት በዘላቂነት ለመፍታት "ከልብ የመነጨ እርቅ ለዘላቂ ሰላም" በሚል መሪ ሃሳብ በግልገል በለስ ከተማ በባህላዊ የእርቅ ሥነ-ሥርዓት ክዋኔ እርቀ ሰላም ተካሄደ።

በእርቀ ሰላም ፕሮግራሙ ላይ የመንግሥትን የሰላም ጥሪ የተቀበሉ ወጣቶች፣ በድርጊታቸው የተጸጸቱ የተሃድሶ ስልጠና ሲወስዱ የነበሩ የጉህዴን አባላት፣ የብሄረሰቡ የአገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች እና የመንግሥት ከፍተኛ የስራ ሃላፊዎች ተገኝተዋል።

ወጣቶች በተሃድሶ ስልጠናው ያገኙትን ግንዛቤ ወደ ተግባር በመቀየር ከሕዝቦች ጋር የነበረውን አብሮነት በማጠናከር ወደ ልማት ለመግባት የተደረገውን እርቀ ሰላም ለማስቀጠል መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

በመተከል ዞን ትጥቅ በመፍታት የመንግሥትን የሰላም ጥሪ የተቀበሉ እርቀ ሰላም የፈጸሙ የጉህዴን አባላት ማንዱራ፣ ድባጤ፣ ቡለን፣ ወምበራና ዳንጉር ወረዳዎች ውስጥ የነበሩ ናቸው።

በእርቀ ሰላም ፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የመተከል ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ጋሹ ዱጋዝ፤ የጠላትን አጀንዳ ከማስፈጸም በመቆጠብ የሰላምን አስፈላጊነት ለሌሎች ግለሰቦች ግንዛቤ በመስጠት ወደ ሰላም ተመልሰው ይቅርታና ምህረትን በእርቀ ሰላም በመፍታት ወደ ልማት መግባት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የይቅርታና ምህረት ፕሮግራሙ የተካሄደው በጉሙዝ ብሄረሰብ ዘንድ ግጭቶችን በዘላቂነት ለመፍታት በሚታወቀው ባህላዊ የእርቅ ሥነ-ሥርዓት ክዋኔን መሰረት በማድረግ መሆኑን ከመተከል ዞን ኮሙኒኬሽን ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።

# 80 በመቶ የሚሆነውን የኮንስትራክሽን ግብዓት በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት እየተሠራ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዳማ፡- በኮንስትራክሽን ዘርፍ ውስጥ 80 በመቶ የሚሆነውን ዋና ዋና ግብዓት በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን የኮንስትራክሽን ማኔጅመነት ኢንስቲትዩት ገለጸ።


ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ታምራት ሙሉ በዘርፉ የአሥር ዓመት እቅድ ውስጥ 80 በመቶ የሚሆነውን ዋና ዋና የኮንስትራክሽን ግብዓት በአገር ውስጥ ምርት ለመተካት መታቀዱን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ እስከ 60 በመቶ የሚሆኑ መሠረታዊ የግንባታ ግብዓቶች ከውጭ የሚገቡ ናቸው ያሉት ዳይሬክተሩ በዚህ መጠን ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ ጥገኛ ሆኖ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለመገንባት አስቸጋሪ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ወደ ግማሽ ምዕተ ዓመት ያስቆጠረ ቢሆንም በሚፈለገውና በሚገባው ልክ ያላደገው እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የዕድሜው ቆይታን ያህል ተወዳዳሪ መሆን ያልቻለው ዘርፉ በውጭ ግንባታ ግብዓቶችና መሣሪያዎች ላይ ጥገኛ በመሆኑ ነው ብለዋል።

ውስብስብ የሆኑ ሕንፃዎች፣ ትላልቅ ፕሮጀክቶች እና የባቡር መንገድ ግባታዎች በአመዛኙ እየተከናወኑ ያሉት በውጭ የሥራ ተቋራጮች መሆኑንም ለዘርፉ የውጭ ጥገኝነት በአብነት አንስተዋል።

በዚህም ምክንያት አሁን ያለው ዓለም አቀፍ ገፅታ



ተፅዕኖው በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ላይ በቀጥታ እንዲንፀባረቅ እንዳደረገ ይገልፃሉ።

ሀገሪቱ ከጥገኝነት ለማላቀቅም መንግሥት አገር በቀል የግንባታ ግብዓቶችን ማምረት የሚያስችሉ የፈጠራ ሥራዎችን እያበረታታ መሆኑን ተናግረዋል።

አገሪቱ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የምትጠቀማቸው ቴክኖሎጂዎች፣ የግንባታ ግብዓቶች በአብዛኛው በውጭ ምርት ላይ ጥገኛ መሆናቸውን ለመቅረፍ አገር በቀል ዕውቀቶችና የፈጠራ ሥራዎች ላይ በትኩረት እየሠራን ነው ሲሉም አክለዋል።

የዘርፉን ችግሮች በአገር በቀል ዕውቀትና ፈጠራ ሥራዎች ለመፍታት የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ከተረፈ ምርቶች ሠርተው ያቀረቡ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ኮሌጆች እና ግለሰቦች እንዳሉ ገልጸው በርካታ የፈጠራ ሥራዎች ወደ ሽግግርና ስርጸት እንዲያመሩ ለማድረግ የሚመለከታቸው አካላት እንዲሳተፉና ፈጠራዎችን እንዲመለከቱ እያደረግን ነውም ብለዋል።

እንደዚህ ዓይነት ምርትቶች አካባቢን ከብክለት የሚከላከሉ፣ ለዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩና የውጭ ምንዛሬ እጥረትን የሚቀርፉ ከመሆናቸውም በላይ የዘርፉን ግብዓቶች በአገር በቀል ምርት ለመተካት ከፍተኛ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

የኮንስትራክሽን ማኔጅመነት ኢንስቲትዩት በተለይ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም በዘርፉ የሚወጡ የፈጠራ ሥራዎችን በፋይናንስ እየደገፈ ይገኛል ያሉት ዳይሬክተሩ የኮንስትራክሽ ግብዓት አምራቾችን በቀጥታና ሙሉ በሙሉ በፋይናንስ በመደገፍ ብቻ ሳይሆን በፋይናንስ ከሚደግፋዋቸው ጋር በማገናኘት እና የገበያ ዕድሎችን በመፍጠርም ሚናውን እየተወጣ መሆኑም ጠቁመዋል።

እንደ ኢንጂነር ታምራት ገለጻ በተጨማሪ ከዚህ በፊት ይደረግ የነበረው በተለይ በኮንስትራክሽን ዕቃዎች ግዢ ላይ የሚወጡ ደረጃዎች የአገሪቱን ምርት ሳይሆን የውጭ ምርቶችን እንዲገዙ የሚያደርጉ ናቸው። ለወደፊት አሁን በሙከራ ደረጃ የተጀማመሩት የገበያ ዕድላቸው እንዲሠፋ የጨረታ ሰነዶችና የመሳሰሉት የግዢ ሂደቶች የአገር ውስጥ ምርቶችን ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ ይደረጋል።

ይህም አገር በቀል ዕቀውቀቶችንና ፈጠራዎችን በማበረታታት የግንባታ ግብዓቶችንና የማምረቻ መሣሪዎችን ለመተካት የሚደረገውን ጥረት የሚደግፍ እንደሆነ ኢንጅነር ታምራት ተናግረዋል።

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዩማን ራይትስ ዎች በጋራ ያወጡትን ሪፖርት እንደማይቀበለው ገለጸ

አዲስ አበባ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዩማን ራይትስ ዎች በጋራ ያወጡት ሪፖርት ሚዛናዊነት የጎደለው፣ ለአንድ ወገን ያደላ እና ተዓማኒነት የሌለው እንዲሁም የተቋማቱን ፖለቲካዊ ወገንተኝነት የሚያሳብቅ ነው ሲል ገለጸ።

ክልሉ ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ፤ የተቋማቱ ሪፖርት በአፍሪካ ሕብረት የሕዝቦች መብት ጥበቃ ኮሚሽን ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጽህፈት ቤት የሰብአዊ መብትቶች ጥበቃ ከፍተኛ ኮሚሽን እና በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የጋራ ጥምረት የተከናወኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምርመራ ጥረቶችን ዋጋ የሚያሳጣና በሰብአዊ መብቶች ጠበቃነት ካባ ተሸፍኖ በሰብአዊነት ላይ በገሀድ የተፈጸመ ኢ-ሞራላዊ ጥቃት ሆኖ እንዲታይ ያደርገዋል ብሏል።

መግለጫው አክሎ እንዳተተውም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በየትኛውም ዘመን፤ በማንኛውም የዓለማችን አገራት ሕዝቦች እና ማንኛውም አይነት የብሔር፣ ሃይማኖትም ሆነ የቆዳ ቀለም ባለው ሰብአዊ ፍጡር ላይ የተፈጸሙ በማንኛውም ደረጃ የሚገለጹ ሁሉንም አይነት የመብት ጥሰቶችን ይቃወማል።

ማንኛውም አይነት የተቃርኖ ምክንያቶችን ተገን በማድረግ በሰው ልጅ ላይ የሚፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን፤ የዘር ማጥፋትም ሆነ የጦር ወንጀሎችንም ያወግዛል። ይህን መሰል እኩይ ድርጊቶችን ለመከላከልም ሆነ ጥፋተኞችን ለሕግ ለማቅረብ የሚደረጉ ምርመራዎችን ያደንቃል፤ ያበረታታልም።

የክልሉ መንግሥት ለሰብአዊ መብቶች መከበር ያለው ውግንና የሚመነጨው ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ የሰብአዊ መብቶችን ለማስጠበቅ ላጸደቃቸው ሕጋዊ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ባለን ቀናዒነት ብቻ ሳይሆን የአማራ ሕዝብ ቀደምት ሁለንተናዊ የሥልጣኔ ትሩፋቶቹን ተመርኩዞ ማሕበረሰባዊ ሰብእናውን የቀረጸባቸው የባህል፣ የሞራል፣ የእሴቶቹ እና የመለኮታዊ አስተምህሮቶቹ ስለማይፈቅዱለትም ጭምር ነው። ለሰብአዊ መብቶች መከበር ሲባል የጸደቁና አገራችን የተቀበለቻቸው የሕግ ማዕቀፎችና ድንጋጌዎች ሁሉ በክልሉ ውስጥም ሆነ ከክልሉ ውጭ ባልተሸራረፈ መልኩ ተፈጻሚነታቸው እንዲረጋገጥ ያላሰለሰ ጥረት እያደረግን የምንገኝበት ዐቢይ ምክንያትም ይኸው ነው።

ይሁን እንጂ ‹ሰብዓዊ መብቶችን ለማስከበር ጥብቅና ቆመናል› የሚሉ አንዳንድ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ አሸባሪ እና ወራሪው የሕወሓት ቡድን የአማራ ሕዝብን ሕልውና ለማክሰምና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለመናድ አልሞ የከፈተውን ጦርነት ተከትሎ የተከሰተው ቀውስ ላይ ተመስርተው የአማራ ክልል መንግሥትን እና ሕዝብን ‹‹የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፤ የዘር ማጥፋትና የጦር ወንጀሎችን›› ፈጽመዋል የሚሉ ገለልተኛነት፤ ሚዛናዊነት እና ተዓማኒነት በሌላቸው ሪፖርቶች ላይ የተመሰረቱ፤ በጦርነቱ የተፈጠሩ ሰብአዊ ቀውሶችን ለማከምም ሆነ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመከላከል አጋልባችና አዎናታዊ ሚና የሌላቸው ሐሰተኛ ክሶችን በተደጋጋሚ ሲያሰሙ ተስተውለዋል።

እነዚሁ አካላት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ኤፕሪል 6/2022 በሂዩማን ራይትስ ዎች እና በአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጥምረት የተዘጋጀውና በሰብዓዊ መብት ላይ የሚፈፀሙ ከባድ ጥሰቶችን በማስታከክ ‹‹የጦር ወንጀል›› እና ‹‹የዘር ማጽዳት›› ክሶችን ሽፋን አድርጎ በዋነኛነት በአማራ ክልል የወልቃይት ጠገዴ ሰቲት ሁመራ ዞን ላይ የሚያጠነጥን ሪፖርት ይፋ ማድረጋቸውን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ታዝቧል።

ሪፖርቱ የአማራ ክልል የመንግሥት ኃላፊዎችን፣ የልዩ ኃይል ፖሊስ አባላትን፣ ሚሊሻዎችን እና በሕግ ማስከበርና የህልውና ዘመቻ ላይ የተሳተፉ የፋኖ አደረጃጀትን ‹‹በንብረት ዝርፊያ››፤ ‹‹በአፈናቃይነት››፤ ‹‹በአስገድዶ መድፈርና የወሲብ ባርነት ፈጻሚነት››፤ ‹‹በጾታዊ ጥቃት››፤ ‹‹በዘር ማጥፋት››፤ ‹‹በጦር ወንጀልና እና በከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰት›› ፈጻሚነት ይወነጅላል። መሬት ላይ ያለውን ሐቅ ለሚያውቁ ገለልተኛ አካላት፤ ለክልላችን ሕዝብም ሆነ ለመላው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የሪፖርቱ ፋይዳ ከሦስት ግቦች አይዘልም።

አንደኛ፡- የሕዝባችንን ጨኸት ለመቀማትና የአገራቸውን ሉዓላዊነትና ህልውናቸውን ለማስከበር ብሔራዊ ግዴታቸውን በተወጡት የመንግሥት ኃላፊዎች፣ የጸጥታ መዋቅር አባላትና በሐቀኛ ፋኖዎች መካከል ያለውን ጠንካራ ትስስር በመስበር ወደፊትም በሉአላዊነታችን ላይ የሚጋረጥ አደጋ ቢመጣ በአንድነት መታገል የማይችል አቅመ ቢስ ሕብረት እንዲኖር የማድረግን ዓላማ ያነገበ ነው።

ሁለተኛ፡- በአሸባሪና ወራሪው የሕወሐት ቡድን ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉም አይነት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፤ የዘር ማጥፋትና የጦር ወንጀል ሰለባ በሆነው የአማራ ሕዝብ ቁስል ላይ እንጨት በመስደድ የአማራ ሕዝብን እንደ ሕዝብ ፍትህ በመንፈግ በኢትዮጵያዊነቱ እና በዓለም አቀፍ የፍትህ፤ የሰብአዊ መብት ተከራካሪና የዴሞክራሲ እሴት ግንባታ ባለድርሻ አካላት ላይ ተስፋ ቆርጦ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ እና የሕዝብና የግዛት አንድነትን ለማስከበር ያለውን ቁርጠኝነት በማሟሟት በብሔራዊ የእርቅና የምክክር መድረኮች ሰላምን ለማስፈንና ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን ለመገንባት የሚኖረውን ሚና ለማምከን ታስቦ የተዘጋጀ ደባ ነው።

ሦስተኛ፡- የማዕከላዊውም ሆነ የክልላችን መንግሥት ወታደራዊ ግጭትን በማቆም ለሰላምና ለሰብአዊ ድጋፎች ተደራሽነት በሙሉ አቅሙ እየተጋ በሚገኝበት ወቅት ይህ ሚዛናዊነት፤ ገለልተኛነት እና ተዓማኒነት የሌለው ሪፖርት ይፋ መደረጉ መንግሥት በአፍሪካ ሕብረት የህዝቦች መብት ጥበቃ ኮሚሽን (ACHPR)፣ በተባበሩት መንግሥታት ጽህፈት ቤት የሰብአዊ መብትቶች ጥበቃ ከፍተኛ ኮሚሽን (OHCHR) እና በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (EHRC) የጋራ ጥምረት የተከናወኑ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምርመራ ጥረቶችን ዋጋ የሚያሳጡና በሰብአዊ መብቶች ጠበቃነት ካባ ተሸፍኖ በሰብአዊነት ላይ በገሀድ የተፈጸመ ኢ-ሞራላዊ ጥቃት ሆኖ እንዲታይ ያደርገዋል።

በተለይም ሪፖርቱን ያዘጋጁት ተቋማት ከተመሰረቱበት ዓላማ ባፈነገጠ ሁኔታ በሪፖርታቸው ላይ የአገር ውስጣዊ የፖለቲካ ለውጦችን የማስተጓጎል፣ በክልሎች መካከል የሚገኙ የወሰን ጉዳዮች ላይ ብያኔ የመስጠት እንዲሁም በአንድ ሉዓላዊ አገር የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ገብቶ ሕዝብን ከሕዝብ የማጋጨት ጥረቶች መስተዋሉ አሸባሪው የሕወሃት ቡድን ጦርነቱን በከፈተበት የመጀመሪያዎቹ ወራት ላይ አንዳንድ ኃያላን አገራትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ሲሰነዝሩት የነበረውን ለአንድ ወገን ያደላ ሃሳብ በሪፖርታቸው ላይ አጭቀው ማቅረባቸው የክልላችን መንግሥት በሪፖርቱ ላይ ብቻ ሳይሆን ሪፖርቱን ባዘጋጁት ተቋማት ላይም ጭምር በገለልተኛነታቸው፣ በሚዛናዊነታቸውና በተዓማኒነታቸው ላይም ጭምር ጥርጣሬ እንዲኖረው አድርጓል።

የተቋማቱ ዋና መቀመጫ መሥሪያ ቤት በእንግሊዝ ለንደን እና በአሜሪካ ኒውዮርክ የሆነውና በሱዳን ምድር ሆነን 427 ተጠቂዎችን በአካልና በስልክ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ሪፖርቱን አዘጋጅተነዋል ያሉት የድርጅቶቹ ባለሙያዎች በስልክ ቃለ መጠይቅ አደረግንላቸው ያሏቸው አንዳንዶቹ ‹‹የዘር ማጥፋት ወንጀል ሰለባ ናቸው›› የተባሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች በአማራ ክልል ውስጥ የሚኖሩ በመሆናቸው በስልክ ለማግኘት መቻላቸውን መግለጻቸው እርስ በእርሱ ይጣረሳል።

ሱዳን ከሚገኙ ስደተኞች ሰበሰብነው ያሉት መረጃም ቢሆን የጥቅምት 30/2013 ዓ.ም. የማይካድራ ጭፍጨፋን ከትግራይ ልዩ ኃይልና ሚሊሻ ጋር ሆኖ ከመራውና ‹ሳምሪ› ከተሰኘው ኢ-መደበኛ አደረጃጀት ላይ እንደሆነ እናምናለን።

ከዓለምአቀፍ ሕግ በሚቃረን መልኩ በሱዳን የስደተኛ ካምፖች ውስጥ አሸባሪው ሕወሓት ንጹሃን የአማራ ተወላጆችን ለመጨፍጨፍ የተጠቀመባቸው የትግራይ ልዩ ኃይል፣ የሚሊሻና የኢ-መደበኛ አደረጃጀት አባላት በስደተኛ ስም እንደሚገኙ ይታወቃል። በሱዳን በኩል ስደተኛ ካምፕ ያሉትን እነዚህን ኃይሎች የሽብር ስልጠና በመስጠት በአማራ ክልል በቋራ እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ በኩል በንጹሃን፣ በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች እና በመሰረተ ልማት ላይ ጥቃት እንዲከፍቱ ስምሪት ሲሰጥ መቆየቱ ይታወሳል። የስደተኞች ካፕም ውስጥ ገብተው መታወቂያ (Refugee ID Card) የተሰጣቸው ነገር ግን አሸባሪው ሕወሓት ለጥፋት ተልዕኮ ወደ ኢትዮጵያ አስርጎ አስገብቷቸው በውጊያ የተማረኩ ምርኮኞች እንዳሉም ይታወቃል።

በተጨማሪም “በአፈናቃይነት” የተወነጀለው የአማራ ክልል መንግሥት በሚያስተዳድረው ክልል ውስጥ በርካታ የትግራይ ክልል ተወላጆች በንግድ ሥራ፣ በመንግሥት ሠራተኝነት፣... ወዘተ በተጨባጭ የሚኖሩ መሆኑን ዘንግቷል፤ አልያም ክዷል። ዛሬም ‹ሥርዓት ይመጣል፣ ይሄዳል፣... ይቀያየራል የሕዝብ ግንኙነት ግን ቋሚና ዘላቂ ነው› በሚል እምነት ከአማራ ወንድሞቻቸው ጋር በሰላምና በፍቅር የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች በክልላችን ውስጥ መኖራቸው የአማራ ሕዝብን አቃፊነት የሚያሳይ በመሆኑ የክልሉን መንግሥት ያኮራዋል።

እውነታው ይህ ሆኖ እያለ በሪፖርቱ ላይ የቀረበው ክስና ውንጀላ የተቋማቱን ፖለቲካዊ ወገንተኝነት የሚያሳብቅ ነው። ሌላኛው አሳዛኝ ሁነት ጥናቱን ለማከናወን በመረጃ ምንጭነት የተጠቀማቸው ግለሰቦች የአንዱን ማሕበረሰብ ወገን ብቻ መሆኑ ሪፖርቱ በመረጃ አሰባሰብ ሥነ-ዘዴው ደካማ መሆኑን ከማረጋገጡ ባሻገር በውጤቱም ሚዛናዊነት የጎደለው፣ ለአንድ ወገን ያደላ እና ተዓማኒነት የሌለው እንዲሆን አድርጎታል።

በዚህም ምክንያት ተቋማቱ አንድ ዓመት እንደፈጀባቸው የገለጹት የጥናት ውጤት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር አዎንታዊ ሚና ከመጫወት ይልቅ ችግሮችን የበለጠ የሚያወሳስቡ፣ ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶችን የሚያጨናግፉ፣ በተፈጠሩ ግጭቶች ምክንያት በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ሰለባ የሆኑ ዜጎች ፍትህና ርትዕን ለማረጋገጥ የሚቻልባቸውን ዕድሎች የሚያጠቡ ሆነው አግኝተናቸዋል።

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የጥናት ቡድን ለአስራ ስድስት ወራት ባደረገው ጥናት መሰረት በወልቃይት ጠገዴ በርካታ የጅምላ መቃብሮችን አግኝቷል። “ገሃነም” ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የሚገኙ በርካታ የሕወሓት የጉድጓድና የዋሻ ድብቅ እስር ቤቶች ላይ ጥናት ያደረገው ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው የአገር ሽማግሌዎችና የዓይን እማኞች በኩል ከተጠቆሙት የጅምላ መቃብሮች መካከል ለሙከራ አምስቱን አስቆፍሮ ጭካኔ በተሞላበት

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ‹‹ብሄራዊ ምክክሩ የሁሉንም ቀና ልብ የሚፈልግ ትልቅ አገራዊ ጉዳይ ነው››

## - ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ብሄራዊ ምክክሩ የሁሉንም ኢትዮጵያውያን ቀና ልብ የሚፈልግ ትልቅ አገራዊ ጉዳይ ነው ሲሉ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ አስታወቁ።

ኡስታዝ አቡበከር በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ አገሪቱ የረጅም ዓመት የታሪክ ባለቤት እንደመሆኗ መጠን በበርካታ ውጣ ውረዶች ውስጥ አልፋለች። በየትኛውም አገር እንዲከሰተው ሁሉ በታሪክ ሂደት አኩሪ ክስተቶች እንዳሉን ሁሉ የቅራኔ ምንጮችም ተከስተዋል። መልካም ነገሮቻችን በተገቢው በማጎልበት ወደ አለመረጋጋትና ግጭት የሚወስዱን ቅራኔዎች በመፈፍታት አገርና ሕዝብን ማሻገር በዚህ ትውልድ ላይ ተጥሏል።

እንደ ኡስታዝ ገለጻ፣ እንደ ጥላቻ፣ መገፋፋት፣ ክፋትና መለያየት ያሉ ብልሹ አስተሳሰቦች ኢትዮጵያን ትልቅ ዋጋ አስከፍለዋታል። አሁንም የሚያስፈልጉን ቅንነት፣ በጎነትና ወንድማማችነት ነው።

በመሆኑም በሂደት የተፈጠሩት የታሪክ፣ የሕገ መንግሥት፣ የባንዲራ፣ የመንግሥት ዓይነት አለመግባባቶች በሰከነ ምክክር ለመፍታት ሁሉም በቅንነት እንዲሳተፍ ጠይቀዋል።

እነዚህ ቅራኔዎችና አለመግባባቶች አገሪቱ በጦርነት፣ በመገዳደልና በመገፋፋት እንድታልፍ ማስገደዳቸውን ያወሱት ኡስታዝ አቡበከር፣ አሁን ላይ ይባስ ብለው አገር የማፍረስ ደረጃ የደረሱትን ችግሮች ለመቀልበስ ጠብመንጃ የያዘም ያልያዘም ሁሉ በቅንነት በውይይቱ ለመሳተፍ መነሳት ይጠበቅበታል ብለዋል።

ዛሬ የእድገትና የሥልጣኔ ቁንጮ ላይ የምትገኝ አሜሪካም ብትሆን በነጮችና በጥቁሮች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት በርካታ ዘግናኝ ታሪኮችን ያሳለፈች አገር ናት ያሉት ኡስታዝ አቡበከር ፣ ዳሩ ግን በፈጠሩት የጋራ መግባባት ጥቁር ጠባሳውን ቆርጠው በመጣል አዲስ ምዕራፍ በመክፈት ለዚህ ደረጃ መብቃታቸውን አንስተዋል።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ግን



“ከሚያራርቁን የሚያቀራርቡን ጉዳዮች ያመዝናሉ” ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፣ ሁሉም ተከብሮ የሚኖርባት ኢትዮጵያን ለመገንባት አገራዊ ምክክሩ የጋራ

ቃልኪዳናችን የምናድስበት ወርቃማ ክስተት መሆኑን አስገንዝበዋል።

ኡዝታስ አቡበከር እንዳሉት በጋራ አገር ውስጥ የተሳለጠ ልማት፣ የተሳካ አገረ መንግሥት ግንባታ፣ የሰከነ የፖለቲካ ባህልና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ማየት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለምክክሩ ስኬታማነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት አገራዊ ግዴታው ነው። ምክክሩ በራሱ የታሪክ አካል ሲሆን ለስኬቱ በመስራት አገርን ከአደጋ መታደግ ደግሞ ራስን በታሪክ መዝገብ ላይ በደማቅ ቀለም መጻፍ መሆኑን አመልክተዋል።

የኮሚሽነሮቹ ገለልተኝነትና ጥንካሬ በተመለከተ ኡስታዝ አቡበከር እንዳሉት፣ ቀድሞውኑ ኮሚሽነሮቹን በቅርበት እንደሚያውቋቸውና ወገንተኛ ያልሆኑና ኢትዮጵያዊነት ስሜት ተላብሰው ለአገር አንድነትና ለሕዝቦች እኩልነት ሲሟገቱ የቆዩ መሆናቸውን ተናግረዋል። ጠቃሚ ሃሳብ ከማቅረብ አኳያ ያላቸዉ ልምድና ብቃት ለምክክሩ ስኬታማነት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረውም ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

# በኦሮሚያና በሱማሌ ክልሎች ከድርቁ ተጨማሪ የአንበጣ ወረርሽኝ ሥጋት መሆኑ ተጠቆመ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በድርቅ ክፉኛ እየተጎዱ ያሉት የኦሮሚያና የሱማሌ ክልሎች የአንበጣ ወረርሽኝ ሌላው ሥጋታቸው መሆኑን አመለከቱ።

የኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ሃላፊ እና የሶማሌ ክልሎች አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ በሁለቱ ክልሎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከሰተው ድርቅ በአይነቱ ልዩ በመሆኑ በርካታ የቤት እንስሳት ሲገድል በርካታ ዜጎችን ለተረጂነት ዳርጓል። ሰሞኑን የዘነበው ዝናብ ተስፋ ሰጪ ቢሆንም ቀጣይነት ባለማሳየቱና ዝናቡንም ተከትሎ በአንዳንድ አካባቢዎች የአንበጣ መንጋ በመከሰቱ ችግሩ ተደራራቢና አሳሳቢ ሆኗል።

የኦሮሚያ ቡሳ ጎኖፋ ኃላፊ አቶ ሙስጠፋ ከድር እንደተናገሩት፣ በኦሮሚያ በስምንት ዞኖች ማለትም ቦረና፣ ሁለቱ ጉጂዎች ፣ በሁለቱ ባሌና በምስራቅ ሸዋ በጥቅሉ በ56 ወረዳዎች የተከሰተው ድርቅ 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሰዎችን ለተረጂነት ሲያዳርግ በሚሊዮች የሚቆጠሩ ከብቶችን ገድሏል።

ድርቁ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ በተለይም የሰው ሕይወት እንዳይቀጥፍ በመንግሥት መንግሥታዊ አካላት ሰፊ እርብርብ እየተደረገ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሙስጠፋ በድርቁ ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች እስካሁን 1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ እርዳታ መቅረቡን ተናግረዋል። ሆኖም ድርቁ ከፍተኛ በመሆኑና በተይም ሰሞኑን የጣለውን ዝናብ ተከትሎ የአንበጣ መንጋ በመከሰቱ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚደረግ ድጋፍ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል።

ሰሞኑን የጣለው ዝናብ በአንዳንድ አከባቢዎች ሳር እንዲበቅል ማድረጉና ቀጣይነት ካለውም ለእርሻ ሥራም ተሰፋ ሰጪ መሆኑን የተናገሩት ሃላፊው፣ ነገር ግን ባልተጠበቀ መልኩ በቦራ ተልተሌ አካባቢ የተከሰተው የአንበጣ መንጋ የበቀለውን ሳር የማውደም አቅሙ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በቀጣይ በሚደረገው የግብርና እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል አመልክተዋል።

እንደ አቶ ሙስጠፋ ማብራሪያ፣ ወትሮም ኬንያን፣ ሶማሊያንና ሌሎች ቆላማ አካባቢዎችን ተገን በማድረግ የአንበጣ ወረርሽኝ ይከሰታል። የአሁኑ ግን ከወዲሁ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ ከድርቁ ጋር ተደምሮ መዘዙ የከፋ ይሆናል። ለከብቶች መኖነት ሊሆን የሚችለው ሳርም በዚሁ የአንበጣ መንጋ ሊወድም እንደሚችል ያላቸውን ስጋት ጠቁመዋል።

የሶማሌ ክልል የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ምክትል ኮሚሽነር አብዱልፈታ መሐመድ በበኩላቸው በክልሉ ባሉ 11 ዞኖች ድርቅ መከሰቱን ጠቁመው፣ በድርቁ ምክንያት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ከብቶች ሲያልቁ ከ 3 ነጥብ 5 ሕዝብ በላይ ደግሞ ለአስቸኳይ እርዳታ ተዳርጓል ብለዋል።

በሶማሌ ክልል 50 ሚሊዮን የሚጠጋ የእንስሳት ሀብት እንዳለ የሚናገሩት አቶ አብዱልፈታ ምናልባት ቀጣዮቹ ሳምንታት ዝናብ ካልዘነበና በቂ የመኖ ድጋፍ ካልቀረበ ክልሉ ከፍተኛ የሆነ የእንስሳት ሀብቱን ሊያጣ እንደሚችል ያላቸውን ስጋት አጋርተዋል።

ከሁሉም በላይ የአንበጣ ወረርሽኝ አስከፊ በመሆኑ በቦረና የተከሰተው የአንበጣ መንጋ ለሶማሌ ክልል የሚተርፍ በመሆኑ ከወዲሁ የመከላከል ስራ ሊከናወን እንደሚገባ አሳስበዋል። አምና በክልሉ የተከሰተው የአንበጣ ወረርሽኝ እንቁላሉን በአካባቢዎቹ ጥሎ ስለነበርና እንቅላሎቹም እዚያ ስለሚቆዩ የመከሰት ዕድሉ ሰፊ በመሆኑ ከወዲሁ የመከላከል ስራ እንዲከናወን ጥሪ አቅርበዋል።

# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ...

ከ3ኛው ገጽ የዞረ

ግፍ የተረሸኑ ንጹሃንን አፅም አስወጥቷል።

በዚህ አሰቃቂ እስር ቤት የታሰሩ ንጹሃን በሚደርስባቸው ሰቆቃ ምክንያት ራሳቸውን ማጥፋታቸውን፣ የሕወሓት ታጣቂዎች በየቀኑ ታሳሪዎችን እየወሰዱ ይገድሉ እንደነበርና የብዙዎቹ አስከሬን በአካባቢው የሚገኝ ቃሌማ ወንዝ ላይ ይጣል እንደነበር ከሞት የተረፉት አዛውንቶች ለጥናት ቡድኑ ቃላቸውን ሰጥተዋል። እልፍ የአማራ ተወላጆች ባለቁበት በዚህ ‹የኢትዮጵያው አሽዊዝ› ሦስት አሰርታትን ለሚሻገሩ ዓመታት ዓለም ያላስተዋለው የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሟል።

የድብቅ እስር ቤቱ ውስጥ በበሽታና በርሃብ፣ በድብደባ ተሰቃይተው እንዲሁም በሕወሓት ታጣቂዎች ለሚገደሉት እስረኞች ቀብር ይቆፍሩ የነበሩት እስረኞች እንደነበሩም በጥናቱ መሰረተ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ ጥናት ባሻገር ዓለም የሚያውቀውና ድርጊቱን በሚገባው ልክ ባይሆንም ያወገዘው ጥቅምት 30/2013 በማይካድራ ከተማ በአማራ ተወላጆች ላይ የደረሰው ዘርን መሰረት ያደረገ ጭፍጨፋ በሕወሓት መሪነት የተፈፀመ ነበር። ጭፍጨፋው በትግራይ ልዩ ኃይልና ሚሊሻዎች እንዲሁም የሩዋንዳ ኢንተር ሃሞይ (Interahamw) ሞዴል የሆነው የሳምረ ኢ-መደበኛ ኃይል (Tigrians paramilitary Force) በሕወሓት መሪነት መፈፀሙ፣ በጭፍጨፋውም ከ1600 በላይ የአማራ ተወላጆች መሞታቸው አይዘነጋም።

በጥቅሉ ባለፉት ሠላሳ ዓመታት በሕወሓት መሪነት በአካባቢው የተፈፀሙ ዓለምአቀፍ ወንጀሎች፣ በዓለምአቀፍ መመዘኛዎች ደረጃ ስንመለከተው በወልቃይት ጠገዴ የአማራ ሕዝብ ላይ ዓለም ያልሰማው የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞበታል። ለዚህም ወንጀል ፈጻሚ የሕወሓት አመራሮች በዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ቀርበው ሊጠየቁ ይገባል።

የዓለምአቀፉ ማሕበረሰብ እና ተቋማት በእነዚህ አካባቢዎች ቅድመ እና ድሕረ ነጻነት ያለውን ሁኔታ የሚያዩበትን መንገድ በተለይም የመረጃ ምንጮቻቸውን ሊፈትሹ ይገባል። አምነስቲ ኢንተርናሽናልና ሂውማንት ራይትስ ዎች በተደጋጋሚ ሪፖርቶቻቸው ሰብአዊነትን ሳይሆን ፖለቲካዊ ወገንተኝነታቸውን አሳይተዋል። ይህ የፖለቲካ ወገንተኝነታቸው የሰብዓዊ መብት ጠለፋ (hijacking human rights) በሚል የሚያስተቻቸው ከመሆኑም በላይ በአንዲት ሉዓላዊት አገር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት የተፈረጀን ድርጅት (የሕወሓትን) የፖለቲካ አቋም በሚጋራና የወልቃይት ጠገዴ የእማራ ሕዝብን የዘመናት በደል በሚክድ ሁኔታ በሪፖርታቸው ወገንተኛ ሆነው መገኘታቸው የቆሙለትን ዓላማ እንደካዱ ይቆጠራል። ይህን አሳዛኝ ሁነት የሚያከፋው ደግሞ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ በይፋዊ ገጹ ሪፖርቱን መጋራቱና የተጠያቂነት ጣቱን ተበዳይ ወደሆነው የአማራ ክልላዊ መንግሥት ማዞሩ እጅግ አሳዝኖናል።

ተለዋዋጭ ፖለቲካ አይነተኛ ባህሪው በሆነው የምስራቅ አፍሪካ ፖለቲካ ውስጥ ‹ዓለምአቀፍ ድንበሮች አይገድቡኝም› በሚል ጎረቤት አገራትን ጭምር ለማተራመስ የሚሰራውን አሸባሪውን ሕወሓት የሚደግፍ የትኛውም ዓይነት አቋም መያዝ እንደ ክልልም ሆነ እንደ አገር የተያዘውን የሰላምና መረጋጋት ጉዞ የሚያደናቅፍ ሆኖ አግኝተነዋል። ኤምባሲው በክልላችንም ሆነ በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ የሚያይበትን መንገድ በተለይም የመረጃ ምንጮቹን ደግሞ ደጋግሞ እንዲፈትሽ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ዓለምአቀፉ ማሕበረሰብ የአማራን ሕዝብ በተመለከተ ሊረዳው የሚገባ እውነት የአማራ ሕዝብ ከመላ የኢትዮጵያ ብሔር ብሄረሰቦች ጋር እኩልነትን መርሁ አድርጎ በወንድማማችነት ስሜት፣ በሠላምና በፍቅር ከመኖር ውጭ የተለየ ፍላጎት የለውም።

በጥቅሉ በነዚህ እና የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት እየመረመራቸው በሚገኙ ሌሎች የሪፖርቱ አካል የሆኑና ለክልሉ ሕዝብ ሰላም መስፈንም ሆነ የሰብአዊ መብቶች መከበር የማይበጁ ስሁት ሀሳብና ብያኔዎች ምክንያት በሂዩማን ራይትስ ዎች እና በአምነስቲ ኢንተርናሽናል የተዘጋጀውን የጋራ ሪፖርትን አንቀበለውም ሲል ሃሳቡን አጠቃሏል።

# የሕዝብ ጥያቄዎችን በየደረጃው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በርካታ ስራዎች በክልሉ ሰላም መስፈኑንና አበረታች የልማት ስራዎች መሰራታቸውን አውስተዋል።

በሌላ በኩል ከሕግ የበላይነት፣ የጎሳ ግጭት፣ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች፣ መልካም አስተዳደር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም ከመሬት ወረራ ጋር የተያያዙ በርካታ ቅሬታዎች ቀርበዋል ብለዋል።

በዚህ መሰረትም ከማሕበረሰቡ የተነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች በተገቢው መልኩ በመቀመር ደረጃ በደረጃ እንደሚፈቱና ለዚህም ዝርዝር እቅዶች ተዘጋጅተው ወደ ተግባር ለመግባት ዝግጅት መጠናቀቁን ተናግረዋል።

በዋናነትም ከሕግ የበላይነት ጋር በተያያዘ ማስተካከያ ሊደረግባቸው የሚገቡ አሰራሮች እንዲስተካከሉ፤ በዚህ ረገድ መፈተሽ የሚገባቸው አሰራሮችና ሕጎች በመኖራቸው ማስተካከያ እንዲደረግባቸውአቅጣጫ ተቀምጧል ብለዋል።

ከሙስና እና ብልሹ አሰራር ጋር በተያያዘ በክልሉ ውስጥ ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚረዱ ተቋማትን በማጠናከርና ኃላፊነታቸውን በተገቢው እንዲወጡ እገዛ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ተቋማቱን የማጠናከር ስራ እንደሚሰራ አቶ ሙሰጠፌ ተናግረዋል። ከመሬት ወረራና ተያያዥ የሕግ ጥሰቶች ጋር በተያያዝም አጥፊዎችን ወደ ሕግ የማቅረብ ስራ እንደሚከናወን አስታውቀዋል።

ድርቁ በሰዎች ሕይወት ላይ የከፋ ጉዳት ሳያደርስ ለመቆጣጠር የተደረገው ጥረት አበረታች መሆኑን የተናገሩት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ፣ አሁንም የዝናቡ ሁኔታ አጠራጣሪ በመሆኑና ችግሩም በዛው ልክ እየሰፋ በመሄዱ ምክንያት በቀጣይ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል ብለዋል።

ድርቁ በተደጋጋሚ ማሕበረሰቡን እንዳይጎዳ በአጭር፣ በመካከለኛና በረዥም ጊዜ ችግሩን መፍታት እንደሚያስፈልግ ገልፀው፣ ለዚህም ተግባራዊነት በዋናነት በውሃ ሀብት፣ እርሻና እንስሳት ሀብት ላይ ያተኮረ የልማት እስትራቴጂዎች መከተል እንደሚገባ አስምረውበታል።

ለዚህ ተግባራዊነት ለዘርፉ ከቀድሞው የተሻለ በጀት በመመደብ ማሕበረሰቡ በድርቁ በተደጋጋሚ እንዳይጎዳ ምርትና ምርታማነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ እንደሆነና ይህንኑ ለማረጋገጥም የመስኖ ስራዎች በስፋት በመሰራት ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።

የክልሉ ማሕበረሰብ በየጊዜው ለሚያነሳው ጥያቄ ገዢው ፓርቲ ትኩረት ሰጥቶ የተለያዩ ስራዎችን ሲያከናውን እንደቆየና በቀጣይም በተዘጋጀው ዕቅድ መሰረት የሕዝቡን ጥያቄዎች ለመፍታት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን አቶ ሙስጠፌ ተናግረዋል።

# ‹‹ስብሄራዊ መግባባት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይወሰዳሉ። እስካሁን ይካሄዱ እንደነበሩ ውይይቶች የበላይ አካል ቀርጾ በሚያቀርበው አጀንዳ ሳይወሰን ሕብረተሰቡ በግልጽ በመወያየት ወደ ብሄራዊ መግባባት ለመድረስ መሳተፍ አለበት። አካታች መሆን ስላለበት በሂደት ወደክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ይሄዳል።

እየተነጋገርን ያለባቸው ጉዳዩቹ ምናልባት የ30፣ የ40፣ የ50፣ የ100 እና የ500 ዓመታትም ሊሆኑ ይችላሉ። ነገሮች ደረጃ በደረጃ ከተሟሉ ምክክር ኮሚሽኑ በሶስት ዓመታት ባይሳካለት እንኳን ለቀጣዩ ጊዜያት መደላድል ይፈጥራል ብዬ አስባለሁ ብለዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ኮሚሽኑ ተቋቁሞ ቃለ መሃላ ፈጽሞ ስራ ከጀመረ ዛሬ አንድ ወር ከ18 ቀናት ሆኖታል። በዚህ ሂደት ጽህፈት ቤት ማቋቋምና ማደራጀት፣ አዋጁን ሁሉም ኮሚሽነሮች አጥንተው እያንዳንዱን የስራ ተግባር መርምረውና ተረድተው ሃላፊነታቸውን እንዲቀበሉ ተደርጓል።

ኮሚሽነሮች ስራዎችን ተከፋፍለው ደንብ በማርቀቅና በውስጥ መመሪያ ማዘጋጀት ስራ ላይ ናቸው።

አገር አቀፍ ውይይቱ አካታች እንደመሆኑ ሕብረተሰቡ የውይይት ጽንሰ ሃሳብ ባግባቡ እንዲገነዘብና በተገቢው መልኩ መብቱን እንዲጠቀም የብዙሃን መገናኛና የኮሙኒኬሽን ፖሊሲና ስትራቴጂ እየተሰራ መሆኑንም አመልክተዋል።

የሶስት ዓመታት የስራ ዕቅድና መርሃ ግብር እየተሰራ ይገኛል። በተለያዩ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተሰሩና የተጻፉ ጽሁፎችን በማሰባሰብ፣ አብረው ሊሰሩ ከሚችሉ ተቋማት ጋር እንደአስፈላጊነቱ እየተዋቀወቅን እንገኛለን ብለዋል።

‹‹አንዳንድ የውጭ ተቋማት ምን ይዘው እንደሚመጡ ስለማናውቅ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት አልጀመርንም። የራሳችንን የቤት ስራ እስከምናጠናቅቅ ግንኙነት አይኖርም። አገራዊ ውይይቱም በኢትዮጵያውያን መሳካት አለበት ብለን እናምናለን›› ነው ያሉት።

‹‹ኮሚሽነሮቹ 11 እንደመሆናችን ሁላችንም እየወጣን ብንናገር ብዥታ እንዳይፈጠር በጥንቃቄ እየሰራን ነው። ሕዝቡ የምናደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች አልፎ አልፎ ማወቅ ስላለበት መረጃ የምሰጠው እኔ ብቻ ነኝ በቅርቡ ቃል አቀባይ ይኖረናል›› ብለዋል ፕፌሰር መስፍን።

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ገለጻ ውይይት ካካሄዱ ከ100 በላይ አገራት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው በተሻለ መልኩ አጀንዳቸውን ቀርጸው ሲወያዩ፣ አንዳንዶች አጀንዳ ቀርጸውም የውጭ ጣልቃ ገብነት አጋጥሟቸዋል። የየመን ውይይት ጥሩ ቢሆንም የውጭ ጣልቃ ገብነት ስለነበረበት ብዙ አልዘለቀም።

መንግሥታዊ ሥልጣንን ስለመከፋፋል ዋና አጀንዳቸው አድርገው የተወያዩም ነበሩ፤ እንደ ደቡብ አፍሪካ አይነቶች የእውነትና የእርቅ አፈላላጊ ተቋማት ድርድርን አብረው አዋህደው አካሂደዋል። አብዛኛዎቹ ውጤታማ ያልሆኑት የውጭ እጅ ስለነበረባቸው ነው። ይሄ ለእኛ ትልቅ ትምህርት ይሆናል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ 50 የፖለቲካ ድርጅቶች በአገር ውስጥ ያለው አጀንዳ የእነርሱም እንደመሆኑ በቅንነትና በትህትና ከገቡ የተዋጣ ውይይት ይሆናል። ካልሆነ ግን እንደተግዳሮት ሊቆጠር ይችላል።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያን ጠንካራ ሆኖ መውጣት የሚመኙ በርካታ ወዳጅ አገራት ቢኖሩም፤ በአንጻሩ የእኛን አለመረጋጋት የማይጠሉ ይኖራሉ ብዬ ስለማስብ በተወሰነ ደረጃም የውጭ ጣልቃ ገብነት ሊኖር ይችላል ሲሉ ስጋታቸውንም ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፓርላማ አባላት የአስፈጻሚ ተቋማትን የመሞገት ጅማሮ ተጠናክሮ ይቀጥል!

በሀገራችን የዴሞክራሲ ስርዓትን የመገንባት ጉዳይ የውዴታ ሳይሆን የግዴታ ጭምር ነው። የትኛውም ዓለም በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ ዘርፎች የቱንም ያህል ዕድገት ቢያስመዘግቡ ሁሉም ሰው ባለው ነገር እኩል ረክቶና ተደስቶ አይኖርም። ምንም ይሁን ምን ዴሞክራሲን ይናፍቃል። ነፃነትንና እኩልነትንም ይሻል! ስለዚህ ዴሞክራሲ ስጦታ ብቻ ሳይሆን ለአንድ የሰለጠነ ሀገርና ህዝብ አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ ነው። ለዚህም ነው ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ መስዋዕትነት የሚከፈለው፤ ሕይወትም የሚገበረው።

በሀገራችንም የዴሞክራሲ ስርዓት ለመተግበር በየስርዓቱ መሻቱ አለ ፤የሚፈለገውን ያህል አይሁን እንጂ ሙከራዎችም ይታያሉ። በተለይ ባለፉት አራት ዓመታት ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ሕዝብ የሚፈልገውን መንግሥት በነጻነት መምረጥ እንዲችል ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። ነጻ የዴሞክራሲ ተቋማት ተገንብተዋል፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ማለት በሚያስደፍር መልኩም ህዝቡ ይወክለኛል፣መብትና ጥቅሜን ያስከብርልኛል ያለውን የሚፈልገውን መንግሥት በካርዱ መርጧል። ድምጹን በየአደባባዩና መድረኩ ያለ ተጽዕኖ መግለጽ ችሏል ። ያልተስማማበትን ሀሳብ በመቃወም የሚስማማበትን ደግሞ በመደገፍ ሀሳቡን ማንሸራሸር ቀጥሏል። ይሄ በሀገራችን የዴሞክራሲ ጭላንጭል ያሳየ ክስተት ነው። በቂ ነው ማለት ግን አይደለም፤ ገና ብዙ ሊሰሩ የሚገቡ ከሕዝብም ሆነ ከመንግሥት፤ ከተፎካካሪ ፓርቲዎችም ሆነ ከሃይማኖት ተቋማት የሚቀሩ ሥራዎች አሉ። ስልጡን በሆነ መልኩ ሀሳብ መግለጽ፣ መደማመጥ ፣ ከትናንት ተምሮ ስህተትን ማረም ገና ይቀረናል። እስካሁን የመጣንበት የእውቀት ክፍተት ፣ ጠፍንጎ የያዘን የፍርሀትና የጭቆና ቀንበር እንዲሁም ባህል ዴሞክራሲን በቅጡ እንዳንለማመደው አስሮናል። ሆኖም ይሄ «ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል» እንደሚባለው ሁሉ ቀስ በቀስ ከእስሩ መፈታቱ የማይቀር ነው ።

አሁን በየመድረኩ የሚታዩት አዲስ ባህሎች ይህንን አመላካች ናቸው። በቅርቡ ለነዋሪዎች በተዘጋጁ መድረኮች ነዋሪዎች የተሰማቸውን ቅሬታ ፣ መንግሥትና ሕዝብ ሊያውቀው ይገባል ያሉትን ነገር ሁሉ ያለ ከልካይ አቅርበዋል፤ያለ ገደብ ተናግረዋል። ይሄ ይበል የሚያሰኝ ጅምር ነው ።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በምክር ቤቱ ሪፖርት የሚያቀርቡላቸውን አስፈጻሚ ተቋማት ሪፖርት አድምጠው ብቻ አላቆሙም። በቀረበላቸው ሪፖርት በመነሳት፣ ከሕዝቡ የሚነሱ ቅሬታዎችን እንዲሁም አከራካሪና አወዛጋቢ የሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት ማብራሪያ እንዲያገኙ ጭምር የሥራ ኃላፊዎችን ሲያፋጥጡ ዓይተናል። ይሄ በጣም ትክክለኛና መሆን ያለበትም ነው። የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ለተቀመጠበት ወንበር የሚመጥን ተገቢውን ኃላፊነትን የሚመጥን ሥራ መስራት አለባቸው። ችግሮችን በወቅቱ መፍታትም ግዴታ ነው። የሕዝብን ቅሬታ ማድመጥና ተገቢ ምላሽ መስጠትም እንዲሁ። ከመሸንገያ ቃላቶች ወጥቶ በተግባር ችግሮችን መፍታት ይጠበቃል። ህዝቡንም የመፍትሄ አካል አድርጎ ማሳተፍም የግድ ነው።

ሰሞኑን በተወካዮች ምክር ቤት የታዘብነው ከዚህ ቀደም በነበሩት አምስት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች ከምናውቀው የተለየና ሪፖርት ቀርቦ አቆለጳጵሶና አሽሞንሙኖ ፤ ተሞጋግሶና ተመሰጋግኖ እንደመለያየት የቀለለ አልነበረም ። ይልቁኑ እያንዳንዱ ጉዳይ «የነብር ዓይን አየኹ» ዓይነት ክትትል እንዳለበት ያመላከተ እንጂ። የምክር ቤቱ አባላት ይህን ብናገር ፣ ይሄን ብጠይቅ ነገ ምን ይከተለኝ ይሆን ከሚል ቆፈን ወጣ ብለው ታይተዋል። የተሰማቸውንና ለሀገር ይጠቅማል የሕዝብን ችግር ይፈታል ፣ ህዝብና መንግሥት ሊያውቁት ይገባል ያሉትን ሀሳብ በሚገባ ማቅረብ ጀምረዋል። ሕዝቡም ይወክለኛል ብሎ ከመረጠው የምክር ቤት አባል የሚጠብቀው ድምጹን እንዲያሰማለት ነውና ይሄ ተገቢና ተጠናክሮ ሊቀጠል የሚገባ አዲስ ባህል ነው።

ይሁን እንጂ ይሄ ብቻውን በቂ አይደለም። አንድ የመንግሥት ተቋም የሥራ ኃላፊ ሥራውን ሊያሰራው ያላስቻለውንና ኃላፊነቱን ለመወጣት እንቅፋት የሆኑበትን ችግሮች በቅርበት ማየትና መከታተልም ያስፈልጋል። ከበጀት ፣ ከመመሪያና አሰራር ጋር ተያይዞ ያሉ ተግዳሮቶችን መፍታት ይገባል። ኃላፊነትን መወጣት ከአቅም ማነስ ነው? ወይስ ሌላ መሰናክል አለ የሚለውን መገምገም ይገባል። ስለዚህ የምክር ቤቱ አባላት የተቋማትን ስህተቶች እና ድክመቶች ምንጥር አድርጎ ከማውጣትና ኃላፊዎችን በአደባባይ ከመሞገት ጎን ለጎን ያሉባቸውን ችግሮች የመመርመር ፣ የመደገፍና የመከታተል ሥራ አብሮ ሊሰሩ ይገባል።

ዛሬ ሀገር የእከሌና የእከሊት አይደለችም። የሚፈለገው ወሬ፣ ተረትና ቧልት አይደለም። ድህነቱ አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል ። የኑሮ ውድነቱ ተባብሷል ፣ ሰው ሰራሹና የተፈጥሮ አደጋው አይሏል። ስለዚህ መተሳሰብ ፣ መተባበር ፣በእውቀት ላይ ተመስርቶ በቅንነትና በትጋት ሀገርና ህዝብን ማገልገል ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የሁሉንም ትጋት ይጠይቃል። አሁን በፓርላማ የተጀመረው አስፈፃሚ አካላትን የመሞገት አዲስ ባህል ይሄን ከዳር ለማድረስ የሚያግዝ ጅምር ነውና ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ጅብ ከሚበላህ በልተኸው ተቀደስ

**በአብዲ ወዬሳ**

ዊኒስተን ቸርቺል እንደሚሉት፤ የማይቀየር ወዳጅም ሆነ የማይቀየር ጠላት የሚባል ነገር የለም፤ ምን ጊዜም የማይቀየረው የሰው ፍላጎት ብቻ ነው። ይሄንን ብሂል ብዙ ሰዎች ሲደጋግሙት እንሰማለን። ኮምጣጣው ያገሬ ሰው ግን ይህን አይቀበለውም፤ ይልቁንም፡-

**"ጠላትማ ምጊዜም ጠላት ነው**

**አስቀድሞ መግደል አሾክሻኪውን ነው፤"** ይላል።

ዝም ብዬ ሳስብ በአንድ በኩል የሀገሬ ሰው ያለው ትክክል ነው። የማይላቀቁ ጠላቶች አሉ። የታሪክ ጸሐፊዎቿ እንደሚያጫውቱን ሀገራችን በታሪኳ ብዙ የውጭ ጠላቶችን እንደአመጣጣቸው አስተናግዳለች። በመጡበት እግራቸው የተመለሱም ተመለሱ፤ የተረፉትንም ያለፈውን ቂም ትተን "ይቅር ለእግዚአብሔር" ተባብለን ከነዚሁ ጋር በሰላምና በፍቅር እየኖርን ነው። ሆኖም አንደ አልቅት ተጣብቃን የማትላቀቀው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ባላንጣ የሆነችብን ግብጽ ነች። የአገሬን ሰው ብሂል እውነት ያስባለች የማትቀየር ባላንጣ ነች። ዓባይን ለዝንተ ዘመን ያለ ተቀናቃኝ የግሏ አድርጋ ስለኖረች አሁንም ለሚመጡት ዝንት ዓለሞች ያለ ተጋሪ የግሏ ሆኖ እንዲቀጥል ያላት ፍላጎት ቀጣይ ነው። በስስት ለምትመለከተው ዓባይ ተቀናቃኜ ነች የምትለው ኢትዮጵያን ነው፡፡

በኢትዮጵያ ላይ ዓይኗን ካደፈረሰች፣ ጥርሷን ከነከሰች ብዙ ዘመን ሆኗታል። ኢትዮጵያን ለማሽመድመድ ቢቻል ለማጥፋት በሚገርም ትጋት ለዘመናት ሣታቋርጥ እየሠራች ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ ግብጽን ላጥፋት ብላ ኢትዮጵያ አቅዳ አታውቅም። ግብጽ ግን ግልጽና ስውር ደባ በኢትዮጵያ ላይ ትሠራለች። የሚገርመኝ ደግሞ ግብጽ የራሷን ብልሀትና ጉልበት ብቻ ሳይሆን ኃያላን መንግሥታትን በማስተባበርና ተገኗ ማድረግን ተክናበታለች። የምትመጣብን እንደ የአውሮፓንና አሜሪካን ያሉ ኃያላንን አስተባብራ የሙጥኝ ብላ ይዛ ነው። የአሜሪካና የአውሮፓ በተለይም ዘረኛ ነጮች ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ በሚሸረብ የግብጽ የጥፋት ዕቅድ ላይ ለመተባበር አያቅማሙም። እኛ ግን በአብዛኛው ማንም ተገን ሳይኖረን የምንጋፈጠው ብቻችንን ነው፡፡

ለምሳሌ፣ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1863 የግብጽን በትረ-መንግሥት የተቆጣጠረው ከዲቭ እስማኤል ያባይን ሸለቆ እንዲሁም ከተመቸም ዘልቆ ገብቶ ቀሪውን የኢትዮጵያን ክፍል ለመቆጣጠር ተመኝቶ ከፍተኛ የጦር ዝግጅት ሲያደርግ የገንዘብም ሆነ የሞራል ድጋፍ ያደረጉት አውሮፓውያን ነበሩ። እርሱም በኢትዮጵያ ላይ የሚዘምተውን የግብጽን ጦር እንዲመሩለት ያሰባሰበው የጦር አዛዦችና ባለሙያዎች ከአሜሪካ፣ ከዴንማርክ፣ ከሲዊይዘርላንድ፣ ከቱርክ የተውጣጡ የደነደነ የጦር ስልት አዋቂዎችን ነበር። ጦሩን እንዲመሩ ሙሉ ኃላፊነት ለቅጥረኛ አሜሪካውያንና አውሮፓውያን ሰጥቶ የግብጽን ሠራዊት በዘመናዊ መሳሪያ አስታጥቆ ወደ ኢትዮጵያ ሲሸኝ ድል በጁ እንደምትገባ ሙሉ እምነት ነበረው። አለንልህ አይዞህ በርታ!! ከማለትም አልፈው ለጦርነቱ የሚውል ገንዘብ ያበደሩት የአውሮፓ መንግሥታት በተለይም የእንግሊዝና የፈረንሳይን ባለሀብቶችም ጦርነቱ በከዲቭ እስማኤል ድል አድራጊነት እንደሚጠናቀቅ አልተጠራጠሩም።

እንደተመኙትና እንደተገመተው ሳይሆን ቀርቶ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት በአጼ ዮሐንስና በአሉላ አባነጋ እየተመራ ቴክኖሎጂውንና ስልጠናውን የተማመነውን የግብጽን ጦር ከነፈረንጅ መሪዎቹ በጉንደት (እ.አ.አ 1875) እንዲሁም በጉራዕ (እ.አ.አ 1876) በተደረጉት በሁለት ተከታታይ የጦር አውድማዎች ሁሉ ሽንፈትን አቀመሷቸው። አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጂራ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በሚለው መጽሐፋቸው የጦርነቱን ውጤት ሲገልጹ፤ "አጼ ዮሐንስም ሠራዊቱን አስከትቶ ከምስር ታዞ የመጣውን ቱርክ እንደ ካንቻ መታው፤... እየደጋገመ ሁለት ጊዜ ወቃው" ይላሉ። አብዛኛው የግብጽ ጦርና አሜሪካውያንና አውሮፓውያን መሪዎቻቸው ጭምር እዚሁ ጥሪኝ አፈር ሆነው ቀሩ። ቅስሟ ተሰበረ፡፡

በነዚህ ጦርነቶች በደረሰባት ሽንፈት ግብጽ አፍራ የጤፍ ፍሬ አከለች። የአውሮፓ አይዞሽ ባዮች ሁሉ ተበሳጩ። በዚሁም የተነሳ 1879 ከዲቭ እስማኤልን ከስልጣን እንዲለቅ አድርገው ተውፊቅ ፓሻን አስቀመጡ። የነዚህ ጦርነቶች ዳፋ በግብጽ ውስጥ ከፍተኛ ትርምስን ቀሰቀሰ። በጦርነቱ ምክንያት ከተከሰተው የኢኮኖሚው ቀውስ በተጨማሪ "ጦርነቱን የተሸነፍነው በአመራር ድክመት ነው" በሚል ቁጭት የተቀጣጠለው ወታደራዊ አመጽ የተውፊቅን መንግሥት አሽቀንጥሮ ለመጣል ሲወዘውዘው አይታ ጥቅሟን ለማስጠበቅ ስትል እንግሊዝ ጦሯን ይዛ ገስግሳ ግብጽ ገባች። በቀላሉም አልተመለሰችም። በዚያው ግብጽም በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ቀንበር የመጠመድ ሂደት ተጀመረ። "ኢትዮጵያን የነካ የለውም በረካ" ይሏል ይሄ ነው፡፡

በአንጻሩ ኢትዮጵያ በድል ላይ ድል እየጨመረች በ1896 በአድዋ የጦር አውድማ በጣሊያን ወራሪዎች ላይ በአጼ ምኒልክ መሪነት ድሏን ደገመች። በቅኝ አገዛዝ ዘመን የነጻነት ባንዲራዋን እያውለበለበች ብቸኛዋ በአፍሪካ አሁጉር ነጻ ሀገር፤ ለጥቁር ህዝብ አብሪ ኮከብ ሆና ቀጠለች። ይመስገን!!

ግብጽን ከ1882-1922 በቅኝ ግዛት ስርአት እንግሊዞች ቀጥቅጠው ገዟት። በነዚሁ ዓመታት ውስጥ እነርሱም ቢሆኑ አይናቸውን ከኢትዮጵያ ላይ አላነሳ አሉ። እንግሊዞች የዓባይን ተፋሰስ ቦጭቀው ከኢትዮጵያ ወስደው ከቅኝ ግዛታቸው ጋር መቀላቀል ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነበር። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1906 ከፈረንሳይና ከጣሊያን ጋር ኢትዮጵያን ለሶስት ለመቀራመት ተግባቡ። በስምምነቱም ከአዲስ አበባ -ጂቡቲ የባቡር መስመር አኳያ ለፈረንሳይ እንዲሰጥ፤ በዓባይ አቅጣጫ ለራሷ ለእንግሊዝ እንዲሰጥ፤ የቀረውን የኢትዮጵያ ክፍል ደግሞ ለጣሊያን ከኤርትራና ከሱማሌ የቅኝ ግዛቶቿ ጋር ቀላቅላ እንድትገዛ ተስማሙ። ይሄንንም ስምምነት ምኒልክ እንዳይሰሙ ምስጢራዊነቱ እንደተጠበቀ እንዲቆይ ተግባቡ። የሚያስቀው አላማችን "የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት መጠበቅ ነው" የሚል ሽፋን ማልበሳቸው ነበር፡፡

የዚህ ስምምነት ሠነድ ዋና አዘጋጅ የነበረው ሎርድ ሀሪንግተን ለአለቃው ለእንግሊዙ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ የጻፈው ሪፖርት እውነተኛ ፍላጎታቸውን አጋልጧል። የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ማስጠበቅ ሳይሆን ፈራሚ ኃያላን መንግሥታት በጥቁሮች ላይ የሚከተሉት ፖሊሲ የነጮችን ፍላጎት ያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ ነው ብሏል። አፈር ይቅለላቸውና፤ ታዋቂው የታሪክ ጸሐፊ የነበሩት ሪቻርድ ፓንክረስት እንዳስቀመጡት "...his main object was to ensure that the three powers followed a policy in the interests of whites against blacks..." (Richard Pankhurst, Mederek, 1993.)። ይህ መሠሪ ተንኮላቸው አልተሳካላቸውም እንጂ ተሳክቶላቸው ነገሩ ቢፈጸም ምኒልክ የሶስቱን ኃያላን ጦር አሸንፈው የኢትዮጵያን አንድነት ማስጠበቅ ይችሉ ነበር?! ለማንኛውም አልተሳካላቸውም! ኢትዮጵያም ተረፈች!

በ1922 እንግሊዞች ለግብጽ ነጻነትዋን ሰጧት። ዓባይን ያለተቀናቃኝ ለመቆጣጠር ግብጽ ከፈለገች ኢትዮጵያን ማድከም ከተቻለም መበታተን ብቸኛ መፍትሄ መሆኑን እንግሊዞች እጇን ይዘው አስተምረዋት የወጡ ይመስላል። ምክንያቱም ቀደም ሲል ትከተል

ጅብ ከሚበላህ . . .ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ሲሰራበት የሚገባው አገራዊ ምርት የመጠቀም ባህል

**ተገኝ ብሩ**

ኢኮኖሚ ከሚደገፍባቸው ዋንኛ ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው፤ የፋሽን ኢንዱስትሪው ዘርፍ። በዓለም ገበያ ከፍተኛ የማዋዕለ ንዋይ ዝውውር የሚደረግበትና ገበያና ገበያተኛው በቋሚነት የሚገናኙበት፣ ትርፍና ትርፋማነት ከፍተኛ ዕድገት የሚስተዋልበት፣ ተጠናክረው ከሰሩበትና ከፍተኛ ውጤት የሚገኝበት ዘርፍ ነው። ለዚህም ነው አገራት አገር በቀል የሆኑ የፋሽን ምርቶች ላይ በስፋት በመስራት ከራሳቸው አልፈው ወደሌሎች አገራት በመላክ ተጠቃሚነታቸው ለመጠቀም ብርቱ ጥረት የሚያደርጉት።

አገራዊ ምርት መጠቀም ጥቅሙ አያሌ ነው። አገራት ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ አውጥተው ወደ አገር የሚያስገብዋቸው የፋሽን ኢንዱስትሪ ምርቶች በአገር ምርት መተካት ቢችሉ ተጠቃሚነታቸው ከፍተኛ እንደሚሆን አያጠያይቅም። በውጭ አገር የሚመረቱ አልባሳትና ሌሎች የፋሽን ኢንዱስትሪ ግብዓቶች በአገር ውስጥ ምርት መተካት ቢቻል የውጭ ምንዛሪ ወጪን ከመቀነሱም ባሻገር ከፍተኛ የሆነ የሥራ እድል መፍጠርና የፋሽን ኢንዱስትሪውን ዘርፍ ማነቃቃት ያስችላል፡፡

አገራት በራሳቸው የሚመረቱ አገር በቀል ምርቶች በህዝባቸው ተመርጦ ይለበስ ዘንድ ያበረታታሉ ለዚህም ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። እንድ ህንድ፣ ፓኪስታንና፣ ቻይና ለዚህ ዋንኛ ተምሳሌት ናቸው፡፡እነዚህ አገራት ማህበረሰባቸውን አገራዊ ምርትና አገልግሎት እንዲጠቀም በማድረግ ያላግባብ ይወጣ የነበረው የውጭ ምንዛሪ ከማዳናቸውና ኢኮኖሚያቸውን ከመደገፍ ባለፈ ለዜጎቻቸው ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር ችለዋል። በተጨማሪም አገራዊ ባህላቸው የተንፀባረቀበት ምርት ማሳደግ ችለዋል። በዚህም ዘርፈ ብዙ የሆነውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ ችለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በአገር ምርት የመጠቀም ባህል ካላቸው መሰል አገራት ልምድና ተሞክሮን በመተግበር አገራዊ ምርቷን በማሳደግና ከውጭ የሚመጣውን የፋሽን ኢንዱስትሪ ግብዓቶች መቀነስ እና አገራዊ የፋሽን ምርቶች መጠቀም ላይ ትኩረት አድርጋ መስራት እንደሚጠበቅባት የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። ዲዛይነር ሜላት እዚህ ላይ



አስተያየትዋን ትሰጣለች፤ ለፋሽን ኢንዱስትሪው ዕድገት አገራዊ ምርት የመጠቀም ባህል ላይ ተጠናክሮ መሰራት የሚኖርበት መሆኑን ትገልፃለች፡፡

ማህበረሰቡ ለአገራዊ ምርቶች የተሻለ አመለካከትና ፍላጎት ካለው አምራቹ አዳዲስና የተሻሉ ዲዛይኖችን ከጥራት ጋር የማቅረብ እድል ይፈጠርለታል። በዚህም ተጠቃሚውም አምራቹም ብሎም አገር ይጠቀማሉ። በአልባሳት ረገድ ኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው ከውጭ የሚመጡ ልብሶች እንደሚዘወተር የምትጠቅሰው ሜላት ይህ ደግሞ የውጭ ምንዛሪ በማስወጣት አገራዊ ጥቅምን ይቀንሳል።

ከውጭ የሚገባው የፋሽን ምርት መቀነስ ይባክን የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ከማዳን ባሻገር አገር በቀል የፋሽን ኢንዱስትሪዎች ለማነቃቃት አይነተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ከዚህ ባለፈው ባህል ተኮር የሆኑ አልባሳት በስፋት ተሰርተው ገበያ ላይ እንዲገኙ ትልቅ ዕድል ይፈጥራል። የሚሰራውና የሚያመርተው ባህሉንና ወጉን የሚያውቅ እንደመሆኑ ስሪቱም ባህል ነክ የመሆን እድል ይፈጥርለታል።

አገራዊ ምርት የመጠቀም ባህል ፋይዳው እጅግ ብዙ ነውና እዚህ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንዳለበትና ምርቶቹን ማበረታታት እንደሚገባ ባሙያዎች ይገልፃሉ። ዲዛይነር ሄለን አየለ በፋሽን ኢንዱስትሪው ገብታ መስራት ከጀመረች ከ3 ዓመት በላይ ይሆናታል። እንደ ዲዛይነርዋ ዋንኛ ትኩረትዋ አገራዊ ምርቶችን በአገር ውስጥ ተሰርቶ በሚቀርቡ ጨርቆች ሰርቶ ወደ ገበያ ማቅረብ ቢሆንም ማህበረሰቡ ከባህላዊ አልባሳት ውጪ ያሉ አልባሳት በአገር ውስጥ ከሚዘጋጀው ይልቅ ከውጭ የሚመጣውን ይመርጣል፡፡

ዲዛይነር ሄለን፤የማህበረሰቡ ምርጫ የውጭ የሆነበት ዋንኛ ምክንያት ያገር ውስጡ ጥራት የለውም ብሎ በመደምደሙ መሆኑን ትናገራለች። ነገር ግን በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ከውጭ ከሚገቡት በተሻለ መልኩ ጥራትና ያማረ ዲዛይን ቢቀርቡም ማህበረሰቡ እምነቱ ላይ ጠንካራ ሥራ አለመሰራቱ ምርጫው የውጭ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የክሬቲቭ ሃብ የኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ አቶ ተመስገን ፍስሀ አገር በቀል የሆኑ የፋሽን ኢንዱስትሪዎች ለማበረታታት አገራዊ ምርት የማሳደግ ሥራን መስራትና ህብረተሰቡ በአገር ውስጥ ምርት እንዲጠቀም መገፋፋት ወሳኝ መሆኑን ያስረዳሉ። በተለይ የአገር ውስጥ አዳዲስ የዲዛይን ፈጠራዎች በፋሽን ዲዛይነሮች ኢንዲመነጭና የፈጠራ ክህሎታቸው እንዲያድግ ለማድረግ እዚሁ የተመረቱ ምርቶች ማህበረሰቡ መጠቀሙ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

የአገር ውስጥ ምርት የመጠቀም ልማድ ቢጠነክር በአልባሳቱ ባህል እራስን ከማንፀባረቅ ባለፈ ገና ጅምር የሆኑ የፋሽን ኢንዱስትሪዎችን ለማነቃቃትና ሰፊ የሆነ የሥራ እድል ለመፍጠር ጥሩ መንገድ ነው እንደ አቶ ተመስገን። በአገር ደረጃ አንድ ሰሞን ላይ በስፋት እየተሰራበት ቆይቶ መልሶ የሚደበዝዘው አገራዊ ምርት የመጠቀም ባህል የማስተዋወቅና የማበረታታት ተግባር በተከታታይነት ስላልተሰራበት የተፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት አልቻለም የምትለው ዲዛይነር ሜላት ለኢንዱስትሪው እድገት ሥራው ተጠናክሮ መሰራት ይኖርበታል፡፡

በፋሽን ኢንዱስትሪው ተሳታፊ የሆኑ ተቋማት ምርትና አገልግሎታቸው በተጠቃሚው ዘንድ ተፈላጊና ተቀባይነት ማግኘቱ ለተቋማቱ ህልውና ወሳኙ ጉዳይ ነው። የሚያመርቱት ምርት ተጠቃሚው ጋር ደርሶ የሚያወጡትን ወጪ ሊሸፍኑ የሚችሉበት ገቢ ማግኘት ይኖርባቸዋል። አምርተው ለገበያ የሚያቀርቡት አልባሳት ወይ ሌላ ፋሽን ተኮር ቁስ ተጠቃሚው ሲሸምት ገቢያቸው አስተማማኝ በሆነ መልክ ይጨምራል።

ኢትዮጵያ ሰፊ የህዝብ ቁጥር የያዘች አገር እንደመሆንዋ በፋሽን ኢንዱስትሪ የሚመረቱ አገራዊ ምርቶች በአገር ውስጥ በስፋት መጠቀም ቢቻል አገራዊ ኢኮኖሚ ከመደገፍ ባለፈ ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር ያስችላል። በተለይም እንደ አገር ፋሽንን ለማሳደግ ከሚሰሩ ሥራዎች ውስጥ ህዝቡ በአገሩ ምርት እንዲጠቀም የማበረታታትና የማስተዋወቅ ሥራ ሊሰራ ይገባል። ከውጭ ከፍተኛ መዋለ ንዋይ ፈሶባቸው የሚገቡ የፋሽን ምርቶች በአገር ውስጥ ቢሸፈን የውጭ ምንዛሪን ማዳን ያስችላል።

ህብረተሰቡ አገራዊ ምርት መጠቀም ያለው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ እንዲያውቅ ከማድረግ ጎን ለጎን የምርቶቹን ጥራት መጠበቅም ሌላኛው ጉዳይ መሆኑ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ። በፋሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ምርት ተወዳዳሪ ከሚያደርጉት መሰረታዊ ጉዳዮች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ነጥቦች ምርቱ ለአይን የሚስብ መሆኑ፣ ሲጠቀሙበት የሚሰጠው ምቾት፣ የሚሰራበት ቁስ (ማቴሪያል) ጥራትና መሰል ጉዳዮች በትኩረት ማየትና የምርት ሂደት ተግባራዊ ማድረግ ይገባል።

የፋሽን ምርት ወደ ገበያ ሲቀርብ አልያም ለሸያጭ የሚቀርብበት መንገድ ምቹ ማድረግና አገራዊ ምርት ለአገር ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ማድረግ ወሳኙ ነጥብ ነው። አገራዊ ምርት መጠቀም ለአገር ካለው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አንፃር በትኩረት ሊሰራበት ይገባል የዛሬው መልዕክታችን ነው።

# ማረፊያ/ትዝብት

## ሲመሽ የታሉ?

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ፖሊስ መጀመሪያ ሲቋቋም የአራዳ ዘበኛ የሚል ስያሜ ነበረው። በወቅቱ አራዳ የሠለጠነ አካባቢ ስለነበረ እና በደጃች ውቤ ሠፈር በዶሮ ማነቂያ በሠራተኛ ሠፈርና በሰባራ ባቡር አካባቢዎች ውር ውር ስለሚሉ የአራዳ ዘበኛ ተባሉ፡፡ ንጉሥ ኃይለሥላሴ በሕግ ዙሪያ ማሻሻያዎችን ወስደው ነበር። የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እንዲወጣ፤ በእንግሊዞች የሰለጠነ ዘመናዊ ፖሊስ መሠረቱ፡፡እነዚህም አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማን ጨምሮ በሌሎች ከተሞች ነበሩ፡፡ቀይቶም በከተሞችና በኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር መስመሮች ፖሊሶች እንዲሠማሩ ተደርጎ ነበር፡፡

አገልግሎቱን ለማዘመን የተደረገው ጥረት ቀጥሎ በኮልፌ ልኳንዳ ፈጥኖ ደራሽ የሚባለው የፖሊስ ማሠልጠኛ ካምፕ ተቋቋመ፤ የደቡብ አፍሪካ የነፃነት ታጋይና በኋላም የሀገሪቱ መሪ የነበሩት ኔልሰን ማንዴላ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን የሰለጠኑበት እንደነበር “Long walk to freedom” ማለትም ረጅም ፍኖት ለነፃነት በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸው ጠቅሰዋል፡፡

መንግሥት ኃላፊነት የሚረከበው የዜጎች ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ነው። ዜጎች ሰላምና ደህንነት ሲጠበቅ ሠርተው ይኖራሉ ፣ወልደው ይስማሉ፣ ዘርተው ይቅማሉ ። ይቅማሉ ስል ወልዳችሁ ሳሙ፣ ዘርታችሁ ቃሙ ከሚለው የአዛውንቶች ምርቃት ተነስቼ ነው ፤እንጂ ጫት ቃሙ አለማለቴን አስቡ።

ከጮሌዎችም ከ‹ጨዋዎችም› ወገን ጫት የሚቅሙ መጠጥ የሚቀመቅሙም አሉ። ስለሚቀመቅሙ ካነሳን ዘንዳ ልብስም የሚቀመቅሙ ባለሙያዎች መኖራቸውን አንዘንጋ። ቤታቸውንም ከብታቸውን ውበታቸውን ንጽህናቸውን በየመስካቸው ጠባቂዎች አሉ፡፡ ከላይ ያነሳነውን የዜጎች የሰላምና ደህንነት ጠባቂዎች የሆኑትን ፖሊሶችን ሳንዘነጋ ነው።

የጠቀስናቸው ነገሮች ሁሉ የሚተገበሩት ሰላም እና ደህንነት ሲኖር ነው፡፡ፖሊስም በየአካባቢው የሚሠማራው የዜጎችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ወንጀለኛን ለመግታት ነው፡ ፡ማለትም ዜጎችን ከሌቦችና ከቀማኞች እየጠበቀ በሰላም ወጥተው በሰላም እንዲገቡ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው፡፡ የፖሊስ ግርማ ሞገሱ የደንብ ልብሱ ነው። አይደለም መሣሪያ ሳይታጠቅ ዱላውን ሳይጨብጥ ልብሱን አይተው የሚበረግጉ ሌቦችና ወንጀለኞች አሉ፡፡

ነገር ግን በቁንጽሉ አዲስ አበባን ስናያት በተለይ በምሽት ሕዝብ በሚበዛባቸው ዋና ዋና አደባባዮች ፖሊሶች የሉም ማለት ይቻላል፡፡ምግብ ቤቶች በጊዜ ይዘጋሉ። ምግብ በመብላት የሚናፍቀው አርሶአደርም ወዛደርም ላጤም ፅጉሩን እያከከ ይሄዳል ፤አማራጭ አጤ ይሆናል። ለምንድነው በጊዜ 3 ሰዓት ሳይሆን የምትዘጉት ያልኳቸው የምግብ ቤት አስተናጋጆች የሰጡኝ ቀኑን ሙሉ የሠራንበትን ገንዘብ ወጥተን ማለትም ወደ ቤት እየሄድን ሳይሆን እዚህ ሆነን በላተኛ መስለው ገብተው ገንዘቡን ይረከቡናል ። ገንዘብ ከመረከብ በዘለለ ለሕይወታችንም ስንሰጋ በጊዜ እየዘጋን መሄድን መረጥን ብለውኛል፡፡

አንዳንድ ጭፈራ ቤቶችና ቡና ቤቶች መግቢያቸውም ላይ ጥበቃ ስለሚያስቀምጡ ደንበኞቻቸውን የሚተናኮል አይገኝም። ሲመሽ ዶሮ በጊዜ ወደ ቆጥ እንደምትወጣው ሁሉ ሰውም ሌቦችና ቀማኞችን ፈርቶ በጊዜ ወደ ቆጡ (መኝታው) ይወጣል፡፡የዚሁ ነገራችን አንዱ ጣጣም የኪስ ስልኮች የመቀማት ልምድ መስፋፋት ነው፡፡

በአንዳንድ አካባቢዎች ከምሽቱ 12 ሰዓት በኋላ ወጣቶች ተኮልኩለው ሰዎች የያዙትን ስልክ በማየት አመቺ አጋጣሚ ሲያገኙ ይቀሙና ይሠወራሉ፡፡በጠቀስኩት ዕኩይ ተግባር የሚታወቁ ሠፈሮች አሉ፡፡በአንፃሩ አንዳንዶች ደግሞ በየጊዜው የሚሠረቅ ገንዘብና የኪስ ስልክ ቀማኞችን ለመግታት ነዋሪዎች ተደራጅተው የአካባቢው ታዳጊ ወጣቶችን አነጋግረው ሰላምና ፀጥታ የፈጠሩ ቀማኞችን ያራቁ አሉ፤እነዚህ ሊመሰገኑ ይገባል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ የደንብ ልብስና አርማውን መለወጡ እንዳለ ሆኖ ቸልተኛ እና ዘገምተኛ አሠራሩንም መለወጥና ማስተካከል አለበት። የደንብ ልብስ ስለተለወጠ ለውጥ አይመጣም። ፖሊስ ምሽት ላይ ስለማይታይ ታክሲዎች የአምስት ብሩን መንገድ 15 ብር ይጭናሉ። ሰው ደግሞ ለደህንነቱ እየሰጋ የማይከፈለውን ከፍሎ ቤቱ ይሄዳል፡፡ጎበዝ በሥፍራው የትራፊክ ፖሊስ አልያም ፖሊስ ቢኖር ይደረግ ነበር? ጥያቄውን ለናንተ ልተወው፡፡

ከሦስት ዓመት በፊት አንድ ታዳጊ ኳስ ዐይቶ ወደ ቤቱ አምስት ሰዓት ሲመለስ ቤቱ ፎቅ ላይ ስለሆነ ክፈቱልኝ ለማለት ስልክ ደወለ፤ የመርካቶ መሳለሚያ ዋናው አስፋልት ዳር በር ሲያንኳኳ የኪስ ስልኩን ያዩ ሰዎች ወግተውት ስልኩን ይዘው ተሠወሩ፡፡ቤተሰብ በር ሲከፍት ልጃቸው ወድቋል፤ደንግጠው ወደ ሆስፒታል ቢወስዱትም ሕይወቱን ማትረፍ አልተቻለም፡ ፡በአካባቢው ዞር ዞር የሚል ፖሊስ ቢኖር ይህ ድርጊት አይከሰትም ነበር። ቀማኞችም በርትተዋል ፤ይህም ባለቤቱን ካልናቁ አይነት ይመስላል፡፡

በቅርቡም በመሳለሚያ እሳት አደጋ አካባቢ ከንጋቱ 1 ሰዓት መኪኖች ተጋጩ፡፡የመኪኖች ግጭት እንጂ የተጎዳ ሰው አልነበረም። በዚህም በተፈጠረ የትራፊክ መጨናነቅ ሆነ ለ20 ደቂቃ ያህል ወደ መርካቶ፣ አራዳና አካባቢዎች የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች ቆመው ቀሩ፡፡ይህ ሁሉ ሲሆን ፖሊስም ትራፊክ ፖሊስም አልነበረም፡፡ዘግይቶ የትራፊክ ፖሊሱ ሲመጣ ግን የትራፊክ መጨናነቁ ተወገደ።

የሚያስቁኝን የፖሊስ እንቅስቃሴዎች ልጥቀስ ፤በየአካባቢው አስፋልት ዳር የሚነግዱ ነጋዴዎችን እኮ ሲያባርሩ ለማየት አንዳፍታ መርካቶ ሜክሲኮ እና መገናኛ አካባቢዎች ማየት ይቻላል፡፡ሰዎቹ የሚሠሩ እንደመሆናቸው መጠን ጥግ ጥግ ይዘው ወደ አስፋልት ሳይወጡ እንዲሠሩ ማድረግ ነው፡፡ገቢዎች ቢሮም የራሱን አማራጭ ፈልጎ ሥርዓት ማስያዝ ይችላል። የፖሊስ ዋነኛ ሥራ ወንጀል መከላከል ተፈጽሞም ከሆነ መርምሮ ለሕግ አካል ማቅረብ ነው። ማምሸትን የሚጠየፉት ፖሊሶቻችን ቀን ቀን ሠራተኛን ሲያባርሩ ይታያሉ ይሄስ ተገቢ ነው? ምሽት ላይ ግን አይታዩም፤ የፌዴራል የአዲስ አበባና የኦሮሚያ ፖሊሶች ያሉባት ከተማ ምሽት ላይ ፖሊሶች ማምሸትን ተጠየፉ ወይ ያስብለናል። አንዳንዴ ወደ ፒያሳ እና አውቶቡስ ተራ በየመንገዱ ጥግ ተገጥግጠው የሚሳድራቸውን ወንድ የሚጠብቁትን ሴቶች ሲያባርሩ ይታያሉ፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን በየሠፈሩ ኮሚኒቲ ፖሊሲ ተብሎ የተወሰኑ የተደራጁ ቡድኖች አሉ፡፡ቀን ቀን ባለችው ጠባብ ቢሮ ይውላሉ፤ነገር ግን ነዋሪዎችን አደራጅቶ ወንጀል ለመከላከል ተደራጅተው የሚጠብቁበት በየመንደራቸው መብራት ሊያበሩ የሚችሉበትን መንገድ ማሳየት ያስፈልጋል። የኮሚኒቲ ፖሊስ ብቻውን ያመጣው ውጤት ብዙውም ዐይታይም፡፡ግን በየሠፈሩ እየዞሩ መብራት አብሩ ብለው አካባቢውን እየዞሩ ይቆጣጠራሉ፡፡ይህ በራሱ መበረታታት አለበት።

በሸገር ባቡር ከምሽቱ 2 ሰዓት በኋላ ሥራ ያቆማል አንበሳ አውቶቡስም ተመሳሳይ ነው። ሰው በሥራና በተለያየ ምክንያት አምሽቶ ወደ ቤቱ ለመሄድ ትራንስፖርትም አጥቶ በእግር ለመሄድም ፈርቶ የሚታይ ፖሊስ አጥቶ መንከራተት የለበትም። ባቡርም አውቶቡስም የአገልግሎት ሰዓታቸውን ፈቅ በማድረግ ለነዋሪው አለሁልህ ይበሉት።

ከላይ የጠቀስኩት የሸገር የፖሊሶች ዝርክርክ አሠራር ግን እንዲስተካከል እንሻለን፡፡ማምሸትን የሚጠየፉት ፖሊሶቻችን የደንብ ልብሳቸውን ለብሰው በየመሸታ ቤቱ ያምሹ እያልኩ አለመሆኑን ከላይ ያነሳሁላቸው ነጥቦች ይናገራሉ፡ ፡ፖሊሶች የተቀጠሩት ካምፕ ውስጥ አልያም ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በምሽት ሊቀመጡ አይደለም። ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ አምሽተው የሚጠበቅባቸውን ሥራ የሚሠሩ አሉ ፡፡እየወጡ የሚሠሩ አሉ። ለሰዎች ሲታዩ ሌባው እራሱ ፍርሃት ፍርሃት ስለሚለው አካባቢውን ጥሎ ይሄዳል።

የሰረቁና ወንጀል የፈጸሙ አካላት ፖሊሶች እንደያዙዋቸው ያውቃሉ፡፡ወንጀል የፈጸሙ ፖሊስ ሲያያቸው ፍርሃት ፊታቸው ላይ የሚነበብባቸው ናቸው፡፡በዕለቱ የት የት ደርሰው እንደነበር ተነጣጥለው ሲጠየቁ አራምባና ቆቦ ምላሽ የሚሰጡ ከሆነ፤ ችግር እንዳለባቸው ፖሊስ ያውቃል። በቀላሉ ይያዛሉ፤ምርመራው ሲጣራ ደግሞ ከዚያ የበለጠ መረጃ ይኖራል፡፡የፖሊሶቹ ትጋት ታክሎበት በተለያዩ ክልሎች የሚሰሙ የፀጥታ ችግሮች ፤በሸገር ሳይደርስ እናስቀር በሚል ነው፡፡ፖሊስ የሰላም ዘብ፣ የህዝቦች ምርኩዝ እና አለኝታ ነው።

ይህን ስል ፖሊሱ በመደበኛ ሥራው የሚጠበቅበትን ግዴታ እየተወጣ ነው አለማቴን ከግምት አስገቡልኝ፡፡የፖሊስ ሥራ ቀኑን ሙሉ እና እረፍት የለሽ ነው፡፡በሰዓታቸው ለተረኛ ፖሊሶች ሥራውን ይቀየራሉ፡፡ቀማኛዎችን ማስወገድ የሚቻለው ፖሊሶች ግን በጎዳናዎች በእግርም ሆነ በመኪና ሲንቀሳቀሱና አካባቢውን ሲቃኙ ነው፡፡ፖሊሶች በምሽት በዋና ዋና ጎዳናዎች በእግር ዞር ዞር እያሉ ከተማውን ይቃኙ። ፖሊሶች በምሽት መጠለያ ጣቢያዎች ብቻ ቢታጨቁ ችግሩን መቅረፍ አይቻልም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

## ጅብ ከሚበላህ. . .

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

የነበረውን ፖሊሲ በአዲስ ቀየረች። በፊትለፊት ጦርነት ኢትዮጵያን ከመግጠም ተቆጠበች። ኢትዮጵያ ዓባይን ለመጠቀም እንዳታስብ ለማድረግ ሶስት የተጋመዱ ስትራቴጂዎች በአዋቂዎቿ አስጠንታ ተገበረች። እነዚህም በኢትዮጵያ የውስጥ ሰላም ማሳጣትና ዘወትር የማያቋርጥ ረብሻና ግርግር እንዲኖር ማድረግ አንደኛው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ዙሪያዋን በእሳት እንድትታጠር ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በድንበር ወይም በሌላ ሰበብ ፈጥሮ ኢትዮጵያን በጥርጣሬ ገፋ ሲልም በጠላትነት እንዲያዩዋት ማድረግ። ያንንም ክትትል አድርጎ ማጎልበት ነው። ሦስተኛው ዘዴዋ ደግሞ የዓለም አቀፍ አጋሮቿ በተለይም አሜሪካና አውሮፓ መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ ጫና እንዲፈጥሩ ማድረግ ነው። ይኸውም ኢትዮጵያ ለእርሻ፣ ለግድብ ሥራ ብድር እንዳታገኝ መዝጋት። በዓለም አቀፍ ደረጃም ኢትዮጵያን ተቀባይነትን ማሳጣት የሚያስችሉትን የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ነድፋ ተንቀሳቀሰች። እነዚህ ዘዴዎቿም ሠርተውላታል። ኢትዮጵያ ወደ ልማት ፊትዋን ሙሉ ለሙሉ አዙራ ለእድገቷ እንዳትሠራ ግብጽ በውስጥና በውጭ ባስቀመጠቻቸው አሽከላዎች በየአቅጣጫው ስትወጥር ለዘመናት በድህነት ቆይታለች።

ላለፉት 70 ዓመታት በተለይም በ1950ዎቹ መጨረሻ ዓመታት ጀምሮ ግብጽ እነዚህን ፖሊሲዎች በከፍተኛ ሁኔታ መተግበር ቀጥላለች። በ1959 ኢትዮጵያን አግልላ ከሱዳን ጋራ የአባይን ውሃ ለሁለት የተከፋፈሉበትን ውል ተፈራረመች። ቀጥሎም ጃንዋሪ 16 ቀን 1960 ኢትዮጵያን ሳታሳውቅ ትልቁን የአስዋን ግድብ አስጀመረች። በወቅቱ ኢትዮጵያ በአባይ ላይ የሚሠሩ ሥራዎችን አስመልክቶ እርሷም ባለድርሻ መሆኗንና ልትታለፍ እንደማይገባ ማስገንዘብና እርሷም አባይን ለልማት ልታውል የምትችልበትን ሁኔታ ማጥናት ስትጀምር ግብጽም በዚሁ ጊዜ ኢትዮጵያን ለማዳከም ከሆነም ለመበታተን ያግዛል የተባለውን ሥራ ሁሉ ለመተግበር ታጥቃ ተነስታ ያለመታከት መሥራቷን ተያያዘችው፡፡

ግብጽ የኢትዮጵያን ጂኦግራፊ ብቻ ሳይሆን ታሪኳን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ ሥርዓቷን እያንዳንዱ ብሔረሰብ ያለውን ስሜት ከኢትዮጵያውያን የበለጠ ጠልቀው በዝርዝር አጥንተው በሀገራችን ውስጥ የነበረውን የነገድ፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖት ልዩነት አጋኖ በመጠቀምና እርስ በርስ ማለያየት በጭር ጊዜ ያለብዙ ችግር ያሰበችውን ሊያስፈጽምላት እንደሚችል በመረዳት በዚሁ ዙሪያ ሥራዋን ቀጠለች።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሃይማኖት ልዩነት ማጋጋል ቅድሚያ ሰጠች። የካይሮ ሬዲዮ በአማርኛ፣ በሶማሊ እንዲሁም በአደሪኛ ቋንቋዎች ማሠራጨት ሲጀምር አላማው የሙስሊሙ ደጋፊ መስሎ ቀርቦ በኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ጦርነትን መቀስቀስ ነበር። የካይሮ ጋዜጦች ኢትዮጵያን እንደ ኢምፔሪያሊስት ቅኝ ገዥ ሀገር አድርገው ፕሮፖጋንዳቸውን በመርጨት ማነሳሳት ጀመሩ። ኢትዮጵያ የቅኝ ገዢ ስለሆነች ከእንቅልፋችሁ ንቁ ለነጻነታችሁ ታገሉ እያሉ ማነሳሳትና ያንድነት ማሰሪያዎችን ተፈትቶ እንድንለያይና እንድንደክም ያለዕረፍት መስራትን ተያያዘችው። እንዳሰበችው የኢትዮጵያ ህዝብ የሃይማኖት ጦርነት አንስቶ እርስ በርሱ በወቅቱ ባይጨፋጨፍም፤ ይህ ሥራዋ ውጤት አላስገኘላትም ማለት አይደለም። በ1960 የሙስሊሙን ክፍል አሳምና አነሳስታ የኤርትራ ነጻ አውጪ ድርጅት በካይሮ ሲቋቋም በምስራቅ አፍሪካ ደግሞ የሱማሌ መንግሥት ታላቋን ሶማሊያ የሚለውን መፈክር አንስቶ አጋዴንን ከኢትዮጵያ የመገንጠልና የሱማሌ ሪፐብሊክ አካል እንዲሆን ሁለገብ እርዳታዋን ቀጠለች (ሙሉ ዝርዝሩን Teferi Mekonen, The Nile Issue and the Somali –Ethiopian Wars (1960s-78), Annales d'Ethiopie, Annee 2018 ይመልከቱ)። የሱማሌ ብሔረሰብ በኬንያ ኢትዮጵያና ጂቡቲ ያሉ ሲሆን በኢትዮጵያ ላይ ብቻ በተደጋጋሚ ጦርነት የተነጣጠረባት ዋናው ምክንያት ከጀርባው ያለው ኃይለኛው የግብጽ ግፊት እንደሆነ ይታወቃል።

በካይሮ የተጠነሰሰው የኤርትራው እንቅስቃሴ በሀገር ውስጥ መዋቅሩን ዘርግቶ ቅስቀሳውን አሠራጭቶ ጎልብቶና ደርጅቶ ከብዙ ዓመታት የደም መፋሰስ የንብረት ውድመት በኋላ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ የብቻው ሀገር መስርቷል። ግብጽ የታሪክና የባህል አንድነት የነበራቸውን የኤርትራንና የኢትዮጵያን ህዝቦች ደም አቃብታ አለያይታለች። ኢትዮጵያም 17 ዓመታት በዘለቀው የርስበርስ ጦርነት ተዳክማ ከቀይ ባህር ተገፍትራ እንድትወጣ ተደርጋለች። በሱማሌ በኩል ባስነሳችው ከፍተኛ ጦርነት እጇ እንዳለበት አትሸሽግም። በ1960ዎቹም ሆነ በ1970ዎቹ የተቀሰቀሱትን ሁለቱንም ጊዜ የሱማሌን ጦርነቶች ብናሸንፍም እስካሁን የማይሽር ቁስል ተክላብን በየጊዜው እየተነሳ ያመረቅዛል። በእነዚህ ሁሉ ሂደቶች ግብጽ ኢትዮጵያ ቀና ባለች ቁጥር እየነካካች እያደማችን ትገኛለች።

በቅርቡ የኢትዮጵያ አንድነትን የሚፈልግ መንግሥት ሥልጣን ላይ ሲወጣ ትግሏን አፋፍማለች። በተለይም የዓባይ ግድብ ከፍጻሜ እንደሚደርስ ስታውቀው ንዴቷና ቁጭቷ የመጨረሻውን ጣሪያ ነክቷል። የሱዳን ጦር አልፈሽጋን ግዛታችንን እንዲይዝና በሱዳንና በኛ መካከል የማያባራ ግጭት እንዲኖር ሁኔታውን የጠነሰሰቺው ግብጽ ነች። የጋራ የጦር ልምምድም ካንዴም ሁለቴ አድርገዋል። ደግነቱ የምንጊዜም ወዳጃችን የሆነው የሱዳን ህዝብ እስካሁን አልተለየንም፣ እየተከላከለልንና እየተዋደቀልን ነው!!

በቅርቡ በአዲስ መልክ በተለያየ መንገድ ኢትዮጵያን ጎረቤት ሀገሮች የመነጠል ስትራቴጂ እየዞረች የወታደራዊ፣ የመረጃ ልውውጥ ወይም የኢኮኖሚ ትብብር በሚል ርዕስ ሰጥታ ስምምነቶችን ከሱዳን፣ ኬንያ ፣ዩጋንዳ ቡሩንዲ ጂቡቲ፣ ታንዛኒያ እና ደቡብ ሱዳን ጋር ተፈራርማለች። አንዳንዶቹን ወታደራዊ ተቋማችሁን ላደራጅላችሁ ትላለች። ኩታ ገጠም ድንበርተኞቻችንን ደግሞ የጦር ሠፈር እንድገነባ መሬት ምሩኝ እያለቻቸው ነው። በተለያዩ አቅጣጫዎች በሚፈሱ ወንዞቻችን ዙሪያም እንዳንጠቀምባቸው ጎረቤቶቻችን በዚህም ዙሪያ ቅሬታዎች እንዲያነሱብንና አጋዥ ለማግኘት ነገሮችን ጠቆም እያደረገች መሆኑ እየታየ ነው፡፡

ኢትዮጵያን ከዓለም ሀገሮች ለማግለል የሚደረገውን ጥረት ለማሳካት መሪዎቿ ለአፍታም የሚተኙ አይመስሉም። ሲጓዙ ይነጋባቸዋል። ኃያላን መንግሥታት ደግሞ ግብጽን እንደ እንቁላል የሚንከባከቡዋትና እሹሩሩ የሚሉበት ዋናው ምክንያት አውሮፓንና ኤሽያን የሚያገናኘውንና መተላለፊያ የሆነውን የስዌዝ ካናል/ቦይ ባለቤትና እንዲሁም ቀደም ሲል ባፈራችው ተሰሚነት ጸብ በተነሳ ቁጥር እስራኤልና አረቦችን ታስታርቃለች ስለሚሉ ነው። ስለዚህም እንድትከፋባቸው አይፈልጉም። እርሷም ይህን አስተሳሰባቸውን እስከ ጥግ አሟጣ እየተጠቀመች ነው። ትክክል ነች አይደለችም ሳይሉ አብረው ተባብረው ምስኪን ኢትዮጵያን በዲፕሎማሲው ፣በኢኮኖሚው እንዲሁም በፕሮፖጋንዳው የሚወቅጡት ለዚህ ነው።

ኢትዮጵያን ባልፈጸመቺው ወንጀል በዓለም አደባባይ ሸንጣቸውን ገትረው በተደጋጋሚ እየገተሯት ለማሸማቀቅ ይሞግቷታል። የመጨረሻውን የቴክኖሎጂ ውጤት የሆነውን የጦር መሳሪያ አስታጥቀው የሕዳሴውን ግድብ መምታት ነበረብሽ ብለው በገሀድ ያጀግኗታል። መገናኛ ብዙሃኖቻቸው በኢትዮጵያ ላይ የቅጥፈት ወሬ ፈጥረው የዓለምን ህዝብ ያደናግራሉ። የምክር ቤት አባሎቻቸው ከፍተኛውን ማዕቀብ በኢትዮጵያ ላይ ለማስጣል ይሽቀዳደማሉ። የሚገርመው አንዳንዶቹ ያሜሪካ ሰናተሮች ኢትዮጵያ በአፍሪካ ካርታ ላይ የት እንዳለች ማወቃቸውንም እንጃ። ለዓለም ሰላም፣ ለሰብዓዊ መብትና ዲሞክራሲ ዋስና ጠበቆች ነን የሚሉት የአሜሪካ መሪዎች በአሁኑ ጊዜ የወዳጆቻቸውን ፍላጎት በግድ በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን መንግሥትን ያቀረብነውን ተቀብለህ ፈጽም፤ አለበለዚያም 120 ሚሊዮን ህዝብህ ግሮሮ ላይ እንደሚቆሙ እየነገሩት ነው። በሩቅ ሁነን እንደምንሰማው አስበህ ነገረን ብለውታል። ውሳኔውንም እየጠበቁ ነው፡፡

በድህነት አቆራምደውን 120 ሚሊዮን ህዝብ አንገት ላይ ቆመው መንግሥት የሚፈልጉትን እንዲፈጽም እያስገደዱት ያሉት ምን ለማግኘት ነው?። ይኸ ሁሉ የዘመናት ግፍ በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጸመው የግብጽ ህይወት የሆነውን ዓባይን ገድበን ግብጽን የውሀ መጠን ቀንሰን አይደለም፤ ወይንም ህልውናዋን አደጋ ላይ ጥለንም አይደለም። በዓባይ ላይ ያለኝ የበላይነት ይወሰድብኛል ብላ ስለምትጮህ እሷን ለማስደሰት ነው። ከምንጩ ላይ ተፈጥረን ዓባይን በምንም ዓይነት እንዳንጠቀም ስለተፈለገ ነው።

ኃያላኑ የግብጽን ሽርክና እናቆያለን ብለው በኢትዮጵያ ላይ በሚፈጽሙት በደል በዓለም ፊት ክብርና ሞገሳቸው እየተገፈፈ ፣ እያደር እየቀለሉ ነው። ንዴታቸውም በዚያው መጠን ከፍተኛ ነው። እኔ በግሌ ከነርሱ ፍትህን መጠበቅ የዋህነት ነው። ምክንያቱም ምንጊዜም ወዳጃቸው ፍላጎታቸውን ያሟላ ብቻ ነው። ግብጾች እያንዳንዱ ብሔረሰብ ስለ ሌላው ያለውን ስሜት ከኢትዮጵያውያን ይልቅ ጠልቀው በዝርዝር አጥንተዋል። እንደዚህ ያለው ዝርዝር ጥናት ኢትዮጵያን ያለብዙ ችግር ለመከፋፈልና ለማለያየት የሚያስቡ ድርጅቶችን ለመፍጠር አስችሏል። በተለይም ኢትዮጵያ ኢምፔሪያሊስት ቅኝ ገዥ ሀገር ነች የሚለው የግብጽ ቅስቀሳ የዋህ ወጣቶችን ስቧል። ከኢትዮጵያ ነጻ እንወጣለን ብለው ሸር-ጉድ የሚሉ አድርባይ ድርጅቶች እንዲፈለፈሉ አድርጋለች። የትግራይ፣ የኦሮሞ፣ የቤኒሻንጉልጉሙዝ፣ የሱማሌ፣ የአገው፣ የኦጋዴን፣ የወላይታ የሲዳማ፣ የአፋር፣ ወዘተ. ነጻ አውጪ ድርጅቶች ነን እያሉ በሀገሪቱ ላይ የማያቋርጥ ሁከት በየቦታው የሚጭሩ ህዝቡን ሰላም የሚነሱ አብዛኞዎቹ የግብጽ ፕሮፓጋንዳ ሰለባዎች ናቸው። አንዳንዶቹ እርሷን ወክለው ኢትዮጵያን እየወጉ መሆናቸውን ግብጾቹ እራሳቸው በኩራት ይናገራሉ።

አንድ ጊዜ መሐመድ ሙርሲ የግብጽ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ወቅት በተደረገው በአንድ ቀጥታ ስርጭት በነበረ በህዳሴ ግድብ ዙሪያ በተካሄደ ስብሰባ ከታዳሚዎች መካከል የአንድ ፓርቲ መሪ ተነስቶ እንደገለጸው "ካስፈለግ በኢትዮጵያ ውስጥ ባደራጀናቸው ኃይሎች ኢትዮጵያን ማተራመስ ይቻላል" የተባለው በቀጥታ የተሠራጨና ገሀድ ወጥቶ ዓለም የሰማው ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በግድቡ አካባቢ የሚደረገው የጉሙዝ ነጻ አውጪ በሚባለው ድርጅት የሚካሄደው የንጹሀን ዜጎች ጭፍጨፋ ለግብጽ መንግሥት እንጂ ለጉሙዝን ህዝብ ጥቅም ነው እንዴ?!። የተሰጣቸው ተልዕኮ ስለሆነ በየቀኑ ንጹሀንን እየፈጁ ነው።

ከመቼ ወዲህ ነው ምስኪን የአማራ ገበሬ ኢምፔሪያሊስት ቅኝ ገዢ የሆነውና ዛሬ በተገኘበት እየተከበበ የግፍና የጭካኔ ድርጊቱ ጥግ በደረሰ ሁኔታ የሚፈጸምበት?። ምንም መሳሪያ የሌለውን የአማራን ምስኪን ድሀ ገበሬ ቤቱን ማቃጠል እርሱን መግደል፣ ሚስትና ሴት ልጁን መድፈር፣ የትግራዋይን ወይንም የኦሮሞን ወይንም የጉሙዝን ህዝብ ከምንና ከማን ነጻ ያወጣዋል?? የትስ ያደርሰዋል ?? ጥያቄውን አነሳሁት እንጂ ነጻ አውጪ ነን የሚሉትም ቢሆኑ ነጻ እናወጣለን ለሚሉት ህዝብ ጥቅም እንዳልሆነ ያውቁታል። ህዝቡም ጠመንጃ ስለያዙ ፈርቶ እንጂ ከመካከሉ አብሮት የኖረው ድሀ ገበሬ ጎረቤቱ አማራ ስለሆነ ብቻ ጨቋኝ ተብሎ እንደከብት ተጎትቶ ሲታረድ የኦሮሞ ህዝብም ይሁን የትግራይ ህዝብ ወይም ፣የጉሙዝ ሕዝብ የህሊና እረፍት ይሰጠዋል ብዬ አላስብም። ገዳዮቹ ግን አድርጉ የተባሉትን ነው እያደረጉ ያሉት።

ግፉን እየፈጸሙ ያሉ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የግብጽ ጦር ሠራዊት አካል ናቸው ማለት ይቻላል። እነዚህኮ በህዝቦቻችን መካከል መሽገው ለጠላቶቻችን ወግነው ጦርነቱን ጀምረውላቸዋል። መንገዱን ከፍተውላቸዋል ። እየተዋደቁላቸው ነው። ከነዚህ ነፍጥ አንስተው ሕዝቡን ከሚጨርሱት በተጨማሪ ሰላማዊ ትግል እያካሄድን ነው እያሉ ያለምንም ሀይ ባይ በህዝቡ መካከል መርዛም ንግግራቸው የሚረጩትን ድርጅቶችም ሆኑ የሃይማኖት አባቶች ነን ባዮች ከእነዚህም ተነጥለው የሚታዩ አይደሉም።

ነጻ አውጪ ነን ያሉትን ሁሉ ንጹሁን ከወንጀለኛው ሳትለይ ጨፍልቀህ ሁሉንም የግብጽ ቅጥረኞች ናቸው ብለህ ኮንነህል የሚል ካለ ምላሹ አዎ ነው። ነጻ አውጪ የሚለውን ስም ሲመርጡ ቢያንስ ከግብጽ ጋር በሃሳብ ማግጠዋል። በውስጣቸው መርዝ የሆነ የሀገር ጥላቻ አለ። የትግራይ ነጻ አውጪ ድርጅት 27 ዓመት ሲገዛ የአንድነትን ቋጠሮ አንድባንድ ሲበጥስ ከርሞ ከሥልጣን ሲወርድ ትግራይን ከኢትዮጵያ እገነጥላለሁ ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ እያለ ባለበት በአሁኑ ወቅት ግብጽም ምዕራባውያኑም ይህቺ ሃሳብ በሌሎችም ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ባላቸው ኃይል ሁሉ እየደገፉት ናቸው።

እዚህ ላይ ያለፉትም ሆኑ አሁን ያለው መንግሥት ህዝብን የሚያስከፋ ሥራ አይሠሩም፤ የህዝብ ብሶትና ምሬት አልነበረም ወይም የለም ማለቴም አይደለም። ያለፈውን ተውና በአሁኑ ሰዓት እንኳን በነዚህ ወንጀለኞች ላይ እርምጃ መውሰድ ሲገባቸውና መውሰድም እየቻሉ የማይወስዱ፣ እኩይ ተግባራቸውን እያወቁ የማይናገሩ፣ ሙያቸው የሚጠይቀውንና እጃቸውን አንስተው በህዝብ ፊት ለሙያቸው ክብር የማሉትን መሀላ ረግጠው ወንጀለኞችን ለፍትህ የማያቀርቡ የፍትህ አካላት የወጀለኞች አጎልማቾች መሆናቸውን አምናለሁ። ይህ ድርጊት ዜጎችን እያበሳጨ መሆኑን አላጣሁትም። ግን እነዚህን ባለሥልጣናትና ያንዳንድ ህብረተሰብ ክፍሎች ስህተቶችን አዚሁ በመታገልና በማስተካከል ፋንታ ሀገርን ለማጥፋት ዘወትር ከሚዶልት ጠላት ጋር ማበርን አላምንበትም። ጀግና የሆነ ትውልድ ሀገሩን አይከዳም። ከኢትዮጵያም መሰደድ መፍትሄ አድርጎ አይቀበልም። ምትክ አድርጎ የሚሰደድበት ሀገር ዋናዋን ሀገሩን በምንም አይተካለትምና!

ወደዋናው ነገሬ ለምለስና ግብጽ ይህን ሁሉ ማድረጓን እያየን እንዲህ መከበባችንን ስናውቅ፤ አባይን አንዲት ጠብታ ውሃ አትነኩብኝም ብላ ታጥቃ መነሳቷን ስንረዳ፤ የዓለም ኃያላንን አስተባብራ በውስጥ በገንዘብዋ የተገዙ ድርጅቶችን መሳሪያ አድርጋ በተለያዩ ዘዴዎች ያንድነት ማሰሪያችን በመበጣጠስ እንድንለያይ ያለእረፍት እንደምትሠራ ስናውቅ እንደዜጋ ምን እያደርግን ነን። ምን መደረግ አለበት ብሎ ህዝብና መንግሥት መምከር ያለባቸው አሁን ነው!! ዓባይንም ኢትዮጵያንም እንዳናጣ ልዩነታችንን ለሌላ ጊዜ አስቀምጠን አሁን እንተባበር! ለሀገር አንድነት ሲባል የዛሬን ችግር በጋራ እንቋቋም፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥትስ ምን ማድረግ አለበት? የሚል ካለም፤ እኔ የበኩሌን ሃሳብ እሰጣለሁ፤ ሌላውም እንዲሁ ይስጥ። የውስጡ ሰላም ማስጠበቅ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው። ሕዝባችን በየቦታው እየተገደለ ነው ። በሀገር ደረጃ ያፈራነው ሀብት እየወደመ ነው። ሰላም የለንም። የወደፊት ህይወታችን በተስፋ ዕየተሞላ አይደለም። በሀገር ውስጥ መሳሪያ አንስተውም ይሁን በወንበራቸው አማካኝነት ወይም በማይክሮፎናቸው ጫፍ እየወጉን ያሉትን የውስጥ አዳካሚዎች በጠንካራ ክንድ መንግሥትም በሚቻለው ፍጥነት ማስወገድ አለበት። ህዝቡ ሥራውን እንዲሠራ፣እንዲያመርት፣ ኢኮኖሚው እንዲስፋፋ ለማስቻል የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍሎ መንግሥት ሰላምን ማስፈን አለበት። አበው ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል እንዲህም ከሆነ ጅቡ ቀድሞ ከሚበላህ በልተከው ተቀደስ ይላሉ!! እኔም የምለው ይሄንኑ ነው፡፡

የሀገራችንን ዳርድንበር ለማስከበር የውሃ ሀብታችንን ለመጠቀም የውስጣችንን ሰላም ለማስጠበቅ የሚችለው መንግሥት ግልጽ አካሄድና የፈረጠመ ጉልበት ሲኖረን ብቻ ነው። ሥልጡን ወታደርና አሻግሮ የሚመታ መሳሪያ ከምጊዜም በላይ ዛሬ ያስፈልጉናል። ግድባችንን ቢመቱ የሚሳሱለትን ቦያቸውን የምንመታበት የተዘጋጀ ኃይል ያስፈልጋል። የሰላ አንደበትና ብቃት ያላቸው ዲፕሎማቶች የጠላቶቻችንን ሸር/ደባ በዓለም አደባባይ ለማጋለጥ ይረዱናል። እናም በዚህ መልኩ በሚቻለው ፍጥነት ማሰማራት ያስፈልግ ይመስለኛል ፡፡

በተለይ ወጣቱ በጽንፈኝነት እንዲንተከተክ የሚያደርጉትን የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ዓላማቸውን ተከታትሎ ይድረስበት። ጽንፈኝነትና የሃይማኖት አክራሪነት በቀላሉ በስሜት የሚያስገነፍሉና የአብሮነትን ብርሃን የሚያጨልሙ ናቸው።

እስካሁን የነበረን ጽኑ መቋቋም በአጠቃላይ ግብጽንም ሆነ ኃያላኑ መንግሥታት የውሸት ድለላ ተቋሞቻቸውና ነውረኛ ሥራቸው በዓለም ፊት በገሀድ እንዲታይ አድርጓል። በነጻነት የኖረ ህዝብ ጨዋና በቀላሉ ገፍትረው ክብሩንና ንብረቱን መንጠቅ እንደማይችሉ አሳይቷል። ይሁንና ጠላቶቻችን እጃቸው ረጅምና መምጫ መንገዳቸው ብዙ ነው። በየጊዜው ዙሩን እያከረሩት ነው። ዛሬ የመዘዙትን ካርድ (ኤች አር 6600 እና ተጓደኞቹ) በመንግሥት ዘዴኛነት በህዝብ አንድነትና ድጋፍ ይከሽፋል!

እኛም አንድነታችን እየጠከረ በእልህ የቅጣት ምታቸውን ፊት ለፊት ተደርድረን መከላከል አለብን። ጊዜ የለንም! ቸልተኝነት አያዋጣም። ቸልተኝነት በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ (1928-1933) ወቅት አባቶቻችንን ከባድ ዋጋ አስከፍሏል። የኢትዮጵያ ገዢዎች ጣሊያን ጦሩን ሲያስጠጋ ምሽጉን ሲምስ ድንበር ሲገፋ ፕሮፓጋንዳውን በህዝቡ ውስጥ እንደልቡ ሲያሰራጭ በውስጥ ሹኩቻ ላይ ተጠምደው ነበር፡ ጦርነቱ እደጃቸው ሲደርስ ነው በቂ ዝግጅት እንዳለነበራቸው ያወቁት። ጦርነቱ ሲከሰት የሰለጠነ ወታደር፣ ስንቅ ትጥቅ የህክምና እርዳታ በበቂ ባልተዘጋጀበት ሁኔታ ህዝቡ ከዘመናዊው የጣሊያን ወራሪ ጦር ጋር መጋፈጥ ነበረበትና ተማገደ። በጥንቃቄ ጉድለት ለአምስት ዓመታት በጅምላ የመሞት የመከራና የስደት ጊዜን እንዲያሳልፍ ተደረገ፡፡

አባቶቻችን ያቺን ወቅት አምስቱ የመከራ ዘመን ይሏታል፡፡እኛም ዛሬ ያቺን ታሪክ አንርሳ። መንግሥት ግብጽንም ሆነ ሌሎች ክፉ አሳቢዎችን የት ላይ እንደሚመታ አውቆ እዚህም ቤት እሳት እንዳለ የሚያሳይ ዝግጅት እንደሚኖረው አልጠራጠርም። እዚህ ላይ ብዙም አልናገርም። ሊገድል የመጣ ጠላት አባባ ቢሉት አይምርምና የሚመለከተው ያስተውል። ቸር ይግጠመን፤ አበቃሁ፤ ሰላም!

# ግብርና

## የበልግ ግብርና -

**ስምስም መንግሥቱ**

በምግብ ዋጋ መናር የዕለት ኑሮን መቋቋም ያለመቻል ጉዳይ መነጋገሪያ በሆነበት በዚህ ወቅት ስለበልግ የግብርና ሥራ፣እንዲሁም ምርትና ምርታማነቱ የሚገኝበትንና ምርቱ ደርሶ የእለት ኑሮአቸውን ሊያቃልላቸው ይችል እንደሆነ ተስፋ ለማድረግ መረጃው እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ሰዎች ጥቂት እንደማይሆኑ እንገምታለን። ይህን ታሳቢ በማድረግም የበልጉ የግብርና ሥራ በምን አይነት መልኩ እየተካሄደ እንደሆነ ትኩረታችንን በልግ አብቃይ ወደ ሆኑ የኢትዮጵያ አካባቢዎች አድርገናል። የበልግ መግቢያ ላይ ይጥል የነበረው ዝናብ ዋናው የክረምት ወቅት እስኪመስለን ድረስ ነበር ከባድ እንደሆነ ብዙዎቻችን ስንገልጽ የነበረው፡፡አሁን ግን ከባዱ ዝናብ በተለይ በከተማ እንደጅምሩ ሳይሆን ቀዝቀዝ ማለቱን ነው ትዝብታችን የሚያሳየው። የእርሻ ሥራ በሚከናወንበት በገጠሩም ቢሆን አጥጋቢ ዝናብ ስለመኖሩ እየሰማን አይደለም። የበልግ ወቅት የሚባለው ከየካቲት እስከ ግንቦት ያሉት ወራቶች በመሆናቸው ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረው ተስፋ ይደረጋል። የበልግ ዝናብ አብዛኛውን የሀገሪቱን አካባቢዎች የሸፈነ መሆኑና መዘናጋት ሳይኖር የተገኘውን እርጥበት በመያዝ በአግባቡ ለግብርና ሥራ ማዋል እንደሚጠበቅ ብሄራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ማሳሰቡ ይታወሳል። በልግ አብቃይ የሆኑት የደቡብና አማራ ክልሎች ወቅታዊውን ዝናብ ለግብርና ሥራ በማዋል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እያደረጉ ስላለው እንቅስቃሴና በአካባቢያቸው ስላለው ወቅታዊ የአየር ፀባይ መረጃውን አጠናክረን እነሆ ወደእናንተ አድርሰናል፡፡

በልግ ቀድሞ ከሚገባባቸው የሀገሪቱ ክፍሎች የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አንዱ በመሆኑ በቅድሚያ የክልሉን የግብርና እንቅስቃሴ እንደሚከተለው ቃኝተናል፡፡ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የገጠር ክላስተር አስተባባሪና የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር እንደገለጹልን፤ ክልሉ ከሌሎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች የበልግ ዝናብ ቀድሞ ያገኛል። የሚያገኘው ዝናብም ከ60 እስከ 70 በመቶ ይገመታል። የበልግ ዝናብ ቀድሞ በክልሉ የሚገባ በመሆኑ አርሶ አደሩ በልግ አምራች ነው፡፡ወደ ስምጥ ሸለቆ አካባቢ የሚገኙት ደቡብ ኦሞ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ከፊል ጋሞ፣ ኮንሶ፣ደራሼ፣ ታችኛው አካባቢ የሚባሉት ደግሞ ወላይታ፣ ከንባታ፣ ሀዲያ፣ ሀላባ፣ በቅደም ተከተል ዝናብ ያገኛሉ። በዚህ መነሻ የበልግ ዝናብ ከጀመረ አንድ ወር አልፏል። በወቅቱ የተገኘውን እርጥበት ለመጠቀምም አርሶ አደሩ ፈጥኖ ነው ወደ እርሻ ሥራ የገባው። በተከናወነው ሥራም ውጤቱ አንዱ ከሌላው አካባቢ ልዩነት ቢኖርም በአብዛኛው ጥሩ በሚባል ደረጃ እየተከናወነ የሚገኘው። የዘንድሮ የበልግ ወቅት ካለፉት የበልግ የግብርና ሥራዎች ለየት የሚያደርገው እንደ ሀገር በገጠመው የውስጥ ችግር፣ በዓለም ላይ ደግሞ የኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ መከሰት ያሳደረው የኢኮኖሚ ተጽእኖና በቅርቡ ደግሞ በሩሲያና ዩክሬይን መካከል እየተካሄደ ያለው ጦርነት የግብርና ግብአቶችና ምርቶች ዋጋ እንዲንር እንዲሁም ግብአት በበቂ ሁኔታ ላለማቅረብ ምክንያቶች ሆነዋል። ይህም ማዳበሪያን ጨምሮ የተለያዩ ግብአቶችን በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ አልተቻለም። የማዳበሪያ አቅርቦት አለመኖር ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ግምት ውስጥ በማስገባት አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂ ከመጠቀም ወደኋላ እንዳይልና እንዳይስተጓጎል ያሉትን አማራጮች በተለይም የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲጠቀም የንቅናቄ ሥራ በመስራት ክልሉ የበኩሉን ጥረት አድርጓል። ንቅናቄውን አጠናክሮ በመቀጠልም ውጤታማ ለመሆን እየሰራ ይገኛል።

ሌላው ክልሉ የገጠመው ተግዳሮት የበቆሎ ምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረት መሆኑን ኃላፊው ይናገራሉ። ክልሉ ቀደም ሲል የበቆሎ ምርጥ ዘር ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ከምዕራብ ወለጋ ነበር የሚያገኘው፡፡ በዚህኛው የበልግ የእርሻ ሥራ ከአካባቢዎቹ ማግኘት አልቻለም፡፡ እጥረቱ የተፈጠረው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሽመድመድ አልሞ የተነሳው የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ(ትህነግ)በከፈተው ጦርነት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልና ምዕራብ ወለጋ ውስጥ የነበረው የምርጥዘር ግብአት ሙሉ ለሙሉ በማውደሙ መሆኑን ጠቅሰዋል። ይህም ክልሉ የነበረበትን የበቆሎ ምርጥ ዘር አቅርቦት አስተጓጉሎታል። ክልሉ ቀደም ሲል የያዘውን የበቆሎ ዘር ክምችትና በአርሶአደሩ እጅ የሚገኘውን ጨምሮ አማራጮችን በመጠቀም በበልጉ ያጋጠመውን የበቆሎ ዘር አቅርቦት ችግር ለመፍታት ጥረት ተደርጓል። አቶ ኡስማን እንዳሉት፤ ክልሉ ያለውን የተፈጥሮ ፀጋና ምቹ የሆነ ሥነምህዳር ተጠቅሞ ከሰብል ልማት በተጨማሪ ለሥነምግብ ተመራጭ የሆኑ የሥራሥር ተክሎችን፣አትክልትና ፍራፍሬ የማልማት የቆየ ባህሉን የበለጠ በማጠናከር የበልጉን ወቅት በአግባቡ እንዲጠቀምበትም በንቅናቄው ምክረ ሀሳብ በመስጠት ተጠቃሚነቱ ከፍ የሚልበትን ሁኔታ አመቻችቷል።



**የበልጉ ዝናብ ሁኔታ በተፈጥሮ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ መጠንና ስርጭቱ ከፍ እና ዝቅ ሊል እንደሚችል ይጠበቃል፤**

> **ክልሉ ቀደም ሲል የያዘውን የበቆሉ ዘር ክምችትና በአርሶአደሩ እጅ የሚገኘውን ጨምሮ አማራጮችን በመጠቀም በበልጉ ያጋጠመውን የበቆሉ ዘር አቅርቦት ችግር ለመፍታት ጥረት ተደርጓል**

የበልግ ዝናብ ስርጭትና መጠኑ እየቀነሰ መሆኑ የበለጠ ጥሩ ውጤት እንዳይገኝ ያደርጋል የሚል ስጋት ቢኖርም የበልግ የግብርና ሥራ በተለያዩ ተግዳሮቶች ውስጥም ሆኖ ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ ይገኛል። ከዚህ በኋላም የሚገኘውን እርጥበት ማሳ ውስጥ በማስቀረት አሟጦ ለመጠቀም አርሶአደሩ ያለውን ግንዛቤ የበለጠ ከፍ እንዲያደርግ የክትትል ሥራዎች ይጠናከራሉ። ክልሉ ያሉትን ክፍተቶች በአማራጭ በማካካስ በበልጉ ዝናብ ለመጠቀም እያደረገ ባለው ጥረት በበልግ ዝናብ በመጠቀም ከስምንት መቶ ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በማረስ ስምንት አይነት በሚደርሱ ሰብል፣አትክልት፣ፍራፍሬና ስራስሮች ለመሸፈን አቅዶ በመሥራት ላይ ይገኛል። በበልጉ ከሚለሙት ዋና ዋና ሰብሎች መካከል በቆሎና ማሽላ ተጠቃሽ ናቸው። በአንድ ሄክታር በአማካይ ከሁለት መቶ እስከ ሶስት መቶ ኩንታል የሚገኝበት አጋጣሚ በመኖሩ ሰብልን ጨምሮ ከአጠቃላይ የበልግ ግብርና እና የልማት ሥራ ከ70 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡ የዝናቡ ሁኔታ ከተስተካከለ የምርት መጨመር ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በበልጉ ያጋጠሙ ችግሮች በእጅ የሚገኘን ፀጋ ወይንም ሀብት አሟጦ ለመጠቀም እድል በመስጠት ተሞክሮ የተገኘበት መሆኑን የተናገሩት አቶ ኡስማን «ሳይታይና ሳይመራ የቆየ ነገር ግን አሁን ላይ እየተከናወነ ያለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት አዲስ የሥራ ባህል ነው፡፡ነገር ግን መሬቱም ውሃውም ቀድሞ ነበረ፡፡የነበረው ክፍተት ችግሩን ሊፈታ የሚችል ሀሳብ አለመኖሩ ነበር። አዲስ የመጣው ሀሳብ ነው። በተመሳሳይ የአትክልትና ፍራፍሬ የማምረት ባህሉ አለ፡፡ይሁን እንጂ በብዛት አምርቶ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን የሚደረገው ጥረትና ከውስን አካባቢ የወጣ ልማት አለመካሄዱ ችግር ነው። ያለንን ፀጋ ቆም ብሎ በማየት አሟጦ በመጠቀም ያሉብንን ክፍተቶች በመሙላት ተጠቃሚነትን ከፍ ማድረግ ይጠበቃል፡፡አጠቃላይ የጀመርነውን የብልጽግና ጉዞ ከቤተሰብ እስከ ማህበረሰብ ብሎም እንደሀገር ወደ ብልጽግና ማማ ከፍ ለማድረግ ያለውን አማራጭ አሟጦ መጠቀም ትልቅ አጋጣሚ ነው፡፡አዲስ የሥራ ባህል መፍጠር ያስፈልጋል፡፡በዓመት አንዴ ለማምረት ይቸገር የነበረ ማህበረሰብ ዛሬ በዓመት ሶስቴና ከዚያም በላይ ለማምረት ፍላጎት እያሳየ ነው፡፡» በማለት ሀሳብ ሰጥተዋል።

በአማራ ክልልም በተመሳሳይ በልግ አብቃይ የሆኑ አምስት ዞኖች አሉ። በነዚህ አካባቢዎች እየተከናወኑ ስላሉ የበልግ ግብርና ሥራዎች የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ቃልኪዳን ሽፈራው እንደሚከተው ገልጸውልናል። የግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ እንዳሉት፤ በአምስቱ ዞኖች ወደ 218 ሺ 286 ሄክታር መሬት በበልግ ዝናብ የእርሻ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ ነው ወደ ሥራ የተገባው። በልጉ ከገባ ጀምሮ በተከናወነው የእርሻ ሥራ 196 ሺ 973 ሄክታር መሬት ታርሷል። ከዚህ ውስጥም ወደ 98 ሺ 461 ሄክታር መሬት በተለያየ የሰብል ዘር ተሸፍኗል። ደቡብ ወሎ፣ሰሜን ወሎ፣ሰሜን ሸዋ ከፊል አካባቢ በልጉ እንደገባ ወደ ሥራ ገብተዋል። ሥራው በዚህ መልኩ ቢከናወንም የበልግ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ የዘነበ ባለመሆኑና ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ዝናቡ በመቋረጡ ተጠብቆ የነበረውን ያህል የእርሻ ሥራ ተከናውኗል ለማለት አያስደፍርም። ከታህሳስ መጨረሻ ጀምሮ እስከ የካቲት ባሉት ወራቶች በአካባቢው የበልግ ዝናብ ይጠበቅ ነበር። ነገር ግን ዝናቡ በስርጭትና በመጠን ከሚጠበቀው በታች ነው የሆነው። ጥሩ ጊዜ የሚባለው የበልግ ወቅት እስከ የካቲት 20 ድረስ ባለው የዘር ሥራ መጠናቀቅ ስላለበት ከዚህ በኋላ ያለው ዝናብ የሚጠቅመው በዘር ለተሸፈነው መሬት ካልሆነ በልጉ እየተጠናቀቀ ክረምቱ እየቀረበ በመሆኑ ገና ለሚታረስ መሬትና በበልግ ዝናብ መቋረጥ በዘር ሳይሸፈን ለቀረው መሬት አይጠቅምም፡፡

የዝናቡ ሁኔታ በተፈጥሮ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ መጠንና ስርጭቱ ከፍ እና ዝቅ ሊል እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ በሚከናወን የግብርና ሥራ ወቅቱን ባገናዘበ አቅዶ መንቀሳቀስ ይጠበቃል። የሚጠበቀውን ምርትና በበልግ የሚመረቱ የምርት አይነቶችን በተመለከተ አቶ ቃልኪዳን ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ የሰብል ልማቱ ከአካባቢ አካባቢ ይለያያል። ሆኖም ገብስ፣ ምስር በስፋት ከሚጠበቁ የሰብል ምርቶች መካከል ይጠቀሳል። በአማካይ በሄክታር ከ18 እስከ 20 ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ነው በዕቅድ የተያዘው። ማዳበሪያን ጨምሮ የግብርና ግብአት አቅርቦት በዚህ የበልግ የግብርና ሥራ ከተነሱ ችግሮች ውስጥ ይጠቀሳል።

ክልሉ የግብአት አቅርቦት ችግር የፈታበትን መንገድ በተመለከተም አቶ ቃልኪዳን እንዳስረዱት፤ማዳበሪያና የግብርና ግብአት የሚያቀርቡ የህብረት ሥራ ማህበራት በወራሪው ኃይል ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ትህነግ) ጥቃት ተፈጽሞባቸው ሥራቸው በመስተጓጎሉና ግብአቱም በወራሪው ኃይል በመዘረፉ እጥረቱ ተከስቷል። በተወሰነ ደረጃ የተረፈ ቢገኝም ለበጋ መስኖ ልማት በመዋሉ ለበልግ የግብርና ሥራ በበቂ ሁኔታ ማዳረስ አልተቻለም፡፡ግብአቱን ከተለያዩ አካባቢዎች በማሰባሰብና የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) ጥቅም ላይ በማዋል ነው ለማካካስ ጥረት የተደረገው፡፡

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ባጋጠመው ጦርነት የተወሰኑ የክልሉ አካባቢዎች በጦርነት ቀጣና ውስጥ መቆየታቸው ይታወሳል። አሁን በተፈጠረው አንጻራዊ ሰላም የበልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የተከናወኑ ሥራዎችን አስመልክቶ አቶ ቃልኪዳን ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ጦርነቱ የተካሄደባቸው አብዛኞቹ አካባቢዎች በልግ አብቃይ ሲሆኑ፣ ሰሜን ወሎ፣ሰሜን ሸዋ በከፊልና ዋግ፣ በአጠቃላይ የክልሉ ምሥራቁ ክፍል ጦርነት የተካሄደባቸው ናቸው፡፡አንጻራዊ ሰላም እንደተገኘ በመኸሩ በሰብል የተሸፈነውንና የደረሰውን ሰብል በመሰብሰብ፣ በጦርነቱ ምክንያት ሳይታረስ ጾም ያደረገውን መሬት ደግሞ በመስኖ እንዲለማ በማድረግ፣የበልጉ ከተፈጥሮ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የዝናብ ችግር ያጋጥም ካልሆነ በስተቀር የተቻለው ጥረት ተደርጎ የግብርና ሥራው በመከናወን ላይ ይገኛል።

ከመኸሩ የግብርና ሥራ በኋላ በበጋ መስኖ ልማትና በበልግ የግብርና ሥራው በተከታታይ በመከናወን ላይ ይገኛል። ክረምቱም እየተቃረበ በመሆኑ የግብርና ሥራው ዓመቱን ሙሉ በመከናወን ላይ መሆኑን ማሳያ ነው። በኋላቀር መንገድ እየተከናወነ ባለው የግብርና ሥራ የትም መድረስ እንዳልተቻለ ተደጋግሞ በትችት እየተነሳ ያለው ይህ ዘርፍ ለውጥ እንዲያስገኝ በተከታታይ እየተሰራ ያለው ሥራ ይበል የሚያስብል ቢሆንም፣አሁንም በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ የሚያጋጥሙ ነገሮች በመኖራቸው ብዙ መስተካከልና ከዚህም በላይ ሥራ መስራት ይጠበቃል። አበረታች በሆነውና በተያዘው እንቅስቃሴ ከበጋ መስኖ ልማት ጀምሮ በክልሉ ስላለው ሁኔታ አቶ ቃልኪዳን እንደገለጹልን፤ መስኖ ከዝናብ ጥገኝነት የወጣ ስለሆነ፣በአካባቢው ያለውን የውሃ አማራጭና ቴክኖሎጂ በመጠቀም የተከናወነው የበጋ መስኖ ግብርና ሥራ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል። ለመኸሩ የግብርና ሥራ ዝግጅትም ጎን ለጎን እየተካሄደ ነው። እነዚህ ተከታታይ ሥራዎች ለምርትና ምርታማነት ማደግ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ስላላቸው፣ የግብርና ሥራው አሁን እየተካሄደ ባለበት ተከታታይ ሥራ ይጠናከራል። አሁን እየታየ ላለው የምግብ ዋጋ መናር ዋና መፍትሄው የግብርና ሥራውን ማጠናከር በመሆኑ ይበል የሚያሰኝ ነው።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የትምህርት ጉዳይ በትምህርት ባለሀብቶች ማህበር ዕይታ

**ግርማ መንግሥቴ**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በአዲስ አበባ፣ የመንግሥትንም ጨምሮ፣ በአጠቃላይ ፲ሺህ 522 ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ንብረትነታቸው ይለያይ እንጂ እነዚህ ሁሉ ለአንድ አላማ የሚሰሩ ናቸውና ከትምህርት ጥራት አኳያ መለኪያቸው፣ መስፈሪያ ሚዛናቸው አንድ ነው (ወይም፣ መሆን ይጠበቅበታል)። በመሆኑም ባለፉት ሳምንታት ከመንግሥት፣ በተለይም ከላይ ከጠቀስነው ባለስልጣን አኳያ አንዳንድ ሀሳቦችን አንስተን ተወያይተናል። በዚህ ጽሑፍ ደግሞ ከትምህርት ባለ ሀብቶች አኳያ ስለ ግሉ የትምህርት ዘርፍ እናወራልን።

ከግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ90 በመቶ ያላነሱት ቤት ተከራይተው የሚሠሩ በመሆናቸው፣ መንግሥት ያስቀመጠውን የትምህርት ቤት ግቢ ስፋት አያሟሉም፤ በመምህራን በኩልም መንግሥት የሚጠይቀውን መሥፈርት የሚያሟሉ ማግኘት አይቻልም፤ መንግሥት የሚጠይቀውን መሥፈርት ለማሟላት ሲባል ተማሪዎች የሚጠየቁት ክፍያ ከወላጆች አቅም በላይ ነው፤ የከተማዋን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘቡ ናቸው፤ አላማቸው ትርፍ ማግበስበስ ነው፤ ትውልድ መቅረፅ ላይ መስራት አይፈልጉም፤ ትምህርትን እንደ ማንኛውም በገንዘብ እንደሚገዛ ሸቀጥ ነው የሚያዩት ... እና የመሳሰሉት በግሉ የትምህርት ዘርፍ ላይ የሚሰነዘሩ ያልተቋረጡ ወቀሳዎች ሲሆኑ፤ እነዚህን ወቀሳዎች የግል ትምህርት ቤቶች አሰሪዎች ማህበር እንዴት ይመለከታቸዋል? የሚለውን ከማህበሩ ፕሬዚዳንት ከሆኑት ከአቶ አበራ ጣሰው የምረዳው ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

በእስከ ዛሬ የግል/የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውዝግብ ውስጥ የመንግሥት መምህራን ማህበር (ኢመማ)፣ ወላጅ ተማሪ ማህበርና የመሳሰሉት መኖራቸው እንጂ የግል ትምህርት ቤቶች አሰሪዎች ማህበር ስለመኖሩ ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም። በመሆኑም ስለ ትምህርት ጥራትም ሆነ መምህራን ተጠቃሚነት ጉዳይ ከእነዚህ አካላት ጋር ውይይት ሲደረግ አይስተዋልም። ከዚሁ አኳያ የዛሬው እንግዳችን ከሆኑት የአዲስ አበባ ከተማ የግል ትምህርት ቤቶች አሰሪዎች ማህበር ፕሬዚዳንትን አድርገናልና አብራችሁን ትዘልቁ ዘንድ እንጠይቃለን።

ሁሌም የግልም ሆነ የመንግሥት ትምህርት ተቋማት የአገሪቱን የትምህርት ፖሊስ ተከትለው እንዲሠሩና ብቁ ተማሪ እንዲያፈሩ ከማድረግ አንፃር፣ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ተባብረው መሥራት እንደሚገባቸው ሲነገር ቢሰማም ዳር ሲደርስ ታይቶ አይታወቅም። "አሁንስ?" ለሚለው ጉዳዩ አሁን እንደ አዲስ የተቀሰቀሰ ሲሆን ውጤቱንም ወደ ፊት የምናየው ሆኖ አዲስ ነገር ካለ ከማህበሩ ፕሬዚዳንት ጋር የምናደርገው ውይይት የሚነግረን ይሆናል።

አቶ አበራ ጣሰው ይባላሉ። የአዲስ አበባ የግል ትምህርት ቤቶች አሰሪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ናቸው። ያገኘናቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን በዲአፖል ሆቴል አዘጋጅቶት በነበረው የውይይት (ለትጉህ መምህራንና ትምህርት አመራሮች እውቅና የመስጠት ፕሮግራም) መድረክ ላይ ነው። ከመድረኩ ብቻም ሳይሆን ስለሚመሩት ማህበርና አጠቃላይ አላማው፤ እንዲሁም ስለ ትምህርት ጥራት ጉዳይ አነጋግረናቸዋል። "መድረኩን እንዴት አገኙት?" ለሚለው ጥያቄያችን ከሰጡት መልስ ጀምረንም እንደሚከተለውም አቅርበነዋል።

መድረኩ ጥሩ ነው መወያየት ያስፈልጋል፤ ተገቢም ነው። እኛም መተንፈሻ እናገኛለን። ግን ለውይይት የቀረበው ሰነድ አስቀድሞ ደርሶን ቢሆን ኖሮ ጥሩ ነበር። አልደረሰንም። የደረሰን አሁን ነው። አይተነው፣ አስበንበት፣ ተዘጋጅተንበት፣ ጥሩ የሆነ ግብአት ይዘን እንመጣ ነበር። ምንም እንኳን ውሳኔው የእነሱ፣ የመንግሥት ቢሆንም ለእሱም ግባት ይሆናቸው ነበር። ይሄ ነው እንጂ ችግሩ መድረኩ ጥሩ ነው።

የትምህርት ጥራትን በተመለከተ በእኛ በኩል፤ በግል ትምህርት ቤቶች በኩል ችግር የለም። በቅርቡ ትምህርት ሚኒስቴር ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ካሉት ተማሪዎች ከ65 በመቶ በላይ ማንበብና መፃፍ አይችሉም ያለውን በተመለከተ ለጠየከኝ በእኛ በኩል ምንም ችግር የለም። በራሱ፣ በግል ችግር ካልሆነ



ፎቶ፡ ናሆም አየለ

አቶ አበራ ጣሰው

> **ትምህርት ቤት ማለት ክፍል ብቻ ማለት አይደለም። ትምህርት ቤት ማለት ብዙ ነገር ማለት ነው። ልጆቹ መጫወቻ ቦታ ይፈልጋሉ። የሚሯሯጡበት ሜዳ ያስፈልጋቸዋል። ሌላም ሌላም**

በስተቀር ማንበብና መፃፍ የማይችል ተማሪ በግል ትምህርት ቤት ውስጥ የለም። በተለያዩ ምክንያቶች ግን እንደ አገር ሊኖር ይችላል።

አዲስ አበባን በተመለከተ ከአጠቃላይ ተማሪው 72 በመቶ የሚሆነው እኛ ጋ (የግል ትምህርት ቤት) ነው የሚማረው። የትምህርት ጉዳይ የመንግሥት ጉዳይ ነው ብለን ዝም አላልንም። የመንግሥትን ሸክም ለመጋራት፤ ለማገዝ በሚል ነው ወደ እዚህ ዘርፍ የገባነው። በመሆኑም ያለብን ኃላፊነት ቀላል አይደለም። የከተማውን 72 በመቶ ተማሪ ማስተናገድ ቀላል አይደለም።

ያሉብንን ችግሮች በተመለከተ በርካታ ናቸው። ያሉብንን ችግሮች ሁሉ እንግለፅ አንልም። ከሁሉም የባሰው ግን ትምህርት ቤት ለመገንባት የሚያስችለው የመሬት ጉዳይ ነው። በተደጋጋሚ ለግንባታ የሚሆን መሬት እንዲሰጠን ጠይቀን ሊሳካልን አልቻለም። "ይሰጥ አልነበረም ወይ?" ላልከው እሱ በፊት ነበር። በፊት ከባለቤቶቹ 20 በመቶ ከመንግሥት 80 በመቶ ተሸፍኖ በሊዝ ይሰጥ ነበር። አሁን እሱ ቀርቷል። እናም ትልቁ ችግራችን የመሬት ጉዳይ ነው። የትምህርት ባለሀብቱ እኮ በግለሰብ ቤት ነው ተከራይቶ እያስተማረ ያለው።

የስፖርት ሜዳ የለ፣ ምን የለ ላልከውም ይሄ እኮ በግልፅ የሚታይ ጉዳይ ነው። ምንም የለም። የቱ ጋ ሊኖር ይችላል። ለዚህ እኮ የግንባታ ቦታ እንዲሰጠን እየጠየቅን ያለነው። መንግሥት ለትምህርት ቤት መገንቢያ የሚሆን መሬት ለባለ ሀብቱ ቢያመቻች (ቢሰጥ) የግል ትምህርት ቤቶቹ ሌላውን ለማሟላት አይቸገሩም ነበር። ቦታ በሌለበት ግን እንዴት አድርጎ ነው አሁን ያልካቸውን ማሟላት የሚችሉት፤ አይቻልም። ትምህርት ቤቶቹ መጀመሪያ ከግለሰብ ቤት መውጣት አለባቸው።

ትምህርት ቤት ማለት ክፍል ብቻ ማለት አይደለም። ትምህርት ቤት ማለት ብዙ ነገር ማለት ነው። ልጆቹ መጫወቻ ቦታ ይፈልጋሉ። የሚሯሯጡበት ሜዳ ያስፈልጋቸዋል። ሌላም ሌላም። ስለዚህ፣ ይህ ሁሉ ግንዛቤ ተወስዶበት ለትምህርት ባለ ሀብቱ በቂ የሆነ የመገንቢያ ቦታ ሊሰጠው ይገባል።

የዋጋ (የትምህርት ቤት ክፍያ) ጭማሪን በተመለከተ አዎ ብዙ ጊዜ አለመግባባት ይነሳል። ተቃውሞም ግጭትም ይታያል። ግን ምን ማድረግ ይቻላል። ትምህርት ቤቶች የክፍያ ዋጋን የሚጨምሩት እኮ ወደው አይደለም። የትምህርት ግብአት ጉዳይ እየሆነባቸው ነው። የትምህርት ግብአት (የቤተ ሙከራ ኬሚካል ወዘተ) ዛሬ በገዛህበት ነገ አትገዛውም። ጨምሮ ነው የምታገኘው። በየጊዜው ሲጨምር ነው የሚታየው። ታዲያ ትምህርት ቤቶች ያላቸው እድል እኮ ክፍያ መጨመር ነው። የትምህርት ቤቶቹን ችግር የሚረዳ ይረዳዋል። የማይረዱም አሉ። የትምህርት ጉዳይ የሰው ልጅ ጉዳይ ነው። በሌላ ነገር መቀለድ ይቻላል። በልጆች ግን መቀለድ አይቻልም። በመሆኑም ትውልድ እንዲገነባ ካስፈለገ፣ ልጆቹ በሚገባ ሊማሩ፤ ማግኘት ያለባቸውን ትምህርት በሚገባ ሊያገኙ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ክፍያ የግድ ነው።

በነገራችን ላይ የግል ትምህርት ቤቶች አኮ ተመራጭ ናቸው። ባይሆኑ ኖሮ እኮ ይሄ ሁሉ (ወላጅ) ወደ እኛ ዘንድ እየመጣ ልጆቹን አያስገባም ነበር። ትምህርት በአግባቡ እንደሚሰጥ፤ ክፍያውም ተገቢ እንደ ሆነ ስለሚያውቅ ነው።

"በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን አማካኝነት ለውይይት በቀረበው ሰነድ ላይ አዳዲስ አሰራሮች ለታዳሚው ተዋውቀዋል። ለምሳሌ 'ግብረ ኃይል ማቋቋም ...' እና የመሳሰሉት። በዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?" ለሚለውም ፕሬዚዳንት አበራ ጣሰው አስተያየታቸውን የሰጡ ሲሆን "እኔ በበኩሌ 'ግብረ ኃይል ማቋቋም ...' ወይም '... ይቋቋማል' የሚለው ብዙም አያስደስተኝም። በሀይራርኪ አላምንም። በእንደዚህ አይነቱ መመሪያ ብዛት ምንም አይገኝም። የሚበጀው መነጋገር፣ መወያየት . . . ነው። ምንም እንኳን ወሳኙ ባለስልጣኑ፤ መንግሥት ቢሆንም ከእኛም ቢሆን ግብአት ስለማይታጣ መነጋገሩ ጥሩ ነው።" ነበር ያሉት።

በመጨረሻም "የሚያስተላልፉት መልእክት ካለዎት" ለሚለውም፤ እኛም ሆንን ባለስልጣኑ፤ ሁላችንም ተማሪዎቻችንን ማእከል አድርገን ነው የምንሄደው፤ መሆን ያለበትም ይኸው ነው። ይህ ደግሞ ትልቅ ኃላፊነትን የሚጠይቅ ከባድ ጉዳይ ነው። ዛሬ ተንበርከክ፣ እንዲህ ሁን ... የምንላቸው ተማሪዎቻችን ነገ አለቆቻችን ናቸው። መሪዎቻችን ናቸው። ነገ የእነሱ ነው። በመሆኑም ዛሬ በአግባቡ እነሱን ልናበቃቸው ይገባል። በመሆኑም እኛ፣ እንደ ትምህርት ቤት እነዚህን ልጆች፣ የነገ መሪዎች ከማብቃት አኳያ ትልቅ ኃላፊነት ነው ያለብን። የምንንቀሳቀሰውም ከዚሁ አኳያ ነው። እንደ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ደግሞ ምን ጊዜም እኛንም በማይጎዳ፣ ተማሪዎችንም በማይጎዳበት ሁኔታ ቢሰራ፤ እኛንም እየመከረ፣ እያሳተፈ ... ቢመራን ጥሩ ነው የሚሆነው።

ወላጆችም ልክ ክፍያ ተጨመረ ብለው እንደሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ወደ ትምህርት ቤቶች ብቅ እያሉ ልጆቻቸውንም መከታተል ይገባቸዋል። ምን ሲሰራ ዋለ፣ እየተማረ ነው ወይ፤ የመማር ማስተማሩ ሁኔታ ምን ይመስላል፤ ትምህርት ቤቱ ውሎው እንዴት ነው? .... የሚለውን ሁሉ መከታተል፤ ማወቅ አለባቸው። ትምህርት ቤት ብቻውን ምንም አያመጣም። የወላጆች ክትትል የግድ ያስፈልጋል። ወላጆች ይሄንን ማወቅ አለባቸው። የጎደለ ነገር ካለ ... ከትምህርት ቤቶቹ ጋር ቀረብ ብሎ በመመካከር ልጆቹን ተገቢ ቦታ ላይ ማድረስ ይገባል። አገሪቱን የሚረከቡት እንግዲህ እነሱ ናቸው። በመሆኑም እነሱን ማብቃት አለብን። አንዳንድ ወላጆች ዝም ብለው ከፍለው ልጃቸውን መላካቸውን ብቻ ነው የሚያዩት። ምንም አይነት ክትትል የማያደርጉ አሉ። ትምህርት ቤቱ ያስተምረው አያስተምረው፤ ግብአት ያቅርብ አያቅርብ ... ምንም የሚያውቁት ነገር የለም። ትምህርት ቤቱ እግዚአብሔርን ካልፈራ በስተቀር የሚከታተለው ወላጅ የለም። ይህ ደግሞ ስህተት ነው። ይህን ሁሉ ትቶ፣ ከትምህርት ቤቶችና አመራሮቻቸው ጋር በቅርበት ሆኖ፤ እጅና ጓንት ሆኖ መስራት ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ነው የታሰበው ሁሉ የሚሳካው።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# “ኤች አር 6600ም ሆነ ኤስ 3199 በኢትዮጵያ ታሪክ ከውጫሌ ቀጥሎ አሳሳች እና መላ ኢትዮጵያውያንን የሚጎዱ ረቂቅ ህጎች ናቸው”

**- አቶ እንዳለ ንጉሴ**

**በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር**

**ምህረት ሞገስ**

ኤች አር 6600ም ሆነ የኤስ 3199 ረቂቅ ህጎች በምክር ቤት ጸድቀው ተግባራዊ የሚሆኑ ከሆነ የሚኖራቸው ተጽዕኖ ምንድን ነው? ጉዳታቸው ምንያህል ነው? ከእዚህ ለመውጣት ምን መደረግ አለበት? የራሺያና የዩክሬን ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ የሚፈጥረውን ተፅዕኖ በሚመለከት እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴን አነጋግረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ወቅት ዲፕሎማሲ ላይ መሠራት ያለበት ምንድን ነው?**

**አቶ እንዳለ፡-** ውስጥ ላይ ደካማ ከሆንን ማንም አይሰማንም፡፡ከውስጥ ጠንካራ ከሆንን ውጪም ተደማጭ እንሆናለን። ዲፕሎማሲ የሚጀምረው ከውስጥ ነው። ለእዚህ ደግሞ እኛ ምቹ ነን። አሁን ከውስጥ የተከፋፈልን እንዲመስል ፕሮፖጋንዳ እየተሠራ ነው። በዓለም በየትኛውም አገር አንድ አይነት ባህል ወይም ሕዝብ የለም። በዓለም ያሉ አገራት ውስጥ የተለያዩ ባህሎች አሉ። በየሥራቸው ንዑሳን ባህሎች አሉ። በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ነው። ኦሮሚያ ቢሔዱ የተለያዩ ባህሎች አሉ። ጉራጌ ጋር ሲደርሱም የተለያየ ባህል አለ። ብዝሀነት የትም መኖሩ መታወቅ አለበት። ብዝሃነት ውበት እና ጥንካሬ ነው። ብዝሃነት መለያየት አይደለም።

ህወሓት ብዝሃነትን ልዩነት ብሎ ተርጉሞታል። ትክክል አይደለም። እኛ መለያየት አይመጥነንም። ሕዝቡ አንድነት ሲባል እንዴት እያለቀሰ እንደተቀበለ ታይቷል። መጀመሪያ መንግሥት ለአንድነት ዕውቅና ሰጥቷል። ከዚህ በፊት በነበረው ስህተት በንብረትም በሕይወትም ብዙ አስከፍሎናል በማለት ግልፅ ውይይት ተካሂዷል። ውይይቱ ሲያልቅ ወደ ጎረቤት አገር መኬዱም የሚታወስ ነው። ወንድሞቻችን እና ቤተሰባችን ከሆኑት ከኤርትራውያን ጋር እጅግ አሳፋሪ ውጊያ አካሂደዋል። ምክንያት የሌለው ውጊያ አካሂደናል። የአሜሪካ መንግሥት ስለፈለገው በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል ሰፊ ልዩነት ኖሮ እንዲቀጥል ያ ጦርነት ተካሒዷል። በዛ ጊዜ የተካሔደው ጦርነት ስለወደብ እና ስለድንበር ጉዳይ አይደለም። የደህንነት ጉዳይ ነው። የእኛ ህልውና ከኤርትራ ጋር የተያያዘ ነው። የእነርሱም ህልውና ከእኛ ጋር የተያያዘ ነው።

እኛ ጋር የሚፈጠረው ችግር ከሁሉም ቀድሞ የሚገባው ኤርትራ ላይ ነው። የእነርሱም እኛ ጋር ነው። ስለዚህ አንዳንዶች እንደውም ከገዛ ወንድሞቻችሁ ጋር ያልተስማማችሁ እንዴት ሌላ አገርን ታስታርቃላችሁ? እንዴት የአፍሪካ መዲና ትሆናላችሁ? ይሉ ነበር። ይህ ሁሉ አልፎ ወደ ጎረቤት አገር መግባት ተቻለ፤ አፍሪካ፣ ኤዢያ እና አውሮፓ ድረስ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በተመሳሳይ ከባቢ ውስጥ ገቡ። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን ለማስፈፀም የተመቸ ፖሊሲ ሆነ። ምክንያቱም ዲፕሎማሲ አገርን የሚወክል ነው። በአመለካከት ላንግባባ እንችላለን። ብዝሃነት አይመርጥም ሁሉንም የሚያገለግል ነው። ዲፕሎማሲ የሚያገለግለው ሁሉንም ነው።

ቀደም ሲል ዲፕሎማቶቹ የተወሰኑት ወጣ ብለው ይስሩ እንጂ ብዙዎቹ ንቁ አልነበሩም። በህወሓት ዘመን አንድ ጥያቄ ያቀረበ ሰው ከመባረር አልፎ ዕድሜ ልኩን እንዲሰቃይ ይደረግ እንደነበር አይዘነጋም። የሚጠይቅ አመራር፣ የሚጠይቅ ምሁርም ሆነ ዲፕሎማት አይፈለግም። ለዲፕሎማሲ ምቹ መሠረት ያስፈልገው ነበር። ለዛም የመከፋፈል መሠረት ተቀይሮ የዜግነት ዲፕሎማሲ መሆን ነበረበት አሁን ያ ሆነ። ይሄ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ለአገራቸው ዲፕሎማቶች እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን ፈጠረ። ይሄ ትልቅ አገር አምስት እና ስድስት በሆኑ ዲፕሎማቶች ወይም በተወሰኑ ኤንባሲዎች ሊሸፈን አይችልም። ይሄ ታይቷል።


ምርጫ፣ የሕዳሴው ግድብ እና የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ ውጪም ውስጥም ያሉ ኢትዮጵያውያን አንድሆነው በዲፕሎማትነት ታይተዋል። ይህ ምዕራባውያንን ያሳስባቸዋል። ስለዚህ ምዕራባውያን ኢትዮጵያውያንን የሚያዳክም የሚከፋፍል ሥራ መሥራት ጀመሩ። በተለይ በግለሰብ ደረጃ እነሰማንታ ሳይቀሩ ከሽብር ቡድኑ ጋር እጅግ የጠበቀ ግንኙነት የነበራቸው የኢትዮጵያ ነፃነት የማይጥማቸው ሁሉ ኢትዮጵያን ማዋረድ እንደሚፈልጉ ታይተዋል። አሁን ደግሞ ወደ ማስፈራራት መጥተዋል። የኢትዮጵያን ስም ወደ ማጥፋት ገብተዋል። እዚህ ውስጥ ሆኖ እንኳ ኤንባሲው ይሠራ የነበረው ታይቷል። በጣም የተሳሳተ ከትልቅ አገር የማይጠበቅ ውሸት ጭምር ሲያስተጋቡ ነበር። ያንን ከማድረግ አልፈው አሁን ፖሊሲ ወደ ማውጣት ገብተዋል፡፡

ኤች አር 6600ም ሆነ ኤስ 3166 ሁለቱም 95 በመቶ ተመሳሳይ ናቸው። በተለያየ መልኩ ጉዳዩ ወደ ታችኛው ምክር ቤትም ሆነ ወደ ላይኛው ምክር ቤት እንዲሔድ አስበዋል። እንደገና አመጣጡ የአንድ ፖሊሲ ሒደትን የጠበቀ አይደለም። አንድ ፖሊሲ ሲወጣ ሰባት ደረጃዎች አሉት። የመጀመሪያው አጀንዳ ሲወጣ ችግሩ ምንድን ነው? በሚል የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ይሠራል። ከዛ ፖሊሲ ለማውጣት የሚመለከታቸው አካላት ይወያያሉ። በእዚህ ላይ ግን የተወያየ አካል የለም። በተጨማሪ በእኛም በኩልም ሆነ በእነርሱ በኩል የተፈጠረ ክፍተትን አያሳይም። አሜሪካ ምን ምን ጥሩ ሥራ ሠራች? አሜሪካ ምን ጉድለት አሳየች? የኢትዮጵያ መንግሥት ምን ጥሩ ነገር ሠራ? በውጭ በኩል ተፅዕኖ ያሳደሩ ምን ጉዳዮች ነበሩ የሚሉት ጉዳዮች በሙሉ አልታዩም። ውይይትም አልተደረገባቸውም።

ህግ እያወጡ ያሉት እና ኢትዮጵያ ላይ ወደ መደፍደፍ የሔዱት ተጠያቂነትን ለመዝለል ነው። በዚህ በኩል ሁለቱም አካሄዳቸው አንድ አይነት ነው። ሂደታቸውን የጠበቁ አይደሉም። እዛው ራሳቸው በተገቢው መልኩ አልተወያዩባቸውም። ሌላው በፖሊሲ ቀረፃ ላይ ግብን ማስቀመጥ የሚባል ነገር አለ። ቅደም ተከተልም ይኖረዋል፡፡መጀመሪያ ይህንን እሠራለሁ፤ ቀጥሎ ይህንን እሠራለሁ ይባላል። ሶስተኛው ባይሠራስ የሚል ሶስተኛ አማራጭ ይቀመጣል። ዕቅድ አንድ ዕቅድ ሁለት ይባላል። ነገር ግን ይህም አልተደረገም። ይህንን ሁሉ ደረጃ ጠብቆ በተወካዮች ምክር ቤት ገብቶ መፅደቅ ነበረበት። ነገር ግን ደረጃውን ሳይጠብቅ ተዘጋጅቶ በላይኛውም ምክር ቤት በታችኛውም ምክር ቤት ፀድቆ ፕሬዚዳንቱ ፈርሞ ህግ እንዲሆን ብቻ ታስቧል። ማንኛውም ፖሊሲ ሲያወጡ እኛን ብቻ የሚጎዳ አይሆንም፤ እነርሱንም ይጎዳል። ስለዚህ ፖሊሲው ራሱ ሒደቱን ያልጠበቀ እና ከሽብር ቡድኑ ጋር ግንኙነት በነበራቸው ሰዎች ከፍተኛ ፍላጎት ኢትዮጵያ ላይ ጉዳት ለማድረስ ታስቦ የተሠራ መሆኑን ማንኛውም አካል ማወቅ አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ረቂቅ ህጎች በምክር ቤት ጸድቀው ተግባራዊ የሚሆኑ ከሆነ የሚኖራቸው ተጽዕኖ ምንድነው? ከእዚህ ለመውጣስ ምን መደረግ አለበት?**

**አቶ እንዳለ፡-** ረቂቁ ግልፅ የሆነ ጣልቃ ገብነት ነው። የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚጥስ፣ ታሪክን የሚሰርዝ የአሜሪካንም ሆነ የኢትዮጵያ ጥቅም የሚጎዳ ነው። አልፎ ተርፎ የግለሰቦች ጉዳይ ድረስ የሚገባ ሲሆን፤ ልክ እንደውጫሌው ላይ ላዩን ጥሩ መስሎ ውስጡ ግን በተዘዋዋሪ የቅኝ ግዛት ሃሳብ እና ፍላጎትን የያዘ ነው። ሰላም፣ መረጋጋት እና ደህንነት ቢልም ተግባሩ ተቃራኒ ነው። ኢትዮጵያ የደከመ ኢኮኖሚ ይዛ የደከመ ደህንነት ይዛ ያልተረጋጋች አገር እንድትሆን የሚያደርግ፤ እንደውም ጨርሶ የአዲሱ ቀኝ ግዛት ፖሊሲ ነው ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር እንዳትገናኝ ከአፍሪካ ህብረትም ሆነ ከዓለም ባንክ፣ ከዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ከማንም ጋር እንዳትገናኝ የሚያደርግ ነው። የማሰደም ፖሊሲ ነው።



ፎቶ፡ በኣይ አበፋቸው

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሊታሰብ የሚገባ አይደለም። ያ ቡድን ወደ መቃብር እየወረደ ነው። በህዝብ ልብ ውስጥ የሞተን ቡድን መመለስ አይቻልም። የትግራይ ህዝብም ቢሆን ተበዳይ ነው። 30 ዓመት ሙሉ በስማቸው ሲዘረፍ ቆይቶ ለአሜሪካ ደላሎች እና ለሎቢስቶች እየከፈሉ ኖረዋል። ለኢትዮጵያ የተሰጠው ዕርዳታ ተመልሶ የሚሔደው ለነዚሁ ሎቢስቶች ነበር። የጊዜው ቅንጡዎች የተወሰነ 2 በመቶ ዱባይ ቢዝናኑበትም ለእኛ ዕዳ እያስቀመጡ የሚልኩት መልሰው ወደ አሜሪካ ነበር።

አሁን ግን እንደዛ ጊዜ አይደለም። በዚህ ምክንያት የአሁኑ የእነርሱ ፖሊሲ የአፍሪካ ህብረትን ቻርተር የጣሰ ነው። በቻርተሩም ሆነ የአፍሪካ ሕብረት ሰብዓዊ መብት ቻርተር ላይ ቀኝ ግዛትን መዋጋት ዋነኛው መሥመር ነው። አሁን አዲሱ ቅኝ ግዛት የሚመጣው በፖሊሲ ነው። ይህንን ህግ አሜሪካ ራሺያ ላይ ወይም ሰሜን ኮሪያ ላይ ብታወጣ ብዙ ላይገርም ይችላል። በወዳጅ አገር በኢትዮጵያ ላይ ይህንን ማሰቧ ራሱ በጣም የሚገርም ነው። ኢትዮጵያውያንን የሚያዋርድ ነው። ቀን ያስቀምጣል። ለ10 ዓመት የሚፈፀም ይሆናል ይላል። ሁለቱም የሚወስኑት በፕሬዚዳንቱ ነው። ዲሞክራቶች ሁልጊዜም የውጪ ፖሊሲያቸው ችግር ያለበት ነው። በክሊንተን ጊዜ እነኢጎዝለቪያ ፈርሰዋል። በደላሎች እና በግለሰቦች የሚመራ ኢትዮጵያን ለማዳከም እና ብሎም ለማፍረስ ታስቦ የተዘጋጀው ይህ ሰነድ ማንም ኢትዮጵያዊ ሊደግፈው አይችልም፡፡

ኢትዮጵያውያን ከዚህ ኢትዮጵያን ከሚያዋርድ ሰነድ ጎን አይቆሙም። በእርግጥ ጥቂቶች ምንም ቢያደርጉ የማይመለሱ ከስልጣናቸው ውጪ ምንም የማያሳስባቸው አሉ። በማኪቬሊ ህግ የሚሔዱ ናቸው። ለስልጣን ሞራላዊም ሆነ ሞራላዊ ባልሆነ መንገድ ምንም ነገር ቢሆን የትኛውንም አድርግ የሚለውን መንገድ በመከተል ላይ ናቸው። ይሄ የማይለወጥ ባህሪ ነው። አንዳንዶች በደንብ የሕጉን ጭብጥ ሳይረዱ የሚናገሩ ይኖራሉ። ሆኖም ይሄ ነገር ቢወሰን ኢትዮጵያውያን የምንሆነው ባሪያ ነው። ነፃነት ሊተመን የማይችል ዋጋ ያለው ነው። ሊገዛ የሚችል አይደለም። ስለዚህ ነፃነታችንን አሳልፈን አንሰጥም።

**አዲስ ዘመን፡- የኤች አር 6600ም ሆነ የኤስ 3199 ጉዳት ምንድን ነው?**

**አቶ እንዳለ፡-** ጉዳቱ አንዳንዶች ባለስልጣንን ብቻ ወይም መንግሥትን ብቻ የሚነካ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ባለስልጣን አንድ አገር ቢከለከል ሌላ አገር መሔድ ይችላል። ቢቀርም ችግር የለም። ነገር ግን 99 በመቶ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ በኢኮኖሚ እንዳይንቀሳቀስ አድርጎ የሚጎዳ ነው። እዛ ያሉ ኢትዮጵያውያንን ራሱ ይነካል። ለምን ተንቀሳቀሳችሁ? እንዴት ሄዳችሁ? እያለ ውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ሳይቀር የሚያስጨንቅ ነው። ለቤተሰባቸው ብር መላክን በሚመለከት ራሱ እንዲያጣራ ይታዘዛል። ስልክ ደውሎ ማነጋገርን ይገድባል። የራሳቸውን የአሜሪካንን ህገመንግሥት ይጥሳል። የጄኔቫ ስምምነቶችን ይጥሳል። በአንድ

# ወቅታዊ

ሉዓላዊ አገር ውስጥ ጣልቃ ይገባል።

ኢትዮጵያ ደካማ እንድትሆን፤ መከላከያዋ ደካማ እንዲሆን ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ሕብረት እና ከአውሮፓ ሕብረት እንድትነጥል ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነው። ኤርፖርቶችም ሳይቀሩ አሁን ላይ ከኢትዮጵያ ጋር መሆን ይፈልጋሉ። የረቂቅ ህጎቹ ግብ መንግሥትን መጉዳት ሳይሆን ኢትዮጵያውያንን ማዋረድ ነው። ኢትዮጵያ ከሌሎች ጋር እንዴት መገናኘት እንዳለባት ሁሉ ያስቀምጣል። እንደውም በዝርዝር ላየው ሰው እጅግ አስገራሚ ነው። ኢትዮጵያ እነርሱ ካመጡባት የዘረኝነት መዘዝ ለመውጣት ጥረት እያደረገች ነው። ይህንንም ብዙ አገራት በመረዳት ላይ ናቸው። ለ30 እና ለ40 ዓመታት ወንጀል ሲሰራ የኖረውን ህወሓትን አንድም ቦታ ላይ አይጠቅሰውም። ስለዚህ ይህ ህግ የረቀቀው ኢትዮጵያን አዳክሞ ለግብፅ ለመስጠት ነው። ግብፆቹ እንደፈለጋቸው ያድርጓት፤ የሚል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን እነዚህን ረቂቅ ህጎች በመቃወምም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች እያደረጉ ያለው በጎ ተግባር በተለይ ለዲፕማሲያዊ ግንኙነት መጠናከር የሚኖረው አንድምታ ምንድነው? በተቃራኒው ጉዳዩን ሰፊ ቦታ አለመስጠት እና አልፎ አልፎም አንዳንዶች በተቃራኒው ለመደገፍ ዳር ዳር ይላሉ። በዚህ ላይ የእርሶ አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ እንዳለ፡-** ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ከድህነት መውጣት እና መልካም አስተዳደር ነው። በፊትም ቢሆን የተማሪዎች እንቅስቃሴ ላይ ዋለልኝ የፃፈው ፅሑፍ ምንም ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ፍፁም የሚገናኝ አይደለም። በእኛ ዩኒቨርሲቲ ፖለቲካል ሳይንስ ዲፓርትመንት አለ። ፊርማ እንኳን የሌለው አምስት ገፅ ፅሁፍ ነው። ይሄንን ግብፆች አሰናድተው የሰጡት ነው። አሁንም ይህ ህግ እንዲወጣ ለሴናተሮቹ ከፍተኛ ገንዘብ የሠጡት ግብፃውያን ናቸው። ብሩ ግን ሄደ የሚባለው በጁንታው በኩል ነው። ነገር ግን አሁን ለህወሓት ግብፆች ካልሠጧቸው እና ካልደገፏቸው በስተቀር እያለቀላቸው ነው።

ከህዝቡ አንፃር ከተወሰደ ኢትዮጵያውያን ጠንካሮች ነን። ያንን በጠንካራ መንግሥት እየተደገፈ ሲያስተዳድር የነበረን ቡድን መገፍተር ተችሏል። በውጪም ኢትዮጵያውያን በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ሳይቀር እየተቃወሙ ነው። ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊም ዝም ያለው አሜሪካንን ማባበል ስለሰለቸው ነው። ራሺያዎች ስለአሜሪካ ማስረዳት አይፈልጉም። ዩክሬን ላይ የደረሰው ይታወቃል። ሶሪያ እና ሌሎችም በነአሜሪካ ጦስ ፈርሰዋል። መንግሥት መጀመሪያ በፐብሊክ ዲፕሎማሲ በደንብ መንቀሳቀስ አለበት። የሕዳሴን ግድብ ገና ሳናጣጥመው ወደ ችግር ልንገባ ነው። ሰው ይህንን በደንብ ይረዳዋል። ነገር ግን ተራ ማዕቀብ አለመሆኑን ሕዝቡ እንዲረዳ መደረግ አለበት። ይህንን ማሳወቅ ደግሞ የምሁራኑ እና የሚዲያ ኃላፊነት ነው። በእኔ እምነት ኤች አር 6600ም ሆነ ኤስ 3199 በኢትዮጵያ ታሪክ ከውጫሌ ቀጥሎ አሳሳች እና መላው ኢትዮጵያውያንን የሚጎዱ ረቂቅ ህጎች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያ ከአሜሪካም ሆነ ከጥቂት ምዕራባውያን ጋር ያላት ግንኙነት እንዴት ይታያል? ይህንን ግንኙነት ለማጠናከር ምን መደረግ አለበት?**

**አቶ እንዳለ፡-** ምን መደረግ አለበት? ለሚለው የቤት ሥራው መሠራት ያለበት ከቤት ጀምሮ ነው። ኢትዮጵያን የሚያዋርዱ ትንንሽ ቡድኖች ቀይ መሥመር እንዳያልፉ ማገድ ያስፈልጋል። ሕዝቡ ራሱ ህወሓትን እና ሸኔንም ሆነ ሌላውን በቃ ማለት አለበት። ብዙ ሃሳብ ይኖራል። የተለያየ ፓርቲ እና የተለያየ ሃሳብ ፀጋ ነው። ነገር ግን በፓርቲ ስም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት መነካት የለበትም። ስለዚህ ህዝቡ አሁን እንደጀመረው ህወሓትን እና ሸኔን እረፉ ማለቱን መቀጠል አለበት።

ወሳኙ ነገር ቤት ውስጥ መሥራት ነው። ከዛ ቀጥሎ ውጪ ያሉት ኢትዮጵያውያን በዕውቀትም በገንዘብም ተንቀሳቅሰው ጁንታው የከፈለው ብር ያቅታቸዋል ተብሎ አይታሰብም። በእውቀትም ቢሆን ብቃት ያላቸው በቂ ኢትዮጵያውያን ውጪ አሉ። አሁን የዜግነት ዴሞክራሲ ነው፤ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል፤ ስለዚህ መንቀሳቀስ አለባቸው። ከዛ ቀጥሎ መጀመሪያ ኢትዮጵያ ማስረዳት ያለባት ለአፍሪካ ሕብረት ነው። ለጎረቤቶቻችንም ማስረዳት አለባት። የሕዳሴው ግድብ እየተሠራ ስለመሆኑ ሲወራ ያልታሰበብን ነገር የለም፤ ነገር ግን እኛ አያቅተንም። ሁሉም ይህንን ነገር ቢሰማ ባሕርዳርም ሆነ አርባምንጭ በየአቅጣጫው ሲሠራ የነበረው ብዙ ነበር። ነገር ግን ያ ሁሉ ቢሆንም በኢትዮጵያውያን ጠንካራ ድጋፍ እየተገባደደ ነው። ስለዚህ የነፃነት ተምሳሌት ከሆነችው ከኢትዮጵያ አልፎ ይህ ለአፍሪካውያን የሚተርፍ በመሆኑ ኢትዮጵያን መደገፍ እንዳለባቸው ማሳወቅ አለብን።



እጅግ የተሳሳተ እና ኒዮ ኮሎኒያሊዝም መሆኑን መንገር አለብን። ከዛ ደግሞ አሜሪካን ሊገዳደሩ የሚችሉ ትልልቅ የኢትዮጵያ ወዳጆች አሉ። ከእነርሱ ጋር መሥራት ያስፈልጋል። አሁን የተነደፈው የኢትዮጵያ ፖሊሲ እጅግ ጥሩ ነው። ወደ ቀኝም ወደ ግራም አይልም። አማካኝ ቦታን የያዘ ነው። ታሪኳን የሚመጥን ነው። ሁሉንም ያስተናገደች አገር ነች። የትኛውም ሃይማኖትም ሆነ ሌላ ዜጋ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ አልተሸማቀቀም፤ አልተዋረደም። ሰላማዊ ነው። ከዛ በኋላ ለአፍሪካ ህብረትም ሆነ ለተባበሩት መንግሥታት በይፋ እንዲህ ዓይነት ወዳጅነታችንን የሚያሻክር ፖሊሲ እየተነደፈ ነው ብለው ኢትዮጵያውያን መሥራት አለባቸው። መንግሥትም ማገዝ አለበት።

ነገር ግን ከውስጥ አሁን አንዳንድ ባለሥልጣናት የሚሠሩት ደስ አይልም። ወደ ፊት ቢወድቁ ጥሩ ነበር። ነገር ግን ወደ ኋላ ሕዝብ ወደማይፈልገው መውደቅ የሚፈልጉ አሉ። እነዚህን ሥርዓት ማስያዝ ያስፈልጋል። በቃ በሰላም ቤትህ እደር መባል አለባቸው። እነርሱ በሚፈጥሩት ስህተት አገሪቷ ዋጋ መክፈል የለባትም። እዚህ ላይ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። እዚህ ላይ መገናኛ ብዙሃን ቡድን ፈጥረው መሥራት አለባቸው። ጊዜያዊ ኮሚቴ መቋቋም አለበት። አውሮፓ ድረስ ቅርንጫፍን ማቋቋም ያስፈልጋል። ለደቂቃም ሳይዘገዩ መሥራት የግድ ነው። ወደ ልዩነት መሔድ ሳይሆን ብዝሃነታችንን አጣጥመን መቀጠል አለብን።

አሁን ብሔራዊ ውይይት ሊደረግ ነው። ከውይይቱ በኋላ ደግሞ ለውጦች ይኖራሉ። ሕገመንግሥት ይሻሻላል፤ ሌላም ሌላም ይሠራል። ነገር ግን ይህ እንዳይሆን ቀድመው ፈንጂ እየቀበሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለራሺያና ዩክሬን ምን ይላሉ? ኢትዮጵያ በእነርሱ ጦርነት የሚፈጠረውን ተፅዕኖ ለመቋቋም ምን ማድረግ አለባት?**

**አቶ እንዳለ፡-** ተፅዕኖ ብቻ አይደለም በረከትም አለው። አሜሪካኖቹ ከራሺያና ዩክሬን ጦርነት በፊት አፍሪካ ቀንድ አካባቢ ዝግጅት ሲያደርጉ ነበር። ብዙ አቅደው እንደነበር የሚታወቅ ነው። ህጉ ራሱ ከሶስት ወር በፊት ሊፈፅሙት ያሰቡት ነው። እዚህ ላይ ሌላውን ምን ያህል ለመጉዳት እንደሚንቀሳቀሱ ታይቷል። አሁን ግን ዓለም በምዕራቡ ብቻ የሚመራ አይደለም። ምዕራቡ አንድ ባለድርሻ ነው። ስለዚህ ድሮ እየመሩት በነበረ ሰዓት ከተጎዱ አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ ነች። ብዙ ዋጋ ከፍላለች። ከወንድሞቿ ጋር ተጣልታ የሰው ሕይወት ገብራለች። ግብፅ የበላይ እንድትሆን የማያደርጉት ጥረት የለም። ስለዚህ አሁን የዩክሬን እና የራሺያ ግጭት ኢኮኖሚካሊ በአሜሪካም ጭምር ተፅዕኖ አለው። እንደሚታየው ራሺያ ወደ ጦርነቱ የገባችው አስባበት አጥንታ እና ተዘጋጅታ ነው። ዩክሬን አልተዘጋጀችም የአሜሪካንን ትዕዛዝ ጠበቀች፤ አሁን አመድ እየሆነች ነው። አሜሪካኖቹ የሚፈልጉት ይህንን ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከራሺያ ጋር ያላት ግንኙነት ታሪካዊ ነው። ራሺያዎች እንደአሜሪካን አይደሉም። ራሺያዎች በኢትዮጵያውያን ላይ ችግር በተፈጠረ ቁጥር አብረውን ናቸው። ይህንን በሚመለከት ከጣሊያን ጀምሮ ያለውን የጦርነት ታሪክ በማጣራት መረጋገጥ ይቻላል። ተራ ምሳሌ ቢጠቀስ ባልቻ ሆስፒታልን መውሰድ ይቻላል። አሜሪካ አንድ ሆስፒታል እንኳ አልሠራችም። በእርግጥ ራሺያ ስትወጠር የሚጎድልብን ነገር ይኖራል። የዓለም ባላንስ ወደ ራሺያ እየሔደ ነው ይህ ዕድል ነው። አሜሪካኖቹን የሚያዋጣቸው ከአገራት ጋር አብሮ መሥራት ብቻ ነው።

አዳዲስ ተዋናዮች ሲመጡ፤ እንኳን ደህና መጣችሁ ማለት ያስፈልጋል። ቱርክ ከድሮ ጀምሮ ከኢትዮጵያ ጎን ናት። ከፋሲለደስ ጀምሮ ታሪክ ማገላበጥ ይቻላል። ፋሲለደስ አውሮፓዎችን ትቶ የሚሠራው ከቱርክ ጋር ብቻ ነበር። ስለዚህ ምዕራቡ ዓለም ይመራበት የነበረው አቅሙ በመቀነሱ ተጠቃሚ ነን። በተረፈ እኛ ማንም እንዲጎዳ አንፈልግም። ፖሊሲያችንም ይህንን አይልም። መስተጋብሩ በረከትም ያመጣል። አሁን ዝናብ እየመጣ ነው፤ ዝግጅትም እየተደረገ ነው። አሁን ኢትዮጵያውያን እንደነግብፅ አይደለንም። በዓለም ላይ የነዳጁም ሌላውም ብዙ ችግሮች አሉ። በተረፈ ለዓለም መረጋጋት እና ለዓለም ዴሞክራሲ እንዲህ ዓይነቱ ለውጥ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ከሳውዲአረብያ ብዙ ኢትዮጵያውያን እንዲመለሱ ጫና እየተፈጠረ ነው። ወደ አገር በመግባት ላይ ናቸው፡፡ይሄ የግብፅ አሻጥር ያለበት ይመስላል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ እንዳለ፡-** ይሄ መንግሥት ለዜጎች ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ የሚያሳይ ሲሆን፤ ሳኡዲ ይህንን ያደረገችው ለግብፅ ይሁንታ ብላ መሆኑ ግልፅ ነው። ኢትዮጵያ እና ሳኡዲ የፍላጎት ግጭት የለባቸውም ። እንደውም ኢትዮጵያ በቁርዓን አደራ የተሰጣች ነች። ሳኡዲዎች ገና አሁን በዩክሬን ምክንያት መንቃት የጀመሩ ይመስላሉ። ስንት አረብ አገራት በአሜሪካ ምክንያት ፈርሰዋል። አረብ አገር ቆሞ እንዳይሔድ ተደርጓል። በጣም የሃብት አገር የንግድ አገር ነበሩ። ብዙ ስልጣኔ መነሻው ከዛ ነው። ነገር ግን ምዕራቦች የእነርሱ ጊዜያዊ የማይጠቅም ሥልጣኔ እንዲታወቅ አስበው የሚያደርጉት ነው። ሰዎች ከስደት መመለሳቸው በኢኮኖሚው ላይ ጊዜያዊ ጫና ቢፈጥርም ጥቅምም አለው። ቻይና ሕዝቧ ብዙ መሆኑ በእጅጉ ጠቅሟታል። ዜጎቻችን ደግሞ እዛ ከሚሰቃዩብን ያለንን ቆሎም ቢሆን ብንካፈል ይሻለናል። አሁን በቅርቡ 100ሺህ ይመጣሉ ተብሏል። ቀላል አይደለም፤ በቤተዕምነትም ሆነ በሌላ መንገድ ሕዝቡ ድጋፍ ማድረግ አለበት። መጠንቀቅ ያለብን ይህን ያደረገው የሳኡዲ ሕዝብ አይደለም። የተወሰኑ የመንግሥታቸው ሰዎች ናቸው።

በተረፈ ግብፅ የተቋቋመችው የአረብ አገራትን ለማዳከም ነው። ግብፆች ከፍተኛ የመከፋፈል አቅም አላቸው። አሜሪካ ከእስራኤል ቀጥሎ ከፍተኛ ገንዘብ የምትረዳው ለግብፅ ነው። ይህም የአረብ አገራትን ለመከፋፈል ነው። የመን፣ ሊቢያ እንደዛ እየወደመ ዝም ብለዋል። በእርግጥ የራሳቸውን የሃይማኖት ህግ እየጣሱ መሆኑን ማሳወቅ ያስፈልጋል። በእርግጥ አሁን ዩክሬንን በተመለከተ ተለያይተዋል። ግብፅ ወደ አሜሪካ ሲያደላ ሳኡዲ ወደ ራሺያ እና ቻይና አድልታለች። እኛ ይሄንን ቀዳዳዎች መጠቀም አለብን። እርግጥ የአሜሪካንን ሰባት ሰዎች ስላባረርን እንዴት እንዳበዱ እናውቃለን ለዜጎቻችን ክብር አለመሰጠቱ ቢያበሳጨንም እኛም ከመቀበል ወደ ኋላ አንልም።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበርን ቆይታ እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አቶ እንዳለ፡-** እኔም እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## በሩሲያ ነዳጅና ጋዝ ምርቶች ላይ ሙሉ እገዳ ቢጣል የዩክሬንን ጦርነት ሊያስቆመው ይችላል

ምዕራባውያን አገራት በሩስያ ነዳጅና ጋዝ ምርቶች ላይ ሙሉ እገዳ ቢጥሉ በዩክሬን ያለውን ጦርነት ሊያስቆመው እንደሚችሉ የፕሬዚዳንት ፑቲን የቀድሞ የምጣኔ ሀብት ዋና አማካሪ ተናገሩ።

ዶክተር አንድሬይ ኢላሪዮኖቭ እንዳሉት ሩሲያ የሌሎች አገራት የሃይል አጠቃቀማቸውን ለመቀነስ የሚያደርሱትን ዛቻ በቁም ነገር ሩሲያ እየተመለከተችው እንዳልሆነ ገልጸዋል።

በሩስያ ኃይል ምንጮች ላይ ያለውን ጥገኛነት ለመቀነስ ቢሞክርም በአሁኑ ወቅት አውሮፓ ነዳጅ እና ጋዝ መግዛቱን ቀጥሏል ብለዋል።



ባለፈው ዓመት የዋጋ ማሻቀቡን ተከትሎ ለሩሲያ መንግሥት የገባው የነዳጅ እና የጋዝ ገቢ 36 በመቶውን ወጪውን ሸፍኗል።

አብዛኛው ገቢ የሚገኘው ከአውሮፓ ሕብረት ሲሆን፣ ሕብረቱ 40 በመቶ የሚሆነውን ጋዝ እና 27 በመቶውን ዘይት የሚያስገባው ከሩሲያ ነው።

በዚህ ሳምንት የሕብረቱ ከፍተኛ ዲፕሎማት የሆኑት ጆሴፕ ቦሬል "ፑቲን ለሚሰጠን ኃይል አንድ ቢሊዮን ዩሮ በየቀኑ እንከፍላለን" ብለዋል።

ዶክተር አንድሬይ ኢላሪዮኖቭ እንዳሉት "ምዕራባውያን አገሮች ከሩሲያ ወደ ውጭ በሚላኩ የነዳጅ እና የጋዝ ምርቶች ላይ እውነተኛ እቀባን ተግባራዊ ለማድረግ ቢሞክሩ ... ምናልባት በአንድ ወይም በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ የሩሲያ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች በዩክሬን ይቆማሉ ብዬ እገምታለሁ። " በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

"አሁንም በምዕራባውያን አገሮች እጅ ከሚገኙ በጣም ውጤታማ መሳሪያዎች አንዱ ነው" ሲሉም አክለዋል።

ከዩክሬን ጦርነት ጋር በተያያዘ የነዳጅ እና የጋዝ ንግዱ ቢቀጥልም፣ መጠነ ሰፊ ማዕቀቦች መጣላቸውን ተከትሎ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ቆመዋል፣ በርካታ የውጭ ኩባንያዎች ለቀው ወጥተዋል፤ እንዲሁም ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችም ተስተጓጉለዋል።

በቅርቡ የሩስያ ማዕከላዊ ባንክ ባደረገው አንድ ጥናት ኢኮኖሚው በዚህ ዓመት 8 በመቶ እንደሚቀንስ ሲተነብይ ዓለም አቀፉ የፋይናንስ ተቋም ደግሞ በ15 በመቶ ሊቀንስ ይችላል ብሏል።

ዶክተር አንድሬይ እንደሚሉት ፕሬዚዳንት ፑቲን በኢኮኖሚው ላይ የደረሰውን ጉዳት ለመቋቋም ዝግጁ መሆናቸው ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች የት እንዳሉ እንደሚያሳይ ጠቁሟል።

"የግዛት ማስፋፋት ምኞቱ፣ የንጉሠ ነገሥታዊ ምኞቱ ከየሩስያ ሕዝብ መተዳደሪያ እና የአገሪቱን የፋይናንስ ሁኔታ ጨምሮ፣ እንዲሁም ከመንግሥቱን የፋይናንስ ሁኔታ ጨምሮ ከሁሉ ነገር በላይ ናቸው " ብለዋል።

**ምንጭ ቢቢሲ**

## የፓኪስታኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካን ሴሊት በተደረገ ምርጫ ከሥልጣናቸው ተነሱ

የፓኪስታኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢምራን ካን ያለመተማመን ድምፅ ከተሰጠባቸው በኋላ ከሥልጣናቸው ተነሱ።

የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በአገሪቱ ሰዓት አቆጣጠር እኩለ ሌሊት አልፎ ነው የተካሄደው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኢምራን ካንን ከሥልጣን ለማንሳት ቀናት ያስቆጠረና ብዙ ድራማ የታከለበት ሂደት ውስጥ ነበሩ።



ተቃዋሚዎቹ ያለመተማመን ድምፅ አሰጣጡ ባለፈው ሳምንት ነበር እንዲካሄድ የፈለጉት። ነገር ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፓርላማውን በመበተን የድምፅ አሰጣጡ እንዲዘገይ አድርገዋል።

የእሑድ ድምፅ አሰጣጥ ሊካሄድ የቻለው የአገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሕገ-መንግሥታዊ ባልሆነ መንገድ ፓርላማው በትነዋል ብሎ በመበየኑ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ካን ባለመተማመን ድምፅ ከሥልጣን የወረዱ የመጀመሪያው የፓኪስታን መሪ ይሆናሉ።

የፓኪስታን እንደራሴዎች ሰኞ ዕለት ተገናኝተው አዲስ መሪ ይመርጣሉ። አዲስ የሚመረጡት መሪ በቀጣዩ የፈረንጆቹ ዓመት ጥቅምት ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ አገሪቱን ይመራሉ። 342 መቀመጫዎች ካሉት የፓኪስታን ፓርላማ ተቃዋሚ ፓርቲዎች 174 ድምፅ በመስጠት ያለመተማመን ሂደቱን ደግፈዋል።

የተቃዋሚ ፓርቲ መሪው ሼህባዝ ሻሪፍ ፓኪስታንና ፓርላማዋ "በስተመጨረሻ ከከፋ አደጋ ተገላገሉ" ሲሉ ትዊተር ላይ ለጥፈዋል።

### ዓለም አቀፍ ሤራ

ምንም እንኳ ማስረጃ ባይኖራቸውም ጠቅላይ ሚኒስትር ካን፤ በሩሲያና ቻይና ጉዳይ ድጋፍ ባለማሳየቴ አሜሪካ ከሥልጣን እንድነሳ ትፈልጋለች ይላሉ። ኢምራን ካን በተደጋጋሚ የአገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከውጭ ኃይሎች ጋር አብረው እየሠሩ ነው ሲሉ ይከሳሉ።

ዩናይትድ ስቴትስ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ክስ ውሃ አያነሳም ትላለች። ካን፤ ሩሲያ ዩክሬን ላይ ወታደራዊ ጥቃት ባደረሰችበት ወቅት ሞስኮው ሄደው ከፕሬዝደንት ፑቲን ጋር ተገናኝተዋል። አልፎም የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝደንት ጆርጅ ቡሽ ሽብር ላይ የሚደረግ ጦርነት ያሉትን ዘመቻም በግልፅ ይቃወማሉ።

ያለመተማመን ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የኢምራን ካን ወዳድና የታችኛው ፓርላማ አፈ-ጉባዔ የሆኑት አሳድ ቃይሰር ሥልጣን መልቀቃቸውን ይፋ አድርገዋል። ፒቲአይ የተባለው የኢምራን ካን ፓርቲ አባላትም ጠቅላይ ሚኒስትራቸው የዓለም አቀፍ ሤራ ተጠቂ ሆኗል በማለት ሕንፃውን ቀለው ወጥተዋል።

### ኢምራን ካን ማናቸው?

ኢምራን ካን የቀድሞው የፓኪስታን ክሪኬት ብሔራዊ ቡድን አምበል ነበሩ። ወደ ሥልጣን የመጡት በፈረንጆቹ 2018 ሲሆን ሙስናን ለመታገል፤ ምጣኔ ሀብቱን ለማስተካከል ቃል ገብተው ነበር። ነገር ግን ፓኪስታን ከገባችበት የፋይናንስ ቀውስ እስካሁን መውጣት አልቻለችም።

ኢምራን ካን በብዙዎች ዘንድ ቢወደዱም ባለፈው ወር በተነሳባቸው ተቃውሞ ምክንያት መንበራቸው መንገዳገድ ያዘ። የፓርቲያቸው ሴናተር የሆኑት ፋይሳል ጃቬድ ካን እንደሚሉት "ኢምራን ካን ወደ ቤተ-መንግሥቱ ያቀኑት በክብር ነው ሲወጡም አላጎበደዱም። "የጠቅላይ ሚኒስትር ካን ፓርቲ "መሪያችን አገራችንን ከፍ ከፍ አድርጓል" ይላሉ። **ምንጭ ቢቢሲ**

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የግል ትምህርት ተቋማትን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ለማድረግ ያለመ ውሳኔ

**እየሩስ ተስፋዬ**

አካል ጉዳተኞች ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር እኩል የመማር፣የመሥራትና በኢኮኖሚ የማደግ መብት እንዳላቸው ይታወቃል። የአካል ጉዳተኞችን የጉዳታቸው አይነት በማወቅ በሁሉም ዘርፍ ተጠቃሚ እንደሆኑ ማድረግ እንደሚገባም ብዙዎች በመፍትሔነት የሚለግሱ ምክር ነው።በትምህርት ዘርፉ በተለያየ እድሜ ውስጥ ያሉ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ እነርሱን ያማከለ ትምህርት መሰጠት እንዳበትም ይገልጻል። ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የግል ትምህርት ተቋማት የመማሪያ ከባቢው ምቹ አለመሆን፣የሚሠሩት ህንጻዎች እነርሱን ያማከሉ አለመሆንና የመማሪያ ግብአት አለመሟላትም ሕይወታቸውን ከማቅለል ይልቅ ፈታኝ እንዲሆን አድርጎባቸዋል ተብለው ወቀሳ ሲደርስባቸው ይስተዋላል።



አቶ ዐቢይ ደባይ፤

የግል ትምህርት ተቋማት የመማር ማስተማር ተግባሮቻቸውን ሲያከናውኑ ልዩ ትኩረት መደረግ እንዳለበት እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች አመቺ ሁኔታ እንዲፈጥሩ በአዋጅ ቁጥር 1152/2011 በአንቀጽ ቁጥር 41 ላይ ፈቃድ ተሰጥቷቸዋል። በዚህም መሠረት የማስተማሪያ ህንጻ ከባቢያዊ ሁኔታና የማስተማሪያ ግብአት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆን አስፈላጊውን ማሻሻያ አድርገው እስከ ሰኔ 30 ቀን 2014ዓ.ም ሪፖርት እንዲያደርጉ የኢፌዲሪ ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን መጋቢት 26 ቀን 2014ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ ውሳኔ ማስተላለፉ ይታወሳል።

ተቋማቱ የመማር ማስተማር ተግባሮቻቸውን ሲያከናውኑ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆኑን ልዩ ትኩረት እንዲደረግ የተቀመጠው የአዋጅ ድንጋጌ ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ የባለስልጣኑ ዋና ተግባር መሆኑን በመግለጽም፤ በቀጣይ በሚያከናውናቸው የእውቅና ፈቃድ እና የእውቅና ፈቃድ እድሳት አገልግሎት በዚህ አግባብ ተግባራዊ የሚያደርግ መሆኑ ባለስልጣኑ ማስታወቁም አይዘነጋም።

አቶ ዐቢይ ደባይ በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን የእውቅና አሰጣጥና እድሳት ዳይሬክተር ናቸው። እርሳቸው እንደሚገልጹት፤ የግል ትምህርት ቤቶች ለአካል ጉዳተኞች አመቺ ባለመሆናቸው ማሻሻያ እንዲያደርጉ የሚል ውሳኔ የተላለፈበት ምክንያትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ መሆን አለባቸው በሚል ነው። እንዲሁም የፌዴራል ዋና ኦዲተሮች መስሪያ ቤትም በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣን ከማስፈጸም አንጻር አብዛኞቹ የግል ትምህርት ተቋማት ለአካል ጉዳተኞች ማስተማር በሚገባቸው መንገድ ወይም መስፈርቱን እየተገበሩ እንዳልሆነም በግኝት መሠረት ተጠቁሟል።

በ መ ሆ ኑ ም ትምህርት ተቋማቱ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን እንዲቃኙ በማድረግ እንዲሁም የትምህርት ግብአታቸውንም ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ከማድረግ አንጻር የማሻሻያ ሥራ እንዲሠሩና ባለስልጣኑም ይህንን ተከትሎ የራሱን ግምገማ አድርጎ ርምጃ የሚወስድ መሆኑን የሚያሳውቅ ውሳኔ መሆኑን አቶ ዐቢይ ያስረዳሉ።

የተላለፈው ውሳኔ ተግባራዊ ስለመሆኑ ለማረጋገጥም የክትትል መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ወደ ሥራ የገባው ባለስልጣኑ ፤ተቋማቱ የሚያሳዩት ለውጥና እንዲበቁ የማድረጉ ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ተገቢውን ማስተካከያ ባላደረጉት ተቋማት ላይ ግን የእውቅና ፈቃድ እስከ መሰረዝ የሚያደርስ እርምጃ የሚወሰድባቸው እንደሆነም ዳይሬክተሩ ይናገራሉ።


እንደ አቶ ዐቢይ ገለጻ፤ ባለስልጣኑ በዋናነት ትኩረት አድርጎ የሚሠራው የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ሲሆን፤ የተስተዋለውን ጉዳይ ሰፋ አድርጎ ማየትን ያስፈልጋል። አንደኛው በመሠረታዊነት የሚነሳው ጉዳይ በሀገር ደረጃ ያለውን የህንጻ አዋጅ እና ሌሎችን አዋጆች አስገዳጅ መሆናቸውን ታሳቢ ከማድረግ አንጻር ብዙ ክፍተት ያለባቸው ናቸው።በተመሳሳይም የመንግሥትም ይሁን የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የችግሩ አካል ናቸውም ይላሉ።

ምንም እንኳን ከዚህ በፊት እንዲህ ዓይነቱ ችግር እንዳይስፋፋ ሙከራዎች የተደረጉ ቢሆንም አጥጋቢ ናቸው ብሎ ደፍሮ ለመናገር አዳጋች ነው። የትምህርት ጉዳይ የሀገሪቱ የህልውና ጉዳይ እየሆነ በመምጣቱ ፤ችግሩም ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ደፍሮ የመሥራቱም ነገር እምብዛም ነበር ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይም እንዲህ አይነቱ የቁጥጥር ሥራ በስፋት ይሠራል ብለዋል።እንዲህ አይነቱ ሕገ ወጥ ሥራ በሰፊው እየጨመረ በመምጣቱ ከሌሎች ከፌዴራልና ከክልል ተቋማት ጋር በጋራ በመተባበር የማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል ሲሉም ዳይሬክተሩ ያክላሉ።

አቶ ዐቢይ እንደሚሉት በአሁኑ ወቅት በዋናነት የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ አተኩሮ እየሠራ ሲሆን፤በተለይም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በአዲስ መልክ በመዋቀሩ የግል ትምህርት ቤቶች ላይ ብቻ ሳይገደብ በአጠቃላይ በትምህርት ዘርፉ ላይ ይሠራል።

በአንድ ተቋም ብቻ የቁጥጥር ሥራ የአይሠራም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ወላጆች፣ የትምህርት ማኅበረሰቡ፣ ባለድርሻ አካላት፣ ከላይ ጀምሮ ታች ያሉት የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ይህንን ጉዳይ የራሴ ነው ጉዳይ ብለው በመውሰድ ኃላፊነታቸውን በሚገባቸው መጠን እንዲወጡም ዳይሬክተሩ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

# ስፖርት



## የኢትዮጵያ ውሃ ዋና ቻምፒዮና በቢሾፍቱ እየተካሄደ ነው

ቦጋለ አበበ

የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን በየአመቱ ከሚያካሂዳቸው ትልልቅ የውድድር መርሃግብሮች አንዱና ዋነኛው የሆነው የኢትዮጵያ ውሃ ዋና ቻምፒዮና ከትናንት በስቲያ በቢሾፍቱ ከተማ ተጀምሯል። በመኮንኖች ክበብ የመዋኛ ገንዳ እየተካሄደ የሚገኘው የ2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ክለቦችና ክልሎች ውሃ ዋና ቻምፒዮና በወጣትና ልምድ ባላቸው ዋናተኞች መካከል በተለያዩ የውድድር አይነቶች ጠንካራ ፉክክር እያስተናገደ ይገኛል።

በውድድሩ የአማራ፤ የጋምቤላ እና የሲዳማ ክልሎች ተሳታፊ ሲሆኑ የድሬዳዋ ከተማ እና የቢሾፍቱ ከተማ ተወዳዳሪዎችም በተለያዩ ፉክክሮች ተሳታፊ ናቸው።

በክለብ ደረጃ ዳዊት እምሩ የህንፃ ተቋራጭ፤ ሳምሶን ውሃ ዋና ስፖርት ክለብ እና ኦሮሚያ ፖሊስ የሚሳተፉ ሲሆን አቻላ ያኮቤ በግል ተወዳዳሪ በመሆን አቅርቧል።

የውሃ ዋና ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰረት ደምሱ ውድድሩ በዋነኛነት ሁለት ዓላማዎችን ይዞ እንደሚካሄድ ገልጸዋል። ውድድሩ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የውሃ ዋና ስፖርተኞች ያሉበትን ወቅታዊ ብቃትና ደረጃ ለመለየት እንደሚረዳ የጠቆሙት ወይዘሮ መሰረት፣ በውድድሩ ጥሩ ብቃትና አቅም ማሳየት የቻሉ ስፖርተኞች በቀጣይ ለሚከናወኑ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ኢትዮጵያን እንዲወክሉ ለመመልመል እንደታሰበ አስረድተዋል።

"የስፖርት ልዩ ባህሪያት ሰላምን ለማስፈን ፣ መቻቻልን ፣ ሕግ መክበርን፣ አገርን መውድድን፣ የማሕበራዊ እና የልማት ትስስርን ለመፍጠር ትልቅ አቅም አለው" ያሉት ፕሬዚደንቷ ይህ ቻምፒዮናው የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት ፣ ለ2022 አህጉራዊና ዓለም አቀፍዊ ቻምፒዮና አገራችንን በመወከል ምርጥ ስፖርተኞች የሚመረጡበት ስለሆነ ተወዳዳሪዎች ጠንክረው በመወዳደር አቅማቸውን ማሳየት እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል።

በውድድሩ የመክፈቻ ሥነሥርዓት ላይ ንግግር ያደረጉት የቢሾፍቱ ከተማ አፈጉባኤ ወይዘሮ ሎምሽት እንዳለ በበኩላቸው "ከተማችን ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ተቻችሎ ፣ ተከባብሮ በእኩልነት የሚኖሩበት ፣ የሰባት የተፈጥሮ ሀይቅ ባለቤትና የቱሪስት መዳረሻ ከተማ ስለሆነች ከተለያዩ ክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች የመጣችሁ ልዑካን ቡድን እንኳን በሰላም መጣችሁ በማለት" በቆይታቸው ከጎናቸው እንደሚሆኑ ተናግረዋል።

በውድድሩ መክፈቻ እለት ከባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲሁም ከውሃ ዋና ስፖርቶች ፌዴሬሽን ሃላፊዎች የተገኙ ሲሆን በሁለቱም ፆታች በተለያዩ ዘርፎች ስምንት የማጣሪያ ውድድሮች ተከናውነዋል።

ቻምፒዮናው በተለያዩ የውድድር አይነቶች በሁለቱም ፆታ በነፃ ቀዘፋ፣ በጀርባ ቀዘፋ፣ በደረት ቀዘፋ፣ በቢራቢሮ ቀዘፋ፣ በድብልቅ ቅብብል ፣ በነፃ ቅብብል፣ በቅልቅል- ድብልቅ ቅብብል፣ በቅልቅል- ነፃ ቅብብል እና በግል ድብልቅ የፉክክር አይነቶች የሚካሄድ መሆኑን የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን የጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ቀልቤሳ ኤባ ገልጸዋል።

በውድድሩ መክፈቻ እለት በተደረገው የ200 ሜትር ነፃ ቀዘፋ ሴቶች የፍፃሜ ውድድር አማራ ክልል 1ኛ፣ ኦሮሚያ ፖሊስ 2ኛ እና ቢሾፍቱ ከተማ 3ኛ በመሆን ማጠናቀቅ ችለዋል።

"ስፖርት ለሰላም ለህብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል የሚካሄደው የ2014 ዓ.ም የክልሎች እና የክለቦች የውሃ ዋና ቻምፒዮና እስከ ሚያዝያ 8/2014 ዓ.ም በተለያየ የውድድር አይነቶች በርካታ ፉክክሮችን አስተናግዶ አሸናፊዎቹ የሚለዩ ይሆናል።



ለሰባት ቀናት በሚካሄደው ውድድር ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች የሚወክሉ ዋናተኞች ይመረጣሉ፣


## ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጅማ ዲስትሪክት በሊዝ ፋይናንሲንግ ሥርዓት የብሎኬት ማምረቻ ማሽነሪዎች እና ተጓዳኝ መገልገያ ማሺኖች በኪራይ ወስደው የነበረና ከዚህ በታች ስማቸው የተጠቀሰው የማሽን ተከራይ ከባንኩ ጋር በተዋዋሉት የካፒታል ዕቃ ዱቤ ኪራይ ውል ስምምነት መሰረት ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት ባንኩ የተረከበውን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማሽነሪዎች ባሉበት ሁኔታ በድርድር ጨረታ ለመሸጥ ወይም ለማከራየት ይፈልጋል፡

| ተ. ቁ. | የተከራዩ ስም | ንብረቱ የሚገኝበት ቦታ | የንብረቱ ዝርዝርና አይነት | የጨረታ መነሻ ዋጋ | የሐራጁ ደረጃ | ሐራጁ የሚካሄድበት ቀንና ሰአት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አሰጋኸኝ ተፈራ ወሰን | ጅማ ከተማ ውስጥ | ✓ Hollow Block making Machine<br>✓ Concrete mixer<br>✓ Pipe mold(20 diameter)<br>✓ Pipe mold (30 diameter)<br>✓ Pipe mold ring (20cm diameter)<br>✓ Pipe mold ring (30 cm diameter)<br>✓ Vibrating Table<br>✓ Plastic mold 30cm*30 cm<br>✓ Plastic mold 40cm*40cm<br>✓ Pumice crusher<br>✓ JCB Diesel Generator | 1,988,329.91 | በድርድር | ግንቦት 04 ቀን 2014 ዓ.ም ከ 4፡00-6፡00 |

### የሐራጁ መመሪያ፡-

- በጨረታው መሳተፍ የሚፈልግ ማንኛውም አካል (ግለሰብ፣ ተቋማት ወይም አነስተኛና መካከለኛ ማህበራት) ከቀረጥ ነጻ የመጠቀም ተመሳሳይ መብት ያለው ከሆነ ወይም መንግስት በንብረቶቹ ላይ የሚያስከፍለውን የጉምሩክ ቀረጥ ለመክፈል ፍቃደኛ የሆነ ሁሉ በጨረታው መሳተፍ ይችላል፤
- ንብረቱን መከራየት/መግዛት የሚፈልግ ተጫራች የጨረታውን መነሻ ዋጋ 1/4ኛ በጥሬ ገንዘብ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ ጨረታው በሚከናወንበት ቀን ይዘው በመቅረብ በጨረታው መሳተፍ ይችላል፤
- ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ግንቦት 04 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:00 እስከ 6፡00 ሰዓት ጅማ በሚገኘው የባንኩ ዲስትሪክት ይከናወናል፤
- ለተሸነፉት የጨረታው ተሳታፊዎች ያስያዙት ገንዘብ ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል፤
- ንብረቱን ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ለመግዛት ተወዳድሮ ያሸነፈ ተጫራች ቀሪውን ገንዘብ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ አጠቃሎ መክፈል ይኖርበታል፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አጠቃሎ ካልከፈለ የጨረታው አሸናፊነቱ ተሰርዞ ያስያዘውን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለባንኩ ገቢ ይሆናል፤
- ንብረቱን በከፊል መከራየት የሚፈልግ ተጫራች የባንኩን የማሽነሪ ኪራይ መስፈርት ማሟላትና ቢያንስ 1/5ኛ ቅድሚያ ያሸነፈበት ዋጋ መክፈል ግዴታ ይኖርበታል፤
- አሸናፊው ተጫራች ንብረቱን ለመከራየት የሚፈልግ ከሆነ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የባንኩን የማሽነሪ ኪራይ መስፈርት በማሟላት እና የሚጠበቅበትን ክፍያ አጠቃሎ በመክፈል የማሽነሪ ኪራይ ውል መፈረም ይኖርበታል፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ግዴታውን ካልተወጣ የጨረታው አሸናፊነቱ ተሰርዞ ያስያዘውን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለባንኩ ገቢ ይሆናል፤
- የጨረታው አሸናፊ ንብረቶችን በጥሬ ገንዘብ ወይም እጅ በእጅ ሽያጭ የሚገዛ ከሆነ ከቀረጥ ነጻ መብት የመጠቀም ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ከቀረጥ ነጻ የመጠቀም መብት ከሌለው በመንግስት የሚጠየቁ ማንኛውንም ቀረጥ መክፈል ይኖርበታል፡፡
- ጨረታ አሸናፊው የንብረቱን የሽያጭ ዋጋ 15 በመቶ ተ.እ.ታ (VAT) ጨምረው የመክፈል ግዴታ አለባቸው፣
- ስለ ማሽነሪዎቹ ዝርዝር እና ተጨማሪ መረጃን በተመለከተ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጅማ ዲስትሪክት ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር 047-111-09-08/047-111-00-16 ደውሎ ማነጋገር ወይም በአካል ቀርቦ ማሽነሪዎቹን ማየት ይቻላል፡፡
- ባንኩ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይንም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

## የኢትዮጵያ ልማት ባንክ